# ምዕራፍ ዐርባ አምስት

## የኢጣሊያ ጦር መፍረስና ቅጥ ያጣ ሽሽት

ቁጥሩ ሐያ ሺ የሚደርሰው ባንድ ሌተና ጄኔራልና ባራት ማዦር ጄኔራሎች የተመራውና ጦርነት የጠማው ፣ ሰላም ያንገፈገፈው የኢጣልያ ጦር እነሆ ባዬ ምኒልክ የጦር ሠራዊት ተመትቶ ፍርስርሱ ወጣ ። የሞተው ሞቶ የተረፈው ሸሸ ። ከአልቤርቶኒ ጦር የተረፈው ወደ ሳውሪያ ፣ ከዳቦርሚዳና ከአሪሞንዲ ጦር የተረፈው በዬሃና በመሬት ማይ በኩል አድርጎ ፊቱን ወደ መረብ ፣ ወደ አዲ ቀይህ ፣ ወደ አዲግራት ፣ ወደ አሥመራ መለሰ ። በየበኩሉ ቅጥ ባጣ መንገድ እየተዝረከረከ በቁስል እየተሰቃየ ፣ ረኃብና ጥም ፣ እርዛትና ድካም እያንገፈገፈው እየ ወደቀና እየተንገዳገደ ከመንገዝ ላይ ይገኛል ።

ጣልያኖቹ ፣ ለድሉ በፍጹም እርግጠኞች ከመሆን የተነሣ ፣ "ምና ልባት የተሸነፍን እንደሆነ እዚህ ቦታ ተገናኝተን በዚህ መሥመር እየተከታተልን ወደ መጣንበት እንመለሳለን" የሚል ከጠቅላይ አዛዡ የተሰጠ ምንም ዐይነት ፕላን አልነበረም ። የጦርነቱ አመራር ራሱ ከፕላን ውጭ ሆኖ እንደ ተዘባረቀ የሽሽቱ ነገርም ከዚያ የበለጠ ተበ ላሽቶ ብዙ ወታደር በየፊናው ሲሔድ ፣ የኢትዮጵያ ወታደር እየደረሰ በጥይትና በጐራዴ ሲያተራምሰው ባላገር በበኩሉ እየተቀበለ በዱላና በሽመል እየመታ የገደለው ብዙ ነበር ።

ጄኔራል አልቤርቶኒ ፣ በቅድሚያ ሲማረክ ፣ ጄኔራል አሪሞንዲና ዳቦርሚዳ በጦርነቱ ሜዳ ላይ ሞተዋል ። የተጠባባቂው ጦር አዛዥ ጄኔራል ኤሌናና ዋናው ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ባራቲዬሪ ብቻ አም ልጠው ወደ አዲ ቀይህ አመሩ ። እነርሱም በየጦሩ ሜዳ ድል አድራ ጊው ጦር እያዋከበ መምጣቱን ተመልከተው ለጊዜው ባጋጣሚ አጠ ገባቸው ከተገኙት ጋር ተመካከረው የጦርነቱን ፍጻሜ ሳያዩ ፣ "ከመከበ ባችን በፊት እናምልጥ" ብለው ሸሹ ። ጠቅላይ አዛዡ ፣ የጄኔራል አል ቤርቶኒን መማረክ ፣ የሁለቱን ጄኔራሎች ማለትም የዳቦርሚዳንና የአ ሪሞንዲን መሞት አያውቅም ነበር ። የራሳቸው የኢጣልያኖቹ የታሪክ ሰነድ እንደሚያመለክተው ፣ እጦር ግንባር ከቀረበው 17,000 ወታደር ውስጥ ወደ አሥመራና ወደ አዲግራት ሸሽተው ነፍሳቸውን ያዳኑት

258 መኰንኖች ፣ 4666 የነጭ ፣ 4,000 የጥቁር ወታደሮች ናቸው[1] ። በርክሌይ በጠቅላላው የሞተውን የነጩንም ፣ የጥቁሩንም ቁጥር በድምሩ 6133 አድርጎታል[2] ።

ከኢጣልያኖቹ ትራፊ ጦር አጋማሹ አባራሪውን ለመከላከል እንዲመቸው ባንድነት ተሰብስቦ ሲጓዝ የቀረው ተበታትኖ ። ባንድነት ያለውንም ፣ እየተበታተነ ይጓዝ የነበረውንም ፣ አባራሪው ወታደርና ባላገር በጠበንጃም በዱላም እየመታ ብዙ መጨረሱን ባለፈው አንብበናል ። ወታደሩም የካቲት 22 ቀን ለ23 አጥቢያ ሲጓዝ አድሮ የየካቲት 23ትን የውጊያ ቀን የተካፈለ በመሆኑ ፣ ለየካቲት 24 ቀን አጥቢያ ባለው ሌሊት ለመሸሸ ድካም ፣ ረኃብና ውሃ ጥም ስላጠቃው የቆሰለም ስላለበት ፣ የሽሽት ጉዟቸው ለኢጣልያኖቹ የጻዕርና የመከራ ሽሽት ነበር ማለት ነው ። ከጦርነቱ አገማመርና አፈጻጸም የዚህኑ የሽሽት ሁኔታ ከኛ ወገኖች ይልቅ ፣ ከበራሪዎቹ አንዱ የጦር መኰንን የዓድዋ ጦርነት በሆነ በዐሥራ አራተኛው ቀን ከምጥዋ ለናቱ የጻፈላት ደብዳቤ ሁኔታውን በትክክል ያስረዳል ።

### የምስግድልሽና አስደሳቿ የኔ እናት*

ከሁሉ በፊት በእግዚአብሔር ፊት እንስገድ ። ከሞት ተርፌ ሕያው የሆንኩት በተአምራት ነው ። የካቲት 29(22) ቀን ከማታው በ10 (4) ሰዓት ጠመንጃና ጥይት ትንሽ የተፈጨ የቆርቆሮ ሥጋ ብቻ ይዘን የቀረውን ሁሉ ትተን እንድንጓዝ ትእዛዝ ስለመጣ ፣ በሦስት በኩል በሦስት አዝማች ተከፍለን ጉዞ ጀመርን ። እኔ የነበርሁት በዳቦርሚዳ ውስጥ ነበር . . . የተወጠነውም አሳብ በድንገት በጠላት ላይ ደርሰን አደጋ ለመጣል ነበር ። በዚህ ዓይነት ከማታው 10(4) ሰዓት ጀምረን እስኪነጋ 7(1) ሰዓት ድረስ ተጉዘን ስለ ደረስንና ስንደርስም ገና ድሮ ፀሐይ ስለወጣ ፣ በድንገት ደርሶ ጠላትን የማስደንገጡ ነገር ሳተ ። መንገዱ ድንጋይማ ደረቅ ወሃ የሌለበት . . . ስለሆነ ሠራዊቱ እየደከመ ወደቀ ።

በ7 ሰዓት ከ14 (ባንድ ሰዓት ከዐሥራ አራት ደቂቃ) ላይ በቀኝ በኩል ተኩስ ስለ ተሰማ ፣ ጠላታችን ያለበት የመሰለን በግራ በኩል ነበርና ሁላችንም ተደነቅን . . . ቢሆንም በስንት ድካም የአፍሪካ ፀሐይ እያቃጠለን ጉዟችንን ቀጥለን በግራና በቀኝ ተራራ ወዳለው ሥፍራ ደርሰን ወደ ተራራው ለመውጣት ስላልቻልን ፣ በሥሩ ቆመን ሳለ በፊታችን በቀኝ በኩል ግሩም የሆነ አስደናቂ የጥይትና የመድፍ ተኩስ ይሰማን ነበር ። ወዲያው ከፊታችን የአልቤርቶኔ ጦር በሙሉ

---

1 Italia ed Etiopia . . . PP. 447—448.

2 The Campaign of Adwa . . . Chap. XII, PP.335—368.

* በኢጣልያንኛ «Mammina Mia, Adorata, Diletta» ይላል ።



እየሸሸ ሲመጣ ተመለከትነው ። ቀጥሎም በድንገት የኢትዮጵያ ወታደሮች እንደ መጋረጃ ሆነው ከያለበት ፈልቀው በፊታችን ያሉትን ሁለት ተራሮች እየተሽቀዳደሙ ያዙዋቸው ። ቀጥሎም እየፎከሩ እየተጯጯሁ እየተኮሱ በላያችን ላይ የጥይት በረዶ አወረዱብን ። ግማሾቹ ተደብቀው ስለሚተኩሱም ልናያቸውና ልንተኩስባቸው አልቻልንም ። ጥይታቸውም ጭስ የለውም ። ስለዚህ ከነርሱ በሚተኮሰው ጥይት የኛ ወታደሮች እንደ ዝንብ ይረግፉ ጀመር ። ቢሆንም ጣልያኖቹ መልሰው መታኮሳቸውን አልተዉም ።

ከዚህ በኋላ የባታዮው ጦራችን ወደኋላ አፈግፍጎ የጉብታ ሥፍራ ለመያዝ አሰበ ። ነገር ግን በጥይት ተከበን ስለነበረ ፣ በተነቃነቅን ቁጥር የጥይቱ መዓት ስለሚወርድብን ምንም ማድረግ አልተቻለም . . . ይሁን እንጂ ፣ እንደ ምንም ብለን ከወገኖቻችን ተለይተን ወደ ጉብታው ደርሰን ተገን ይዘን ትንሽ እንዳረፍን . . . ወዲያው እነሱም እየተኮሱብን እኛም እየመለስን ስንተኩስባቸው በውጊያ እስከ 4(10) ሰዓት ቆየን ። . . . ከዚያ ሸሽተን ባንድ የሰንበሌጥ ሣር ባለበት ሥፍራ ውስጥ ተደብቀን የሞቱትንና የተረፉትን ወታደሮቻችንን መቁጠር ጀመርን ። ከኔ ጋር በሙሉ ከነበሩት ከመቶ ዐሥራ ሦስቱ ሰባ ብቻ ተርፈው አገኘናቸው ። ከነርሱም ብዙዎቹ ቆስለዋል . . . እኛ ሰባዎቹ ከዋናው የባታዮ ጦራችን ተለይተን ብቻችንን በማናውቀው አገርና ስፍራ አንድ ጠብታ ውሃ በማይገኝበት ተገኝተን እንግዲህ ወዴት እንሒድ? ወይስ ምን እናድርግ?? እያልን እንመካከር ጀመርን ። አለንበትም ስፍራ አጠገብ አንድ ከፍተኛ የቆሰለ ማዦርና 6 በቅሎዎች አገኘን ። ከዚያ እኛ ሹማምንቱ እርስ በርሳችን ምክር ካደረግን በኋላ ፣ ወደ ምሥራቅ እንጓዝና ሰፈራችንን እናገኝ ብለን ውሳኔ አደረግንና ቁስለኞቻችንን በበቅሎ ጭነን ጉዞ እንደ ጀመርን በቅሎዎቹ አልራመድ ስላሉ ከኋላ እየደበደብን በመንዳት ጉዟችንን ቀጠልን . . . የቀሩት ቁስለኞች እያቃሰቱ ውዐ ውሀ እያሉ በኋላ ይከተሉን ነበር ። በድንገት ከኋላችን የጥይት ድምፅ ተከትሎን ስለተሰማ ቁስለኞቹ መራመዳቸውን ትተው እመሬት ላይ ተዘርረው ተኙ ። ተነሡ ብለን ብንቆጣም ፣ ብናባብልም አልሆነም . . . በዚህ ሰዓት እከፉ ሁኔታ ላይ መሆናችን ስለ ተሰማን እኔና ካፒቴኑ በየሽጉጣችን ለመግደል ተፈቃቀድን ። ነገር ግን ይህ አሳብ ወዲያው ከላያችን ተወገደና በብዙ ጭቅጭቅ የተኙትን ቁስለኞች አስነሣንና በዚያ በሾህማና ጠጠርማ መንገድ ከኋላችን ተኩስ እየተከተለን ስንጓዝ ድንገተኛ ያልታሰበ ጥቁር ደመና በሰማይ ላይ ታየና ዝናም መዝነብ ጀመረ ። ዝናሙን አጠራቅመን የምንጠጣበት መግሪያ ስለሌለን፣ በዝናም የራሰውን ልብሳችንን እየመጠጥን ተጓዝን ። ሲመሽ ከማታው በ10(4) ሰዓት አንድ የለመለመ ስፍራ አግኝተን በዚያ ሰፍረን አደርን ። በዚያም ባደርንበት ጊዜ ጠላቶቻችን ጥይት እየተኮሱ ሁለት ወታደር ሁለት በቅሎ ገድለው ሦስቱን ወታደሮች አቆሰሉብን ። ከሌተናዎቹ (ከመቶ አለቆቹ) አንዱ ከቁስለኛው ማዦርና ከዐሥር ወታደር ጋር ወደኋላ ደከመው ቀሩ . . . መረብ ወንዝ ደርሰን ዕረፍት አደረግንና . . . እንደገና ከሌሊት በ10(4) ሰዓት ተነሥተን . . . በመንገድም አንዳንድ ጊዜ መዋጋት ነበረብን ። ከኛ ጋር ካሉት ግማሹ ልብሱ አልቆ በውስጥ ሹራብ የሚሔድ ጫማው አልቆ በሸሚዝ ቁራጭ ወይም በሻሽ ጫማውን አስሮ ይሔዳል ። አንዳንዱም ደክሞት አልሔድ

ሲል እንዲራመድ በዱላ ስንደበድበው ወደኋላ ተሰይቶ እንዳይቀርም
ባላገር እንደሚገድለው ስለሚያውቅ የግዱን መራመድ ይጀምራል ።
እኛ ሹማምንቱ ወታደሮቻችን በግድ እንዲራመዱ ለመደብደብ
ጭካኔ አስፈልጎን ነበር ። . . . እንደዚሁ ባንድ ቦታ ውለን ስንጓዝ
ከጫካ ውስጥ ተተኩሶ አንድ ጓደኛችን ተመታ ። ሊድን የማይችል
መሆኑንም ስናውቅ ትንሽ ውሃ አጠገቡ ትተንለት ጥለነው ሔድን ።
ባንድ ስፍራ ስንደርስ በፊት ለፊት እሳት በብዙ የሚነድ አየን ።
የጠላት ሰፈር መሆኑንም የሚመራን ያገር ተወላጅ ስለ ተናገረ እጉብታ
ላይ ወጥተን መሣሪያችንን ጠምደን ተኛን ። ከዚያም በማግሥቱ የኛ
ዎቹ ወዳንድ መንደር ገብተው ስንቅ ሲፈልጉ ከባላገሩ ጋር ተዋጉና
ሦስቱ ሞቱ ። እኛም በሩቅ እየተኮስን ባላገሮቹን ብዙ እየገደልን አባ
ረርን ። ቢሆንም እንደገና ጉዞ ጀምረን የምንጓዝበት ሜዳ ውሃ የሌለ
በት ስለሆነ ውሀ ጥም እንደገና ያሰቃየን ጀመር ። ወታደሩም እየተኛ
ሰላስቸገረን ተነሡና ተራመዱ ለማለት የኔም የራሴ ምላሴም ጉሮሮ
ዬም በውሃ ጥም ተዘጋና መናገርም እቃተኝ ።

የሆነ ሆኖ ፣ ውሃ እፊታችን እቅርብ አለ እያልን እያባበልን እስነ
ሥተን ሁሉም እያቃሰተና እያላዘነ ይጓዝ ጀመር ። ሲነጋ መጋቢት
5 ቀን (የካቲት 27 ቀን) አንድ የረጋ ውሃ አየንና እኔና ካፒቴን
ተሯሩጠን ተዘርግተን በብዙ ጠጣን ። ከጠጣንም በኋላ ከውሃው ጋር
የግመል ሽንት እንዳለበት ተረዳን ። ነገር ግን መቶ ሜትር እልፍ
ስንል ሌላ መልካም ውሃ ተገኘና ሁሉም እንደልቡ ይጠጣ ጀመር. .
በማግሥቱ ከሌሊት በ4(10) ሰዓት ጉዞው ቀጠለ ። የውሃ ጥም አሰቃ
የን ። በምናልፍበት መንገድ ለምለም ሣር ስለነበረ ከርሱ እየነጨን
እያኘክን እንደ እንስሳ ጉምጅተን ውሀውን እንመጥ ነበር ። . . .በመ
ጨረሻ አንድ ውሀ የተጠራቀመበትን ስፍራ ሲነጋ ስላየን ሰውም
ከብቱም ወደዚያ እየተሯሯጠ ሔዶ ጠጣ . . . ሔደን ሔደን ባንድ ሜዳ
ላይ ስንደርስ የኢጣልያኖች ሬሣ እተረፈረፈበት ደርሰን ሁሉም ራቁ
ቱን የሆነ ግማሹ ሰውነቱን የተቆራረጠ ነበረበት ። ስንደርስ አንዱ
ከፉኛ ቆስሎ አልሞተ ኑሮ ተነሥቶ የጦርነቱን ሁኔታ ትንሽ አነጋግ
ረን . . . የነዚህን የዝግኖቻችንን ሬሣ ለአሞራና ለጅብ ትተን በሐዘን
አልፈናቸው ሔድን ። ሌሎች ያልሞቱ ሁለት ጣልያኖች ራቁታቸውን
ተነሥተው እየሮጡ ተከተሉን ። ከሁለት አንዳቸው በጣም ለሞት የቀ
ረበ መሆኑን ስለተረዳን ከውሃ አጠገብ ጥለነው ሔድን ። አንደኛው
ግን ጉዞውን ከኛ ጋር ቀጠለ . . . የኛ ሰፈር ወደ ነበረበት አቅራቢያ
ስንደርስ ደስ ብሎን ነበር ። ዳሩ ግን ዐሥር ቁስለኛ ያስከተለ አንድ
የ50 አለቃ (ሰርጀንት) አገኘንና ሰፈራችን ሁሉ በጠላት መያዙን ገለጸ
ልን ። የጦር ሠራዊታችን ሁሉ ወዴት ሔደ ብለን ብንጠይቀውም
"የፈረሰ ይመስለኛል" ብሎ ወዴት እንደሚገኝ አለማወቁን ስለነገረን
እኛ ሹማምንቱ እርስ በርሳችን እየተያየን የጦራችንን መፍረስ ተገነ
ዘብን ።

ከዚህ በኋላ ምን ይሻላል በፊታችንም በኋላችንም አበሾች አሉ ።
ስድሳ የምንሆነው የደከምነው ሰዎች ከዚሁ ሐያ ቁስለኛ ስምንቱ
የጸናባቸው ሆነን ወዴት እንሔዳለን እየተባባልን ስንከራከር ቆይተን
ወደ ሰሜን 300 ኪሎ ሜትር እንደገና ተጉዘን አሥመራ ከመድረስ
በቀር ሌላ የደኅንነት መንገድ አለመኖሩን ብንረዳውም ይኸንንስ



ሰደከመ ጉልበት ያለስንቅ በጠላት አገር በተናደደና በሚዋጋን ባላ
ገር መካከል አልፈን እንደምን እንደርሳለን ከተባባልን በኋላ በርቱ
ተበረታቱ ልጆች ተባብለን ጉዞውን ጀመርን ። ስንጓዝ ውለን በ6(12)
ሰዓት አሁንም ጉዟችንን ስንቀጥል ከወደፊታችን ሰዎች ሲመጡ አየ
ንና ጠላቶቻችን መስለውን ለተኩስ ተሰናዳን ። በዚያ ጊዜ አንድ
ወታደር "የጦር መኰንን ነው" ብሎ (በኢጣልያ ቋንቋ) ስለጮኸ
መተኮሳችንን ትተን ብንመለከት ፣ በውነትም የጠፉትን ወታደሮች
ለመፈለግ ሲል ባላገርና ወታደር አስከትሎ የሚመጣ የአሜሊዮ ባታዮ
የጦር መኰንን መሆኑን ተገንዝበን ተያይተን ስንገናኝ እርስ በርሳችን
እንሳቀስ ጀመር ። ከዚያ እነሱን አግኝተን በነርሱ እየተመራን የደከ
ምን የቆሰልን ብንሆንም ፣ እንዳማረብን ብረታችንን በትከሻችን እንደ
ያዝን ከ6 ቀን ጉዞ በኋላ ቁስለኞቻችንን ሳንተው (አሥመራ) ደረስንና
ቅልጥማችን እየተንቀጠቀጠ በዚያ ለነበረው ለማዥር አሜሊዮ የብ
ረት ሰላምታ አቀረብንለት ። በዚያ ያሉት ነጮችም ጥቁሮችም እየተደ
ነቁ እያዩን ሹማምንቱም በላያችን በናፍቆት እየወደቁ ሳሙን ። ከዚያ
ደንበኛ ዕረፍት አደረግን ። እንደ ሕልምና ተረት የመሰለንን የኛንም
መብል (ሚኒስትሮኒ) አቀረቡልን . . .

ሲል የጦር መኰንኑ የሸሸቱን ሁኔታ በዚህ ዓይነት ዘርዝሮ ይደመድ
ማል[1] ።

ድንገተኛ አደጋ በመጣል የኢትዮጵያን ነጻነት ደምስሰው አገሪ
ቱን ለመውረር ፣ እንዲሁም በአላጌና በመቀሌ የደረሰባቸውን የወታደ
ርነት ውርደት ለማደስና የኢጣልያን መንግሥትና ሕዝብ መንፈስ
በኩራት እንመላዋለን ብለው የመጡት ፣ የኢጣልያ የጦር መኰንኖችና
ወታደሮች እነሆ እጦርነቱ ላይ የሞቱት የአሞራና የጅብ ራት ሲሆኑ፣
ጥቂቶቹ በኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ተማረኩ ። የቀሩት ደግሞ ተዝ
ረከርከው ወደ መጡበት ተመለሱ ። ይህ ሁሉ ከመድረሱ በፊት ዐፄ
ምኒልክና የወንድም አገልጋያቸው ራስ መኰንን እርቅ ሆኖ በሰላም
እንዲመለሱ ምን ያህል ጣልያኖቹን እንደ ለመኑዋቸው ከዋናው
ከዓድዋ ጦርነት በፊት ባሉት ምዕራፎች በሰፊው ተገልጿል ።

እውነት ነው ፣ ጠላትን በማናቸውም ረገድ ለማጥቃት ሲሞከር
ሞራል ፣ ይሉኝታና ሐቀኝነት እንዳይገባበት ኒኮላ ማኪያቬሊ የሚባ
ለው የነርሱው ተወላጅ በፍልስፍና መንገድ አስተምሯል ። ሐቀኝነት
የማይወዱ የመንግሥታት መሪዎችም ሠርተውበታል ። ዐፄ ምኒልክም
የባራቲዬሪን ጦር ከምሽግ እንዲወጣ ያደረጉት በተንኮል መሆኑን አን
ዘነጋም ። ቢሆንም ሌሎቹ ለከዳታቸው ወይም ለተንኮላቸው ይሉኝታ

1 Lettere e Diari . . . PP. 92-99.

ሲበርዙበት ፣ ኢጣልያኖቹ ግን በፍጹም ተንኮል ይሠሩበት ነበር ። ነገር ግን በተንኮልም ፣ በማታለልም ፣ በጦርነትም ቢመጡ ዐፄ ምኒልክና መኳንንቶቻቸው ተንኮሉን በተንኮል ፣ ጦርነቱን በጦርነት መልሰው ይኸን ትውልድን ለዘለዓለም የሚያኮራ ድል ሊያቀዳጁ ቻሉ ። በዚህ ድል አድራጊነት ያገሪቱንም ነጻነት ከሚያኮራው የድል ክብር ጋር ለኛ ለዛሬው ትውልድ አስተላለፉልን ። ለአባቶቻችን ኀብረትና ዠግንነት ከፍ ያለ አድናቆትና ምስጋና መስጠት ይገባናል ። ይህ ከዚህ በላይ ያየነው ከዳቦርሚዳ የጦር ግንባር የሸሸውን የጦሩን ሁኔታ ነው ።የሁሉም ይነስ ይብዛ ይኸው ነው ። አንዳንዶቹ ግን ፣ ቀደም አድርገው ከጦርነቱ ቦታ ሸሽት የዠመሩት ባገር ተወላጅ ወታደርና ባንዳ እየተመሩ በተሻለ ሁኔታ ሸሽተው ወደ ሰፈር ደርሰዋል ። ግማሾቹ ደግሞ በተለይ ያገር ተወላጅ ወታደርና አንዳንድ የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ድሉ እንደሳተ ቤተሰቦቻቸውና ሚስቶቻቸው ስንቅና ልብስ እየያዙ መጥተው ከመንገድ እያገኙ የወሰዱዋቸው አሉ ።

በግራ በኩል በዤኔራል አልቤርቶኒ ውስጥ የባንዳ ጦር ይዞ የተዋጋው ቲኔንቲ አሌሳንድሮ ሳፔሊ የሚባለው ከሞትም ፣ ከምርኮም ተርፎ አገሩ ከገባ በኋላ በጻፈው ማስታወሻው ላይ ስለዚሁ መልስ ጉዞ እንደዚህ ይላል ።

...በጧት ከንቲባይ አብተ ማርያምን ይዤ በረዓዮ ውስጥ አዲ ፈቂ ከሚባለው በር ደረስሁ...የማዥር ቁሪቶ ጦር ሲዋጋ የጥይቱ ድምፅ ይሰማን ነበር...ከዚያ የኛ ወታደር እየሸሸ ሲመጣ አየነው... የንጉሡ ነጋሪት ያለማቋረጥ ሲጐሸምና ሲያጓራ ይሰማን ነበር ። ባጠገቤ ያሉትም ሹማምንት የንጉሡ ነገሥቱን ዠንጥላ ሰይተው ያውና እያሉ ያረጋግጡ ነበር ። የኛዎቹ ምንም ቢከላከሉ የሸዋው ጦር እየተ ኸጕደጕደ መጣ ። ከዚያ ሁሉም ይሸሽ ጀመር...ከዚያ ሮጨ ሌላውን የባንዳ ጦር ወደሚያዘምተው ወደ ቲኔንቲ ሉካ ዘንድ ስሔድ እርሱና ጦሩ በሚዋጉበት ጊዜ ፊታውራሪ ተድላ ሞቶ ወንድምየው ባላምባራስ ምኒልክ ቆሰለ...* ከዚያ ግራና ቀኝ እንደ ተከበብን 'ተማረክ ተማረክ' የሚለውን ቃል በሚያጓራው የመድፍና የጠመንጃ ድምፅ መካከል እያዳመጥን ሽሽት ያዝን ። አንዳንድ ጊዜ የሚሸሸውን እንደ ምንም አቁመን ስንከላከል ፣ የሚያዋክቡን የጋላ ፈረሰኞች ጋብ ይሉ ነበር ። እነርሱም ከረዓዮ እስከ እንኪሎ 'እንትጮ' ድረስ እያባረሩ ያዋክቡን ነበር...

አንዳንድ ጊዜ እየተናደድሁ የሚሸሸውን አቁሜ ለማዋጋት እስከ መማታት ስደርስ ፣ በባንዳው ወታደርና በሕዝቡ ዘንድ ከበሬታ ያለው ደጃች ፈንታ 'በከንቱ አትድከም በራሪውን የሕንፃ ግድግዳ እንኳን አያቆመውም ፤ ድሮውኑ በሰንበት መዋጋት አልነበረብንም'

* የባንዳ አለቆች ።



አለኝ...* ከዚያ ሸሽተን ሊነጋ ሲል በሰሳ ወንዝ እኩለ ቀን ሲሆን አዲ ሺአዲ ደረስን ። በዚያም የቀድሞ ወዳጄን የገበእቲ ጓንጉልን ወዳጆች አገኘሁ ። ለተረፉትና ከኔ ጋር ላሉት ወታደሮቼም እህል አገኘሁ ። ውሃ ግን በዚያ አቅራቢያ ስለጠፋ ወደ ቆሐቲት አመራሁ ። እዚያም ሳለሁ የተረፉ ባንዶች አግኝቼ ያለቃቸውን የቲኔንቲ ሉካን መሞት የዠኔራል ባራቲዬሪን ወደ አዲ ቀይህ መጓዝ ሰማሁ... ሁለት ሌሊት እንቅልፍ በማጣት በቀኑ ሽብር ሰውነታችን ደክሞ ዝሎ ሳለ ፣ ሰውነቱን ለማንቃት የሸንኩርት ቁራጭ ሁልጊዜ የሚያኘከው ይኸው ደጃች ፈንታ እንዳርፍ መከሮኝ ሳርፍ ሰል ፣ አንዲት ሴት በፈረስ ሆና አንድ ወታደርና ሁለት ገረዶች አስከትላ ወደኛ ስትመጣ አየሁ ። ለካስ የኔው ሴት የሆነችው ወይዘሮ አምለሱ የጦሩን መፍረስ ወሬ ሰምታ ሞቼ እንደሆነ ለመቅበር ፣ ተማርኬም እንደሆነ ለማጽናናትና ለመርዳት መጥታ ኖሯል ። ገረዶቿ የቆርቆር (ቧት) መብል መድኃኒት ሻሽ እርሷ ደግሞ በፈረሷ ኮርቻ ውስጥ እቤት የነበረ 200 ብር (ማሪያ ትሬዛ) ደብቃ ይዛ ኖሯል ። በዚህ ሰዓት የነበረኝን የግንኙነትና (ከርሷ ስንገናኝ) የስሜቴን መንቀሳቀስ አድናቆቴንና ባለውለታነቷን ልዘረዝረው አልፈልግሁም ። ሌሎች ደግሞ ሴቶች ባሎቻቸውን ለመርዳት የመጡ ነበሩ ። ብዙዎቹ ግን እንደ አምለሱ አልታደሉም ።...1 ይኸውም ሞተዋል ማለቱ ነው ።

*ደጃች ፈንታ በራስ አሉላ ውስጥ የታወቁ የጦር አለቃ ነበሩ ። የመተማንም ጦርነት ተካፍለዋል ። በኋላ ከኢጣልያኖች ጋር ግንኙነት አድርገሃል ተብለው ታስረው ሳለ ከዚያ አምልጠው ወደ ደጃች ደብብ ሔዱ ። ደብብ ከራስ አሉላ ጋር ተዋግተው ስለሞቱ ከራስ አሉላ ምሕረት አግኝተው ኀብተውላቸው የዓድዋ ጉምሩክ ሹም ሆኑ ። በኮዓቲትም በራስ መንገሻ ውስጥ ሆነው ከኢጣልያኖች ጋር ተዋግተዋል ። በኋላ ግን ኢጣልያኖቹ አሸናፊ ስለሆኑ ፣ ለነርሱ ታማኝ በመሆን የዓድዋን ጦርነት ከሳፔሊ ጋር ሆነው ተካፍለዋል ማለት ነው ።

1 Memorie d'Africa (1883-1906). A. Sapelli, PP.115-121.

# ምዕራፍ ዐርባ ስድስት

**ሴተና ዤኔራል አንቶኒዎ ባልዲሠራ አዲስ ጦር ይዞ ምጥዋ እንደገባ— ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ስለ ዕርቅ ጉዳይ ወደ ምኒልክ እንደመጣ —ሴተና ሮቬርስ ባይኑ የተመለከተው የኢትዮጵያ ሠፈር—የዕርቁ ለጊዜው አለመሳካት**

ከንጉሡ ጀምሮ እስከ መሳፍንቱ ፥ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ እስከ ተራው ሠራተኛ ፥ ከመከላከያ ሚኒስትሩ አንሥቶ እስከ ተራው ወታደር ድረስ የነበሩት ኢጣልያኖች ፥ ኢትዮጵያ በዚህ በምኒልክ አገዛዝ ወቅት የነበራትን ጠንካራ የውስጥ ሁኔታ ባለማወቅ ወይም ዐውቆ በመናቅ በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸው የመስፋፋት ምኞት ከፍ ያለ እንደነበር ተመልክተናል ። ዐፄ ምኒልክም ያን ያህል የሰላምና የእርቅ ነገር ደግመው ፥ ደጋግመው የፈተኑት ምንም የተደራጀ ጦር እንዳላቸው ቢያውቁም ፥ "እንሸነፍ ይሆን፤ በብዙ ድካም የተገነባው መንግሥታችን ፥ ብሔራዊ ግዛታችን መልሶ ይፈርስና ውርደት ያስከትልብን ይሆን" በሚል ሥጋት ውስጥ እንደነበሩ አይጠረጠርም ። ብዙ ጊዜ እንዳልነው ፥ ራስ መኰንን ኢጣልያን የጐበኙ ጊዜ የመንግሥቱ መሪዎች ሆነ ብለው የወታደርና የመሣሪያ ድርጅታቸውን በጥንቃቄና በዝርዝር አሳይተው መልሰዋቸዋል ። ይህም ለጦርነቱ ሠግተው ንጉሡንም እንደሚያሠጉ በማመን ያደረጉት ይመስላል ። ጦርነቱ የተካሔደው በአንድ በኩል ለድል አድራጊነቱ ባልተጠራጠረ ፥ አሸናፊነቱን በተማመነ ፥ ራሱን ከፍ አድርጎ በኩራትና በትዕቢት ተወጥሮ የቅኝ ግዛት አምሮት ባሰከረውና በሌላው ወገን ራሱን በትሕትና ዝቅ አድርጎ ለድል አድራጊነቱ በሥጋና በግድ የእናት አገሩን ነጻነት ለመከላከል ብቻ ለውጊያ በቆረጠ ሕዝብ መካከል ነው ። ዳግማዊ ምኒልክ ፥ በኩራትና በትምክህት ተመልቶ እስከ አላጌ ድረስ በግሥጋሤ የመጣውን ኃይለኛ የጠላት ጦር ፥ በሰላም እምቢ ያለውን በውጊያ እየጠረጉ እስከ ዓድዋ ዘልቀው በሰፈሩበት ሰዓት ፥ የኢጣልያ መንግሥት በባራቲዬሪ አማካይነት ፥ ዝናን ፥ የወታደር ክብርን የሚያድስ ፥ ሰፋ ያለ ግዛት የሚያወርስ ድል በጕጉት ተጠብቆ ድሉ የውሻ ሽታ ሆኖ ቀረ ። ከዓድዋ ጦርነት ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ በሮማ ምክር ቤት በጥንቃቄ ምክር ተደርጎ በኢጣልያ የጦር ሠራዊት ውስጥ

ከፍተኛ ዝና የነበረው ከጀኔራል ባራቲዬሪ በደረጃም በችሎታም የሚበልጠው ሌተና ጀኔራል አንቶኒዮ ባልዲሠራ በኤርትራ ጠቅ ላይ አዛዥ ተብሎ ተሾመ ። ይኸ ሰው ከዚህ በፊት ኢጣሊያ እ.ኤ.አ. ከ1888 ዓ.ም. ሰሜን ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር በነበረ ጊዜ ባራቲሪዬ በርሱ ውስጥ ኰሎኔል ነበረ ።

ባልዲሠራ ሲመጣ ፣ ደልማይና እና ሔሽ የሚባሉ ሁለት ሌተና ጀኔራሎች ፣ ቤዚስቲ ፣ ባርቤዬሪ ፣ ጋዜሬሊና ግዛ የሚባሉ አራት ማዦር ጀኔራሎች በውስጡ ሆነው ብዙ ጦር ይዘው እንዲዘምቱ ተወስኗል ። ጀኔራል አንቶኒዮ ባልዲሠራ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቀበለው ትእዛዝ አሥመራ እንደ ደረሰ ፣ አዲስ ይዟቸው የሚሔደውን ከጀኔራል ሔሽ ጦር ጋር ቁጥራቸው ወደ ዐሥራ አምስት ሺ የሚደርሰውን ወታደሮች ኤርትራ ካሉት ሐያ ሺ ወታደሮች ጋር ደባልቆ ጠቅላላውን ቁጥሩን ሠላሳ አምስት ሺ የሚደርሰውን ሠራዊት ከሁለት ላይ ከከፈለ በኋላ ፣ አንዱን ክፍል ለሌተና ጀኔራል ሔሽ ሰጥቶ እርሱ የሁሉም የበላይ ሆኖ በማጥ ጋት ያኔ ምኒልክን ኃይል አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ሰባብሮ ኢትዮጵያን የመውረሩን ጉዳይ በቶሎ ወደ ፍጻሜ እንዲያደርስ ነው ። ባራቲዬሪ እስካሁን ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ አሁን በዚህ ዐይነት አልሠራም ያለ እንደሆነ ወደ ሮማ እንዲመለስ ነበር ።

ጉዳዩም ጀኔራል ባልዲሠራ ፣ አሥመራ ደርሶ ሥራ እስኪገል ጸው ድረስ በጥብቅ ምሥጢር እንዲያዝና ጀኔራል ባራቲዬሪም እንዳ ይሰማ ጥንቃቄ ተወስዶአል ። በጋዜጦችና በደብዳቤዎች ላይ በኢጣል ያም በኤርትራም ፖስታ ቤቶች ጥብቅ ቁጥጥር ተደርጓል ። አንዳንድ ጸሐፊዎች ባራቲዬሪ ምስጢሩን ከአንዱ ወዳጁ ተጽፎለት ስለተረዳው ባልዲሠራ ከመድረሱ በፊት ጦርነቱን ዠምሮ ተሸነፈ ይላሉ ። የሆነ ሆኖ ፣ በግናቸውም ረገድ በዚህ ዐይነት ከፍተኛ ድርጅት ባልዲሠራ ከኢጣልያ ተነሥቶ ወደ ምጥዋ በመርከብ በሚጓዝበት ጊዜ ባራቲዬሪ ጦርነቱን ጀምሮ ባለፈው ባነበብነው ዐይነት ተሸንፎአል ። በሽሽት ወደ አዲ ቀይህ ደርሶ የመሸነፉን ቴሌግራም ከአዲ ቀይህ ወደ ሮማ መጋቢት 3 ቀን እ.ኤ.አ. አስተላልፎ በማግሥቱ ወደ አሥመራ ለመሔድ ከአዲ ቀይህ ወደ ሰገነይቲ በሚጓዝበት በመጋቢት 4 ቀን በበኩሉ በለፈ ፕላን ተዘጋጅቶ የመጣው ባልዲሠራ ነገሩን ሁሉ ሳያ ውቅ በዚሁ በመጋቢት 4 ቀን ምጥዋ ከገባ በኋላ የኢጣልያን ጦር የመሸነፉን መርዶ ሰማ ። በሐዘንም ወደ አሥመራ ተጓዘ ። የሚወደ ውንና የሾመውን የቀኙን ወገን የክሪስፒን መውደቅና የማይወደውን የግራውን ክፍል የዲሩ ዲኒን መሾም አሥመራ ሰምቶ አዲስ ትእዛዝ ይጠባበቅ ጀመር ። ከዓድዋ ድል በኋላ 'ምኒልክ የማይሸነፍ ነው' የሚል እምነት በኢጣልያ አገር በባለሥልጣኖች ላይ ስላደረ ፣ በፊት



እምቢ ያሉትን ዕርቅ አሁን በግድ ጠይቀው እንዲቀበሉ ሁኔታው አስገደዳቸው ። ስለዚህ ጀኔራል ባልዲሠራ የዓድዋ ጦርነት በሆነ በአራተኛው ቀን ምጥዋ ሲደርስ ካላሰበው ሁኔታ ላይ ወደቀ ። ከም ጥዋ ወደ አሥመራ የመጣ ጊዜ የኢጣልያ ጦር ዓድዋ ላይ ተሸንፎ ግማሹ በሞትና በምርኮ መፍረሱን ፣ ከምርኮና ከሞት የተረፈው በብዙ ሥቃይና መከራ ፊቱን ወደ አሥመራ አድርጎ መሸሹን ፣ አዲግራት ያለው አንድ ክፍል ጦር በነራስ መንገሻና በነራስ ስብሐት ጦር ተከበ ብዙ የኢጣልያ ወታደሮች ተማርከው በዋናው የኢትዮጵያ ጦር እጅ እንዳሉና በርከት ያሉት ደግሞ በየቀበሌው በትግሬ ሹማምንት እጅ በምርኮኝነት መኖራቸውን ሰማ ። በተለይ ደግሞ ፣ "ዋናው ጦር ከኋላ ከእንትጮ ተጉዞ መረብን አልፎ ኤርትራን ለመውረር ይዘጋጃል ። ግንባር ቀደምና አሳሽ ሆነው እነራስ ስብሐት ፣ እነደጃች ሐጐስ በመ ረት ግይ ወደ ደንጉሎ ፣ እነደጃች አርአያ ወደ ዳዓር ተከሌ ያመራሉ" የሚለው ወሬ ባልዲሠራን ከትልቅ ሥጋት ላይ ጣለው ። ባፄ ምኒልክ ዘንድ ያለው የስንቅ ማለቅ ወይም ያለማለቅ ሁኔታ ፣ ራሶቹ ፣ ወታደ ሮቹ ከየአውራጃ ከወጡ ሰባት ወር ያህል ስለሆነ ፣ ወደየአገራቸው ለመመለስ ያላቸው ናፍቆትም ምን ያህል እንደሆነ በትክክል ሊገነዘበው አልቻለም ። ዐፄ ምኒልክ በርሱ በኩል ያለውን ችግር እንደማ ያውቁ እርሱም በርሳቸው በኩል ያለውን በግልጽ አያውቅም ነበር ። ይኸን የመሰለው አለመተዋወቅ ፣ ሁለቱም ከትምክህትና ከኩራት ርቀው የሰላምን መንገድ እንዲፈልጉ አስገድዷቸዋል ።

ጀኔራል ባልዲሠራ ፣ ይኸን በመሰለ አሥጊ ሁኔታ ላይ ባለበት ሰዓት በበኩሉ አዲስ ከተሾመው ጠቅላይ ሚኒስትር ከዲሩዲኒ ጋር በቴሌግራም እየተስማማ ፤

፩ኛ ከያለበት እየሸሸ ወደ ኤርትራ የሚመለሰውን የደካከመና የተሸበረ ጦር እየተቀበለ በማጽናናትና ልብ በመስጠት አዲስ ከመጣው ጦር ጋር ደባልቆ ማናቸውንም ነገር ማደራ ጀት ፣

፪ኛ ንጉሠ ነገሥቱ ጦር ይዘው መረብን ተሻግረው ኤርትራን ለመውረር ምናልባት የመጡ እንደሆነ እንደ ተቻለ መከ ላከል ፣

፫ኛ/ በዓድዋ አካባቢ በዩሃ ፣ በማርያም ሸዊቶና በእንዳ አባ ገሪማ የወደቀውን የኢጣልያኖች ሬሳ ሰብስቦ ለመቅበር በማስፈቀድ ሰበብ ፣ የሰላም ንግግር በመጀመር ንጉሠ ነገ ሥቱ መረብን እንዳይሻገሩ ማቆየት ፣

፭ኛ የኢጣልያ ጦር በዓድዋ ሲፈርስ በአዲግራት ምሽግ እንደ ተከበቡ የተቀመጡትን ጣሊያኖች በስምምነት ማስለቀቅ፣

፮ኛ በከሰላ በኩልም ኢጣልያኖች በደርቡሾች ተከበዋል የሚሉ ወሬ ስለተሰማ ለነርሱም እርዳታ መላክ ።

ስለዚህ ፣ በሌሎቹ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች በትጋት ከማከናወን ጋር በ፭ኛና በ፮ኛ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች ለመፈጸም ፣ ከጦርነቱ በፊት ወዳጄ ምኒልክ ዘንድ በመላክ የታወቀው ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ተመረጠ ። ለርሱም ረዳት የሚሆነው የኢትዮጵያውያንን ባህልና የትግርኛ ቋንቋ የሚያውቀው የአዲኳላ ምስለኔ ቴኔንቲ ሮቬርሲ ተጨመረለት ። ከነዚህም ጋር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ባስተርጓሚነት በኢጣልያኖች ዘንድ የታወቁት ፣ ደጃች ባሕታ ከኢጣልያ ሸፍተው የሰገነይቲውን ምስለኔ ቲኔንቴ ሳንጉይኔቲን ያሰሩ ጊዜ ስለ ኢጣልያዊው መኰንን እስራትና መጉላላት ከባሕታ ሐጎስ ጋር የተጣሉትና በዚህም ሥራቸው ሁሉ በኢጣልያኖች ዘንድ በጣም የተወደዱት አቶ ገብረ እግዚአብሔር ተሰጡት ።

በዚህ ዐይነት ማዦር ሳልሳ እነዚህን እንዳስከተለ በሐያ ሰው ታጅቦ ከአሥመራ ወደ አዲኳላ መጣ ። ከጄኔራል ባልዲሠራ እንደ ታዘዘው የአዲኳላ ምስለኔ ስለ ሰላም እንዲዋዋል የኢጣልያ መንግሥት ማዦር ቶማሶ ሳልሳን መሾሙን ዐፄ ምኒልክ ዐውቀው እንዲቀበሉት ለራስ መኰንን ደብዳቤ በመላክተኛ እጅ በቶሎ ላከ ። አዲኳላ ሆነው ሌቱንም ምንም እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ሲጠብቁ አድረው መልሱ ስላልመጣ ፣ መቼም መፈቀዱ አይቀርም ብለው ጉዟቸውን ወደፊት ቀጥለው በየካቲት 27 ቀን (መጋቢት 6 ቀን) ጉንደትን አለፍ እንዳሉ ከራስ መኰንን ዘንድ ከተላኩት መላክተኞች ጋር በመንገድ ተገናኙና ከራስ መኰንን የተጻፈውን ደብዳቤ ለሳልሳ ሰጡት ። በደብዳቤው ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ሳልሳን ለመቀበል መፍቀዳቸው ፣ እነርሱንም እየመሩ የሚወስዱ ሁለት መኳንንት ታዘው መንገድ መጀመራቸው ተገለጸለት ።

በዚህ ዐይነት ተጉዘው አዲ ቀሆት ሲደርሱ ፣ ከሁለቱ መኳንንት ጋር ተገናኙ ። እነርሱም ፊታውራሪ ደሳለኝ የራስ መኰንን መላክተኛ፣ ደጃች አርአያ የራስ መንገሻ ዮሐንስ መላክተኛ ናቸው ። ከእነርሱም ጋር በመልካም መግባባትና ሰላምታ ከተገናኙ በኋላ ፣ አዲቀሆት የደጃች አርአያ ግዛት ስለሆነ ፣ በመልካም መስተንግዶ አድረው በማግሥቱ ከመጋቢት 11 እ.ኤ.አ. ዠምሮ ተጉዘው ዐፄ ምኒልክ ሰፈር እስኪደርሱ ድረስ ያዩትን ሁኔታ በቀጥታ ከራሱ ከቲኔንቴ ሮቬርሲ ጽሑፍ መመልከት የተሻለ ነው ።



. . . ከአዲ ቀሆት በማግሥቱ ተነሥተን 2 ሰዓት እንደ ተጓዝን ዐፄ ምኒልክ ያሉበትን እኛም መኳንንቱም አናውቅም ነበርና አስተዋዩ ፊታውራሪ ደሳለኝ በያዘው መነጽር አተኩሮ ሲያይ እንደ ደመና የቀመ አቧራ ተመለከተና ወደ ፈረስ ማይ የሚጓዘው የሸዋ ጦር (ያፄ ምኒልክ) ነው ብሎ ነገረን ። ወደዚያም ለመድረስ የዩሃን ሜዳ ማቋረጥ ነበረብን ። በዚሁ ሜዳ በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የሞቱት ያብዛኞች ጣልያኖች ሬሳ ፊታቸውን ወደ አንዲት ፈሳሽ ወንዝ አድርገው እንደወደቁ ይታዩ ነበር ። ሜዳው በሙሉ በሬሳ ተሸፍኖ ነበር ። በአፍሪካ 6 ዓመት ስኖር ብዙ ቁስለኛና ሬሳ አይቻለሁ ፣ የአቀርዳትንም የጦር ሜዳ ተመልክቻለሁ ። ነገር ግን በዚህ ቀን በዩሃ ሜዳ እንዳየሁት የመሰለ የሬሳ ብዛት በፍጹም አይቼ አላውቅም ። ጦርነቱ በተደረገ በ8ኛው ቀን በመካከሉ ሳልፍ ሬሳውን አሸናፊዎቹ ሳይገፉት ጅብም ሳይነካው እንዳለ ነበር . . . ሬሳው አንዱ ካንዱ የተቀራረበ በመሆኑ በቅሎቻችን በእግራቸው እንዳይረግጡት በጥንቃቄ እንመራቸው ነበር ። . . . በሬሳ የተሸፈነው ረዥሙ ሜዳ አለቀ ድረስ በመሐረቤ አፍንጫዬን ይዤ ዐይናቼን ባጋማሽ ከድኜ አቋረጥሁ ።

የማዦር ሳልሳ ተከታይ ሆኖ የተላከው ሌተና ሮቬርሲ ፣ የጉዞን አስቀያሚና አሠቃቂ ሥዕል በዚህ ዓይነት ካመለከተ በኋላ ምኒልክ ከዓድዋ ወደ እንትጮ ተዛውረው አሉበት አዳራሽ ገብቶ የውን ሁኔታ ደግሞ እንደዚህ ሲል በመተረክ ያቀርባል ።

. . .ምኒልክ በዙሪያቸው ያጌጠ ልብስ የለበሱ መኳንንቶች አስከትለው ከዓድዋ መጥተው እንትጮው እንደ ደረሱ ሰፈር አደረጉ ። ከሰዓት በኋላም እቴጌ ጣይቱ ደረሱ ። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መጠናቸው የተለያየ ነጫጭ ድንኳኖች በትንሽ ደቂቃዎች ውስጥ ተተክለው አየናቸው ። የሹማምንቱ ድንኳኖች ልዩ ልዩ ቀለም ነበሩዋቸው ። ሰፈሩ በሥነ ሥርዓትና ፍጥነት ባለው ጊዜ ውስጥ ተሠርቶ አልቆ ሳየው እስካሁን ድረስ በዐይኔ ፊት የሚደቀን ያማረ ሥዕል ሆኖ ይታየኛል ። በ4 (10) ሰዓት አንድ የራስ መኰንን ወታደር መጥቶ ወደ ጌታው ወሰደን ። ከርሱም አንዱ ሹም ተቀብሎ ከራስ መኰንን ድንኳን ሁለት መቶ ሜትር ርቆ የተዘጋጀልንን ድንኳን አስረከበን ። ከማታው በ8 ሰዓት (2) ራስ መኰንን ወደ ድንኳናቸው ጠርተውን ተገናኙንና መጠጥ ጋበዙን ። ከዚያ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ነገ ትገናኛላችሁ ብለው አሰናበቱን ። ከደረስንበት ጊዜ ጀምሮ ጧትና ማታ ምግባችን በደንብ ይመላለስልን ነበር ።

በማግሥቱ ጧት ፣ ፊታውራሪ ደሳለኝ መጥቶ እየመራ ወደ ንጉሡ ወሰደን ። 500 ሜትር ርቀት ባለው በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ዙሪያ ያልታወቀ ሰው እንዳይገባ ጩኸትና ልፍለፋ እንዳይደረግ ወታደሩ እንደ አጥር ሆኖ ይጠባበቃል ። ከዚህ የወታደር አጥር ላይ ስንደርስ የኛን ከብቶቻችንንና ተከታዮቻችንን ትተን እንድንገባ ተገደድን ። ወዳንድ ልዩ ድንኳን ገብተን ዐርፈን እንደቆየን አንድ ሰው መጣና ማዦር ሳልሳን ጠራው ። መሣሪያ አለመያዙን ለማረጋገጥ እየበረበረ ከፈተሸው በኋላ ወዳጄ ምኒልክ ይዞት ሔደ ። እኩል ሰዓት ከቆየ በኋላ

፬ኛ የኢጣልያ ጦር በዓድዋ ሲፈርስ በአዲግራት ምሽግ እንደ ተከበቡ የተቀመጡትን ጣሊያኖች በስምምነት ማስለቀቅ፣

፭ኛ በከሰላ በኩልም ኢጣልያኖች በደርቡሾች ተከበዋል የሚሉ ወሬ ስለተሰማ ለነርሱም እርዳታ መላክ።

ስለዚህ፣ በሌሎቹ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች በትጋት ከማከናወን ጋር በ፪ኛና በ፬ኛ ቁጥሮች የተመለከቱትን ጉዳዮች ለመፈጸም፣ ከጦርነቱ በፊት ወዳፄ ምኒልክ ዘንድ በመላክ የታወቀው ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ተመረጠ። ለርሱም ረዳት የሚሆነው የኢትዮጵያውያንን ባህልና የትግርኛ ቋንቋ የሚያውቀው የአዲኳላ ምስለኔ ቴኔንቴ ሮቬርሲ ተጨመረለት። ከነዚህም ጋር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ባስተርጓሚነት በኢጣልያኖች ዘንድ የታወቁት፣ ደጃች ባሕታ ከኢጣልያ ሸፍተው የሰገነይቴውን ምስለኔ ቴኔንቴ ሳንጉይኔቲን ያሰሩ ጊዜ ስለ ኢጣልያዊው መኰንን እስራትና መጉላላት ከባሕታ ሐጐስ ጋር የተጣሉትና በዚህም ሥራቸው ሁሉ በኢጣልያኖች ዘንድ በጣም የተወደዱት አቶ ገብረ እግዚአብሔር ተሰጡት።

በዚህ ዐይነት ማዦር ሳልሳ እነዚህን እንዳስከተለ በሐያ ሰው ታጅቦ ከአሥመራ ወደ አዲኳላ መጣ። ከጄኔራል ባልዲሠራ እንደ ታዘዘው የአዲኳላ ምስለኔ ስለ ሰላም እንዲዋዋል የኢጣልያ መንግሥት ማዦር ቶማሶ ሳልሳን መሾሙን ዐፄ ምኒልክ ዐውቀው እንዲቀበሉት ለራስ መኰንን ደብዳቤ በመላክተኛ እጅ በቶሎ ላከ። አዲኳላ ሆነው ሌቱንም ምንም እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ሲጠብቁ አድረው መልሱ ስላልመጣ፣ መቼም መፈቀዱ አይቀርም ብለው ጉዟቸውን ወደፊት ቀጥለው በየካቲት 27 ቀን (መጋቢት 6 ቀን) ጉንደትን አለፍ እንዳሉ ከራስ መኰንን ዘንድ ከተላኩት መላክተኞች ጋር በመንገድ ተገናኙና ከራስ መኰንን የተጻፈውን ደብዳቤ ለሳልሳ ሰጡት። በደብዳቤው ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ሳልሳን ለመቀበል መፍቀዳቸው፣ እነርሱንም እየመሩ የሚወስዱ ሁለት መኳንንት ታዘው መንገድ መጀመራቸው ተገለጸለት።

በዚህ ዐይነት ተጉዘው አዲ ቆሆት ሲደርሱ፣ ከሁለቱ መኳንንት ጋር ተገናኙ። እነርሱም ፊታውራሪ ደሳለኝ የራስ መኰንን መላክተኛ፣ ደጃች እርአያ የራስ መንገሻ ዮሐንስ መላክተኛ ናቸው። ከእነርሱም ጋር በመልካም መግባባትና ሰላምታ ከተገናኙ በኋላ፣ አዲቆሆት የደጃች እርአያ ግዛት ስለሆነ፣ በመልካም መስተንግዶ አድረው በማግሥቱ ከመጋቢት 11 እ.ኤ.አ. ዠምሮ ተጉዘው ዐፄ ምኒልክ ሰፈር እስኪደርሱ ድረስ ያዩትን ሁኔታ በቀጥታ ከራሱ ከቴኔንቴ ሮቬርሲ ጽሑፍ መመልከት የተሻለ ነው።



...ከአዲ ቆሆት በማግሥቱ ተነሥተን 2 ሰዓት እንደ ተጓዝን ዐፄ ምኒልክ ያሉበትን እኛም መኳንንቱም አናውቅም ነበርና አስተዋዩ ፊታውራሪ ደሳለኝ በያዘው መነጽር አተኩሮ ሲያይ እንደ ደመና የቆመ አቧራ ተመለከተና ወደ ፈረስ ማይ የሚጓዘው የሸዋ ጦር (ያፄ ምኒልክ) ነው ብሎ ነገረን። ወደዚያም ለመድረስ የዩሃን ሜዳ ማቋረጥ ነበረብን። በዚሁ ሜዳ በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የሞቱት ያብዛኞች ጣልያኖች ሬሳ ፊታቸውን ወደ አንዲት ፈሳሽ ወንዝ አድርገው እንደወደቁ ይታዩ ነበር። ሜዳው በሙሉ በሬሳ ተሸፍኖ ነበር። በአፍሪካ 6 ዓመት ሰኖር ብዙ ቁስለኛና ሬሳ አይቻለሁ፣ የአቅርዳትንም የጦር ሜዳ ተመልክቻለሁ። ነገር ግን በዚህ ቀን በዩሃ ሜዳ እንዳየሁት የመሰለ የሬሳ ብዛት በፍጹም አይቼ አላውቅም። ጦርነቱ በተደረገ በ8ኛው ቀን በመካከሉ ሳልፍ ሬሳውን አሸናፊዎቹ ሳይገፉት ጅብም ሳይነካው እንዳለ ነበር...ሬሳው አንዱ ካንዱ የተቀራረበ በመሆኑ በቅሎቻችን በእግራቸው እንዳይረግጡት በጥንቃቄ እንመራቸው ነበር።...በሬሳ የተሸፈነው ረዥሙ ሜዳ አለቀ ድረስ በመሐረቤ አፍንጫዬን ይዤ ዐይኖቼን ባጋማሽ ከድኜ አቋረጥሁ።

የማዦር ሳልሳ ተከታይ ሆኖ የተላከው ሌተና ሮቬርሲ፣ የጉዞውን አስቀያሚና አሠቃቂ ሥዕል በዚህ ዓይነት ካመለከተ በኋላ ዐፄ ምኒልክ ከዓድዋ ወደ እንትጮ ተዛውረው አሉበት አዳራሽ ገብቶ ያየውን ሁኔታ ደግሞ እንደዚህ ሲል በመተረክ ያቀርባል።

...ምኒልክ በዙሪያቸው ያጌጠ ልብስ የለበሱ መኳንንቶች አስከትለው ከዓድዋ መጥተው እንትጮው እንደ ደረሱ ሰፈር አደረጉ። ከሰዓት በኋላም እቴጌ ጣይቱ ደረሱ። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መጠናቸው የተለያየ ነጫጭ ድንኳኖች በትንሽ ደቂቃዎች ውስጥ ተተክለው አየናቸው። የሹማምንቱ ድንኳኖች ልዩ ልዩ ቀለም ነበሩዋቸው። ሰፈሩ በሥነ ሥርዓትና ፍጥነት ባለው ጊዜ ውስጥ ተሠርቶ አልቆ ሳየው እስካሁን ድረስ በዐይኔ ፊት የሚደቀን ያማረ ሥዕል ሆኖ ይታየኛል። በ4 (10) ሰዓት አንድ የራስ መኰንን ወታደር መጥቶ ወደ ጌታው ወሰደን። ከርሱም አንዱ ሹም ተቀብሎ ከራስ መኰንን ድንኳን ሁለት መቶ ሜትር ርቆ የተዘጋጀልንን ድንኳን አስረከበን። ከማታው በ8 ሰዓት (2) ራስ መኰንን ወደ ድንኳናቸው ጠርተውን ተገናኙንና መጠጥ ጋበዙን። ከዚያ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ነገ ትገናኛላችሁ ብለው አሰናበቱን። ከደረስንበት ጊዜ ጀምሮ ጧትና ማታ ምግባችን በደንብ ይመላለስልን ነበር።

በማግሥቱ ጧት፣ ፊታውራሪ ደሳለኝ መጥቶ እየመራ ወደ ንጉሡ ወሰደን። 500 ሜትር ርቀት ባለው በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ዙሪያ ያልታወቀ ሰው እንዳይገባ ጩኸትና ልፍለፋ እንዳይደረግ ወታደሩ እንደ አጥር ሆኖ ይጠባበቃል። ከዚህ የወታደር አጥር ላይ ስንደርስ የጭን ከብቶቻችንንና ተከታዮቻችንን ትተን እንድንገባ ተገደድን። ወዳንድ ልዩ ድንኳን ገብተን ዐርፈን እንደቆየን አንድ ሰው መጣና ማዦር ሳልሳን ጠራው። መሣሪያ አለመያዙን ለማረጋገጥ እየበረበረ ከፈተሸው በኋላ ወዳፄ ምኒልክ ይዞት ሔደ። እኩል ሰዓት ከቆየ በኋላ

ያው ስውዬ መጥቶ በተራዬ ጠራኝ ። በኔ ላይ ያደረገው ምርመራ ከፍ ያለ ነው ። ኮቱንና የውስጥ ልብሴን ሳይቀር ባርሜጣና ኪሶቼን እየደ ጋገመ ፈትሾ አንድ የርሳስ መቅረጫ ስንጢዩን አስቀርቶ የቀረውን መልሼ እንድለብስ ፈቀደልኝና ለጓደኛው አስረከበኝ ። እርሱም እየመራ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን አገባኝ . . .

በመጀመሪያ ዋናው የመልእክቱ መሪ ማዦር ሳልሳ ከገባ በኋላ ቀጥሎ ራሱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ተጠርቶ መግባቱን ሲያወሳ ፣ ላስተርጓሚነት የመጡት ገብረ እግዚአብሔር ለመግባት አልተፈቀደላቸውም ማለት ነው ። ይኸው ሮቬርሲ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ከገባ በኋላ ፣ ባይኑ ያየውንና በጆሮው የሰማውን ለዛሬ ትውልድ የተወልንን ማስታወሻ በቀጥታ ከጸሐፈው የሚቀጥለውን መረዳቱ ጠቃሚ ነው ።

እየመራ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ውስጥ አገባኝና በስመ ጥሩው ንጉሠ ፊት ቆምሁ ። ንጉሡ ከሙሉ ዕድሜ አጋማሽ አለፍ ያሉ ናቸው ። ለስላሳ የብልህ መልክ አላቸው ። ቆዳቸው ግን ጥቁር ነው ። ያበሻን ቤተ መንግሥት ሥርዓት ካለማወቄ የተነሣ ለአውሮፓ ንጉሥ እንደሚደረገው እጅ ነሥቼ ማዦር ሳልሳ አጠገብ ወዳለች ባዶ ወንበር የኔ ሳትሆን አትቀርም በማለት ሔጄ ቆሜ ስጠባበቅ ምኒልክ ወደርሳቸው እንድቀርብ ጠቀሱኝና ተጠግቼ እጃቸውን ዘረጉልኝና ለመጨበጥ ቻልሁ ። ከዚያ አንዳንድ ጥያቄ ካቀረቡልኝ በኋላ ፣ እንድ ቀመጥ ፈቀዱልኝና ስቀመጥ እኔ ከመድረሴ በፊት ከማዦር ሳልሳ ጋር የጀመሩትን ንግግር ይቀጥሉ ጀመር ። በዚህ ንግግር ሰዓት ዐፄ ምኒልክ ሁኔታ ገረመኝ ። ንግግሩ በሚቀጥልበት ሰዓት በመልካቸው ላይ ምንም ሥጋት ሳይታይ በግድየለሽነት አንዳንድ ጊዜ በፈገግታ የደስታ መልክ እያሳዩ ይነጋገሩ ነበር ። . . . ሰሞኑን ካንድ የመንግሥት ባላጋራ ጋር ሲዋጋ ቆይቶ መንግሥታዊ ንግግር ከሚያደርግ ንጉሥ ይልቅ ምንም ነገር ሳይደርስበት ተዝናንቶ የዕረፍት ጊዜ የሚያሳልፉ ይመስሉ ነበር ።

. . . በዋናው ንግግር መካከልም ተራ ንግግር ጣልቃ እያገቡ በኢጣልያ አገር ታላቅ እንቁላል የሚወልዱ ልዩ ልዩ ዶሮዎች አሉ ሲባል የሰሙት እውነት መሆኑን ፣ ቀጥሎም በፊተኛው ጊዜ የሚያውቋቸውን የኢጣልያ ሹማምንት የነካፒቴን አንጌራን የነሴተና ፓርቲኔን የነ ፊልተርንና የሌሎቹንም ደህንነት ይጠይቁ ነበር ። እነዚህም ሁሉ ከሞት መትረፋቸውን ሲሰሙ ደስታቸውን ይገልጹ ነበር ። በዚህ ዓይነት የግዴለሽነት ሁኔታ ማሳየታቸው የዘዴ መን ገድ እንደሆነ ገብቶኛል ። . . .

ማዦር ሳልሳና ዐፄ ምኒልክ የወሰን ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ እኔ በምኒልክ አጠገብ ያሉትን ራሶች እመለከት ነበር ። ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ በቀር የቀሩትን ገና ማየቴ ነበር ። በዚያም የሚታዩት ራሶች የሰውነታቸው ቅርፅ ልዩ ልዩ ነው ። . . . ወፍራሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ማዕዘንማ ቅርፅ ያላቸው ራስ መኰንን ፣



አጠር ቀጠን ያሉት ራስ መንገሻ አቲከም የስፖርት ሰው የሚመስ ሉት ራስ ሚካኤል . . . መልከ መልካሙ የትግሬው ራስ መንገሻ ይታዩ ነበር ። እነዚህ ሁሉ የለበሱት ያማረና በወርቅ ያጌጠ ልብስ ነበር ። . . . ምኒልክ ከሳልሳ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ እነዚህ ራሶች ዝም ብለው ይመለከቱ ነበር ። በኋላ ግን ፣ ከራሶቹ ጋር ለመመካከር ማዦር ሳልሳ ወደ ውጭ ይወጣ ዘንድ ንጉሡ ለመኑትና ወጣ ። ከራሶቹ ከተመ ካከሩ በኋላ እንደገና ሳልሳን አስጠሩት ። በዚያም ጊዜ አንዳንድ የምኒልክን የቀድሞ አሳቦች ራሶቹ ለውጠውት አዲስ ሁኔታ ተፈ ጥሮ ክርክር ተደረገ . . .

በዚህ ሮቬርሲ በተወልን የጽሑፍ ማስታወሻና ደ ሉሊባር ያሳተመው አነጋገር ልክ ነው ። "ዐፄ ምኒልክ ከሙሉ ዕድሜ አጋ ማሽ አለፍ ያሉ ናቸው" ያለው ፣ ዐፄ ምኒልክ የዓድዋ ጦርነት ጊዜ ዕድሜያቸው 52 ዓመት ከመንፈቅ ስለሆነ ፣ ግምቱ ልክ ነው ። "ትልቅ ጦርነት ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ባደረጉበት ሳምንት ሲነጋገሩ የሥጋትና የፍርሃት መልክ በማሳየት ፈንታ ተዝናንተው በግድየለሽነት አነጋገሩን" ያለው ፣ እንኳን ድልን ባገኙበት ሳምንት ፣ በጦርነቱም ሰዓት ቢሆን ዐፄ ምኒልክ ይኸን ዓይነት አቅዋም ማሳየት የተለምዶ ባሕርያቸው ነበር ። በሰላም ንግግር ጊዜ ይኸው ዐይነቱ አቅዋም ጠላትን ከሥጋት ላይ ጥሎ ከጠላት የበለጠ ለመጠቀም ይረዳል ። "የአንጌራን ፣ የፓርቲኒንና የፊልተርን ጤንነት ጠየቁ" ያለውም ፣ እነዚህ ሦስቱም ከዓድዋ ጦርነት በፊት በመቀሌው ከብ ጊዜ በዕርቅ ሰበብ እየመጡ በራስ መኰንን አማካይነት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የተዋወቁ ናቸው ።

ሌላው የሮቬርሲ ዝርዝር ፣

ከድንኳናችን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ስንመላለስ ፣ ቁጥሩ በበ ረከተ ተቀራርቦ በተተከለ ድንኳን መካከል ማለፍ ነበረብን ። የሚን ቀሳቀሰው የወንዱ ፣ የሴቱ ፣ የልጁ ብዛት ልክ እንደ አንድ ትርዒት ይመስላል ። ምንም እንኳን ጠባቂና አጃቢ ቢኖረን ሕዝቡ ወራዶች እያለ ይሰድበን ነበር ።

ከሁሉም በስድብ ረገድ ሴቶቹ ይበልጡ ነበር ። እኛም እየሰማን እንዳልሰማ እናልፍ ነበር ። ይኸንኑ ለሳልሳ ስነግረው ፣ ነገ ለእቴጌይቱ ስላምታ ለማቅረብ ስንሔድ የበለጠ ሳይደርስብን አይቀርምና ለኢጣልያ ስንል ሁሉንም መዋጥ አለብን አለኝ ።

ይላል ። ከዚህ አያይዞ ፣

ዐፄ ምኒልክ ዘንድ ቀርበን ንግግር በምናደርግበት ጊዜ እቴጌን እጅ እንድንነሣ እንዲፈቀድልን ብናመለክት ሸፈንፈን ብለው ቆይተው

ግዴለም እኔው እነግርላችኋለሁ አሉ ። የባለቤታቸውን ጠባይ የሚያውቁት ስለሆነና እቴጌይቱ በመጥፎ ሁኔታ እንደሚቀበሉን ተገንዝበው ስላስቀሩን ውለታ አድርገውልናል ።

ከዚያ ደግሞ እልፍ ብሎ በሌላ ቦታ ላይ ፤

> አምስት ቀን በቆየንበት ጊዜ ደህና መስተንግዶ ተደርጎልን ነበር ። ራሶቹ ሁሉ መልካም አስተያየት አድርገውልናል . . . ምኒልክ የዓድዋውን ጦርነት አንሥተው እኛን ለማሳዘን አንድ ቀንም የቁጣና የወቀሳ ነገር አንሥተው አያውቁም . . . ጥረታቸው ሁሉ ያተኮረው ወደ አንድ ሰላም ለመድረስ ነው ።

ሲል ይደመድማል [1] ።

ሌላው ጸሐፊ ከዚሁ እያይዞ ፤

> በድል አድራጊነት ሰዓት ምኒልክ ከሹመት አባቶቻቸው የሚለዩበት ሁኔታ አላቸው ። ድል በተገኘበት የሁካታ ሰዓት በተሸናፊዎች ላይ መጨከን አይወዱም ። ዘወትር የምሕረት እጃቸውን ለጠላታቸው ይዘረጋሉ ። [2]

ሲል የንጉሠ ነገሥቱን ችሎታና ጠባይ አመስግኗል ። ከሹመት አባቶቻቸው የሚለው ፤ ዐፄ ቴዎድሮስንና ዐፄ ዮሐንስን ማለቱ ይመስላል ።

በዚህ ዓይነት ፤ የጦር መኰንኖቹ ከጦርነቱ በፊት በኢትዮጵያውያን ላይ የነበራቸው የንቀት አስተያየት ከጦርነቱ በኋላ የተለወጠ ይመስላል ። ባለፈው በአላጌ ጦርነት አገር ሊወር የመጣው የጠላት መኰንን ፤ ማዦር ቶዜሊ ከነጓደኞቹ በክብር መቀበሩ በመቀሌ ብዙ ነፍስ ያጠፋውና ያስጠፋው ጋልያኖ በዓድዋ ጦርነት ከመሞቱ በፊት በሽኝ ወደ ወገኖቹ እንዲደባለቅ መደረጉ የሚታወስ ነው ። አሁን ደግሞ ፤ በብዙ መሥዋዕትነት የዓድዋ ድልን ቢያገኙም፣ ከወገናቸው ብዙ ዘመድ አዝማድ የሞተባቸው ራሶችና ንጉሠ ነገሥቱ ምንም የቁጣ መልክ ሳያሳዩ ፤ ሰላም መፈለጋቸውን ሲገነዘበው ፤ ይኸን የመሰለው የማሸነፍ ዕድል በኢጣልያኖች እጅ ገብቶ ቢሆን ምን ዐይነት የኩራትና የትዕቢት አቅዋም እንደሚኖራቸው ሮቬርሲ የሁለቱን ሕዝብ የጠባይ ልዩነት በሕሊናው ሳያመዛዝነው አልቀረም ።

ቴኔንቲ ሮቬርሲ ፤ ከዚህ በላይ ያነበብነውን ጠቃሚ ዝርዝር ሲሰጠን ፤ ማዦር ሳልሳ ከጄኔራል ባልዲሠራ ተልኮ ወደ ዐፄ ምኒልክ የመጣበትን ዋናውን የእርቅ ጉዳይ ካፄ ምኒልክም የተሰጠውን መልስ አልጻፈውም ። ለማንኛውም ዋናው መላክተኛ ማዦር ሳልሳ በዘመኑ አዘጋጅቶት ከሞተ በኋላ ወገኖቹ በስሙ ካሳተሙት መጽሐፍ ላይ አንዳንድ መረጃዎች እንመለከታለን ።

---

1 Douze ans en Abyssinie ,Paul de Laulibar, PP.537-567.

2 Menelik II I'Etiopia le relationi Con l'Italia, Et. Falcone, p 156.



በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ማዦር ሳልሳ ከአሥመራ ወደ አዲኳላ ከዚያ ወደ ዐፄ ምኒልክ መጥቶ ላዩን ሬሣ ለማስቀበርና የተማረኩትን የኢጣልያ ሹማምንቶች ስም ለማወቅ ሲሆን ፤ ውስጡን ግን ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ኤርትራ ሳያመሩ ጠቅላላ እርቅ የሚደረግበትን ለመፈተን ነበር ። ካፄ ምኒልክ ጋር ተነጋግሮ ያገኘውን መልስ ወደ አዲኳላ ተመልሶ በስልክ ለጄኔራል ባልዲሠራ መንገሩ ፤ ከዚያ ወደ ዐፄ ምኒልክ ሁለተኛ ጊዜ ተመልሶ በመምጣት የመጨረሻውን የእርቅ አሳብ ከዐፄ ምኒልክ ተቀብሎ በቀጥታ አሥመራ ሔዶ በቃል ጭምር እያስረዳ ጽሑፉን ለጄኔራል ባልዲሠራ ማስረከቡ ፤ ይኸንንም በአማርኛ ተጽፎ የተላከለትን ጄኔራል ባልዲሠራ ወደ ኢጣልያንኛ አስተርጕሞ በቴሌግራም ለኢጣልያ መንግሥት ማስተላለፉ ተጽፏል ።

በመጋቢት 8 ቀን 1888 ዓ. ም. በዐፄ ምኒልክ ዘንድ የተገለጸው የዕርቅ አሳብ ፤ ውጫሌ ላይ የተደረገው ውል በኢትዮጵያና በኢጣሊያ በሙሉ መፋቁን፣ አዲስ ውልም የሚያበጁበት በኤውሮፓ ያሉ ነገሥታት ሁሉ እንደሚዋዋሉት ውልና ሥርዓት እንደሚሆንና የወሰኑም ጉዳይ እንዳለ እንደሚቆይ ይገልጻል ።

ጄኔራል ባልዲሠራም የዕርቁን አሳብ ተቀብሎና የራሱንም አጭር አሳብ ጨምሮ ወደ ሮማ ለመንግሥቱ በቴሌግራም አስተላልፏል ።

ባልዲሠራ ይኸን ቃል ወደ ሮማ ለመንግሥቱ ካስተላለፈ በኋላ፣ ከኢጣልያ መንግሥት ዘንድ ፤ "ይኸንን የመሰለውን እርቅ እንድታደርግ ፈቅደንልሃል ። ነገር ግን ከእርቁ በፊት የውጫሌ ውል ከመሰረዙ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለኢጣልያ እምቢ ያለውን የበላይ ጠባቂነት መብት ለሌሎች ያውሮፓ ኃያላን እንዳይሰጥ ቃል አስገባ" የሚል ቃል ተጨምሮ መጣለት ። እርሱም በበኩሉ ፤ "ይህ ሁኔታ ባገራቸው ላይ ያላቸውን ሙሉ ሥልጣናቸውን እንደሚቀንስባቸው እየተገነዘቡ የውጭን አገር ጠባቂነት እንዳትቀበሉ ውል ግቡ ብንላቸው አይፈቅዱም ። በዚህ ምክንያት ስንከራከር ፤ ጦሩን ይዞ ምኒልክ ወደ ሸዋ የተመለሰ እንደሆነ እርቁ ፈርሶ ጠቡ ይቀጥላል" የሚል ቃል ጨምሮ ወደ ኢጣልያ አገር እንደገና መልስ ሰጠ ።

በዚሁ መካከል ፤ ከሮማ መልሱ ሳይመጣ ስለቆየና ሳልሳ ከአሥመራ መልሱን ይዞ ወደ ዐፄ ምኒልክ ሊመለስ ቃል የገባበት ጊዜ መጋቢት 25 እ.ኤ.አ. (መጋቢት 16 ቀን) ስለ ደረሰ ጄኔራል ባልዲሠራ ሳልሳን ወደ ዐፄ ምኒልክ እንዲሔድ አሰናበተው ። ሳልሳ በአዲግራት በኩል አድርጎ ወደ ዐፄ ምኒልክ በሚጓዝበት ጊዜ ፤ "የሌላን መንግ

ሥት ጠባቂነት ኢትዮጵያ እንዳትቀበል ምኒልክን በውል ማስገባት
ፍጹም አስፈላጊ ነው” የሚል ከኢጣልያ መንግሥት ለባልዲሠራ
መልስ ስለ መጣለት ፡ ይኸንኑ ቃል በግሥጋሤ ባልዲሠራ ለሳልሳ ከመ
ንገድ እንዲደርስለት ላከለት ። ሳልሳም ያንን እንደያዘ ከአዲግራት
አልፎ ከራስ መኰንን ጋር ተገናኙ ። ከዚያ ሁለቱም አብረው ወደ
ምኒልክ ዘንድ ቀርበው ሳልሳ ላፄ ምኒልክ የተላከበትን አዲስ ሐሳብ
አቀረበ ።

በዚህ ጊዜ ምኒልክ በፊት በጽሑፍ የላኩትን የውል አሳብ እንደ
መጨረሻ ቆጥረውት ሳለ ፡ አሁን ግን ከማዦር ሳልሳ ጋር አስቀድሞ
በተነጋገሩት ላይ አዲስ አሳብ በመጨመሩና የቀድሞ አሳባቸው ስለ
ተለወጠ ተገረሙ ። በርሳቸው በኩል የእርቁን ውል ጽፈው አትመው
ሰጥተውት የራሱንም አሳብ ለእርሳቸው ትቶ ከሔደ ወዲህ ይጠብቁ
የነበረው ከኢጣልያ ንጉሥ ዘንድ አንድ ታላቅ ባለሥልጣን ተልኮ
መጥቶ በዚሁ በቀረበው ሐሳብ ተዋውለው ዘለቄታ ውል አዲስ አበባ
ከገቡ በኋላ ለመዋዋል ነበር ። አሁን ግን ፡ ምንም እንኳን በጠቅላላው
የቀረበውን ውል የኢጣልያ መንግሥት ቢቀበል በዚህ ላይ ፡ “የሌላ
መንግሥት ጠባቂነትን ሳትቀበሉ ውል ግቡ” የሚል ቃል ካልተጨ
መረ አይሆንም የሚል የመንግሥቱን መልስ ይዞ ስለመጣ ዐፄ
ምኒልክ በዚሁ ተናደው ፡ “የሰጠሁህን ጽሑፍ መልሰህ አምጣ ። ያንንም
እስከታመጣ ድረስ እዚሁ መያዣ ሆነህ ተቀመጥ” ብለው ማዦር
ሳልሳን እንደ መያዣ አቆዩት ። ይኸንንም ጄኔራል ባልዲሠራ እንዲያ
ውቀው ከዚህ እንደሚከተለው ደብዳቤ ጻፉለት ።

> ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአ
> ብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከጄኔራል ባልዲሠራ
> ሰላም ላንተ ይሁን ። ማዦር ሳልሳ መጀመሪያ የመጣው ተርታ የሆኑትን
> ነገሮች ለመነጋገር ከዚያ ከኢጣልያ የንጉሥ ማኅተም ይዞ መጥቶ
> ዘለቄታ ያለው ውል ልንዋዋል ንግግራችን በዚሁ አልቆ ነበር ። ሁለ
> ተኛ ጊዜ ወደኔ ሲመጣ ንግግራችንን በጽሑፍ አድርገን የኔን ንግግር
> ጽፌ ለርሱ ሰጠሁት ። የርሱንም ለኔ ሰጠኝና ይኸንኑ ከናንተ ጋር ተነ
> ጋግሮ እንዲጨርስና አሳቡም እንዲመለስ ሔደ ። አሁን እንደገና ወደኔ
> ተመልሶ የተነጋገርንበት ሁሉ ቀረና አዲስ ነገር ይዞ ስለመጣ የእርቁ
> ነገር ቀርቶ ቃሉን ስለለወጠ ፣ ደግ ነው እንግዲህ ጽፌ አትሜ የሰጠ
> ሁህን መልስልኝና የራስህንም ውሰድ ብለው ጽሑፉን እሥመራ
> ትቼው ነው የመጣሁት አለኝ ። እኔም አስመጥተህ እስክትሰጠኝ ድረስ
> እዚሁ እኔ ዘንድ ቆይ ብዬ አቆይቸዋለሁ ። ይኸንንም መጻፌ በሌላ
> ምክንያት ያቆየሁት እንዳይመስላችሁ ብዬ ነው ።
>
> መጋቢት 28 ቀን 1888 ዓ.ም.

ዐፄ ምኒልክ፡ ከየካቲት 23 ቀን እስከ የካቲት 28 ቀን በዐድዋና በፈ
ረስ ማይ ከሰነበቱ በኋላ ፡ መረብን አልፈው ወደ ኤርትራ ለመሻገር



ከዓድዋ ወደ እንትጮ ተጓዙ ። ከቶማሶ ሳልሳ ጋር የእርቅ ጉዳይ
ጀምረው ይኸም ተንኮል ያለበት በመሆኑ ሳይሳካ ቀርቷል ። ይህ
የተንኮል ዘዴ ባፄ ምኒልክ ዘንድ ታውቆ እንደ ነበረ ግራዝማች
ዮሴፍ ለምንዶን ባስተላለፉት ጽሑፍ ላይ እንደዚህ ተብሎ ተገልጿል።

> እንትጮ ሳለን ከጻፍሁልዎ ወዲህ የተገኘ ታሪክ ይህ ነው ።
> ማዦር ሳልሳ የሚባል የኢጣልያ ሹም የሞተውን ልቅበር ብሎ ወደ
> ጃንሆይ ላከ ። ጃንሆይም ምን ከፋኝ ከተቻለህማ ቅበር እንጂ ብለው
> ተቀባይ ሰው ላኩለት ። ጃንሆይ ግን ፡ እንደ ልማዱ የማታለል ምክንያት
> እንደሆነ ዐውቀውበት ነበር ።እነዚያም ሊቀበሉት የሔዱት ሰዎች የራስ
> መኰንን ፊታውራሪ ደሳለኝና የኔ ዘመድ የሆኑ ደጃች እርአያ ነበሩ ።
> እነዚያም ሬሳ በወደቀበት ማሀል ይዘውት መጡ ። የሬሳውንም ብዛት
> ባየ ጊዜ የጦሩ ብርታት ታወቀውና አጥብቆ ደነገጠ ። የኢጣልያኖች
> ሬሳ የወደቀበት ካባ ገሪማ ጀምሮ እስከ መረብ ድረስ ነበር ። አወዳደ
> ቁም ተነባብሮ መሬቱ አይታይም ነበር ። ስለዚህም ምክንያት እንኳን
> ለመቅበር አይቶ ለመጨረስ አልተቻለውም ። እርሱ ግን ፡ ልቅበር
> ማለቱ እጅግ ተንኮለኛ ሰው ነበርና ጃንሆይ ወደ ሐማሴን መኳዝንን
> (መኳዛቸውን) ቢሰግ በመቅበር ምክንያት መጥቶ የእርቅ ነገር
> ጀመረ . . .

በማለት ግራዝማች ዮሴፍ ፡ የሳልሳና ያለቃው የባልዲሠራ ተንኮል
በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ መታወቁን ገልጸዋል ። እንደ ርሳቸውም አባባል
ሁለቱ የኢትዮጵያ መልክተኞች ሳልሳን እየመሩ ያመጡት ሆነ ብለው
ሬሳ በብዛት በተረፈረፈበት ቀበሌ ይመስላል ። የባልዲሠራ አዲስ
ጦር ይዞ መምጣቱ ወሬው ሳይሰማ አይቀርምና ሳልሳ በብዙ ሬሳ
መካከል ሲያልፍ ብዛቱን በሚመለከትበት ጊዜ የኢትዮጵያን ወታደር
ጀግንነት አጢኖ ላለቆቹ የወደፊቱን ጦርነት መክሮ እንዲያስቀር ታስቦ
ይሆናል ። መቼም ባራቲዬሪ ጦርነቱን በመራበት ጊዜ ጥፋት ሁሉ ስለ
ተበላሸበት ፡ ባሁኑ ጊዜ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች የተማረከባቸውንና
የሞተባቸውን የጦር መኳንንትና የወታደር ቁጥር በትክክል ስለማያው
ቁት ፡ ሳልሳ በዚህ ጉዞው ከተማረከው ይልቅ የሞተው እንደሚበልጥ
ይረዳዋል ማለት ነው ።

ከዚሁ አያይዘው ግራዝማች ዮሴፍ፣ ስለ ኢጣልያኖች መሸበር ማዦር
ሳልሳ ደግሞ በጠባዩ እርቅም ጦርነትም የማይፈልግ ሰው ስለመሆኑ፤

> ጃንሆይ ከዓድዋ ተጉዘው ደብረ ዳሞ አጠገብ የሰፈሩ ጊዜ ምጥዋ
> ድረስ ተሸብሮ ነበር ። የዓዲ ቀይህን የሰገነይቲን እርድ (ምሽግ) አፈር
> ባሩድና ዕቃውን አቃጥሉ ነበር ። ጉማ ድረስ ወረደ ። ወታደሩም ነፍ
> ጡን እየጣለ ወደ ምጥዋ ይሸሽ ነበር ። ስለዚህ ሽሽቶ ከዓድዋ ጦርነት
> ያመለጠ የኢጣልያ ወታደር ፍርሃት አድርበት ነበር ። ማዦር ሳልሳ
> ግን እርቁንም ጦርነቱንም የማይወድ ሰው ነው ። በጥር ከጦርነቱ
> በፊት በዩሃ የሰፈርን ጊዜ አስታርቃለሁ ብሎ መጥቶ ነበር ። ጃንሆ
> ይም ምን ከፋኝ እርቅ ከፈለጋችሁ አገሬን ልቀቁልኝ ቢሉት ፡ ተመልሶ

ሔዶ ለባራቲዬሪ ነግሮ የጦር ባንዲራ አስተከለ ። ኋላም በየካቲት 23 ቀን የመጨረሻው ጦርነት የሆነ ጊዜ አንድ መድፍ ሳይተኮስ ፣ የዐሥር ነፍጥ ተኩስ ሳይሰማ በፈረስ ሸሽቶ አዲኳላ ገብቶ አደረ ። ይኸንንም በፈረስ ማምለጡን የነገረን እርሱ ራሱ ነው ” ።

ብለዋል ።

በዚህ አነጋገር ግራዝማች ዮሴፍ ፣ “ንጉሠ ነገሥቱ በእንትጮ አልፈው ደብረ ዳሞ አጠገብ ሰፍረው የነበረ ጊዜ ከመረብ ጀምሮ እስከ ምጥዋ ድረስ ተሸብሮ ነበር” ያሉት ትክክለኛ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት እያመለጡ ከመረብ ባሻገር የሔዱ የኢጣልያ ዘማቾች ሁሉ፣ የጦር ነቱን ብርታትና የኢጣልያኖቹን እልቂት ፣ የኢትዮጵያን ወታደር ጉብዝና እያጋነኑ በመናገራቸው ከነርሱ የሰማው ሁሉ ልቡ እንደሚሸበር አይጠረጠርም ፤ በእርግጥም ተሸብሯል ። [1]

“ሳልሣ ጦርነትም እርቅም የማይፈልግ ነው ። የዋናው ጦርነት ዕለት አንድ የመድፍ ጥይት ሳይተኮስ በፈረስ አመለጠ” ያሉትም የሚመስል ነው ። ሳልሳ ጦርነቱን ተቃውሞ እንደነበር ከድሉ በኋላ በ፲፭ኛው ቀን ለእናቱ በጻፈው ደብዳቤ ፣

> ውድ እናቴ ፣ በጦርነት ስለሞቱብን ኢጣልያኖች አቀባበር እና ስለሰላም ውለታ ለመዋዋል ተስፋ አድርጌ ይኸው ወደ ዓድዋ መሔዴ ነው . . . በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የተደረገውን ሁኔታ ልዘረዝ ርላችሁ አልችልም ። ይህ የእብደት ጦርነት እንዲቀር በማናቸውም ኃይሌ ታግዬ ነበር . . . ዳሩ ግን ለመታገል ብቻዬን በመሆኔ ጄኔራሉ አገረ ገዥውን (ባራቲዬሪን) ገፋፍተው ይኸን የመሰለውን አደገኛ ሥራ እንዲፈጽም አደረጉት . . . 2

ሲል ያመለክታል ።

1 Sul Campo di Adua—Ximenes, P.5

2 Tomaso Salsa,E. Canevari . . . ,PP. 295—296.





ጄኔራል ባልዲሠራ

ኢጣሊያ በአፍሪካ ከሚለው መጽሐፍ

ሔዶ ለባራቲዬሪ ነግሮ የጦር ባንዲራ አስተከለ ። ኋላም በየካቲት 23 ቀን የመጨረሻው ጦርነት የሆነ ጊዜ አንድ መድፍ ሳይተኮስ ፣ የዐሥር ነፍጥ ተኩስ ሳይሰማ በፈረስ ሸሽቶ አዲኳላ ገብቶ አደረ ። ይኸንንም በፈረስ ማምለጡን የነገረን እርሱ ራሱ ነው ” ።

ብለዋል ።

በዚህ አነጋገር ግራዝማች ዮሴፍ ፣ “ንጉሠ ነገሥቱ በእንትጮ አልፈው ደብረ ዳሞ አጠገብ ሰፍረው የነበረ ጊዜ ከመረብ ጀምሮ እስከ ምጥዋ ድረስ ተሸብሮ ነበር” ያሉት ትክክለኛ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት እያመለጡ ከመረብ ባሻገር የሔዱ የኢጣልያ ዘማቾች ሁሉ፣ የጦር ጦርነ ቱን ብርታትና የኢጣልያኖቹን እልቂት ፣ የኢትዮጵያን ወታደር ጉብዝና እያጋነኑ በመናገራቸው ከነርሱ የሰማው ሁሉ ልቡ እንደሚሸበር አይጠረጠርም ፤ በእርግጥም ተሸብሯል ። [1]

“ሳልሣ ጦርነትም እርቅም የማይፈልግ ነው ። የዋናው ጦርነት ዕለት አንድ የመድፍ ጥይት ሳይተኮስ በፈረስ አመለጠ” ያሉትም የሚመስል ነው ። ሳልሳ ጦርነቱን ተቃውሞ እንደነበር ከድሉ በኋላ በ፮ኛው ቀን ለእናቱ በጻፈው ደብዳቤ ፣

> ውድ እናቴ ፣ በጦርነት ስለሞቱብን ኢጣልያኖች አቀባበር እና ስለሰላም ውለታ ለመዋዋል ተስፋ አድርጌ ይኸው ወደ ዓድዋ መሔዴ ነው . . . በመጋቢት 1 ቀን (የካቲት 23) የተደረገውን ሁኔታ ልዘረዝ ርላችሁ አልችልም ። ይህ የእብደት ጦርነት እንዲቀር በማናቸውም ኃይሌ ታግዬ ነበር . . . ዳሩ ግን ለመታገል ብቻዬን በመሆኔ ጄኔራ ሎቹ አገረ ገዥውን (ባራቲዬሪን) ገፋፍተው ይኸን የመሰለውን አደ ገኛ ሥራ እንዲፈጽም አደረጉት . . . 2

ሲል ያመለክታል ።

1 Sul Campo di Adua—Ximenes, P.5

2 Tomaso Salsa,E. Canevari . . . ,PP. 295—296.





ጄኔራል ባልዲሠራ

ኢጣሊያ በአፍሪካ ከሚለው መጽሐፍ

# ምዕራፍ ዐርባ ሰባት

## የዓድዋ ድል በኢጣልያንና በአውሮፓ ተሰምቶ ያደረሰው ስሜትና ረብሻ

የኢጣልያ መንግሥት ፣ በውጭ የእንግሊዝንና የጀርመንን መንግሥታት ድጋፍ እንዳገኘና በውስጥ አስተዳደሩ ደግሞ ፣ በቀኝና በግራ ክንፍ የተከፋፈሉ ሁለት የፖለቲካ ቡድኖች መኖራቸውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። የግራው ክንፍ በሶሺያሊስትነቱ ቅኝ አገር ይቅርብን ሲል ፣ የቀኙ ክፍል ንጉሡንና መሳፍንቱን ፣ ባላባቶቹንና ሀብታሞቹን ጨምሮ እንደ ሌሎቹ የአውሮፓ መንግሥታት በአፍሪካ ቅኝ አገር ፈጥረን ኢጣልያን ኃያል እናድርጋት የሚል ነው ። በዚህ በተለያየ ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች በምክር ቤት ሁል ጊዜ የተከራከሩበትን ሁኔታም ባለፈው ጠቅሰናል ።

በግናቸውም ረገድ ፣ ከላይ ንጉሡ እየደገፈ የቀኞቹ የምክር ቤት አባሎች የድምፅ ብልጫ እያገኙ ቅኝ አገር ለማግኘት በጄኔራል ካርሎ—ዠኒ ፣ በጄኔራል ሳንግርሳኖና በጄኔራል ባልዲሠራ መሪነት የኢጣልያ ወታደር እ.ኤ.አ. በ1885—87 ዓ.ም. ምፕዋ ተራግፎ በየጊዜው አካባቢውን ለመውረር የበቃው በዚሁ ምክንያት ነው ። ወደ ዚህም ለጦር ነትም ላገዛዝም የሚላኩት ጄኔራሎች ባራቲዬሪ ጭምር ሁሉም ከቀኝ ክፍል ይኸው ማለት የቅኝ አገርን ፍላጎት ከሚደግፉት ወገኖች እየተመረጡ ነው ።

የኢጣልያ ጦር ፣ በኮአቲትና በሰንዓፌ ላይ ያገኘው ድል አደፋፍሮት ወደፊት ገሥግሦ አላጌ የመሸገ ጊዜ እ.ኤ.አ. በ1895 ታኅሣሥ 3 ቀን ጉዳዩ ለምክር ቤት ቀረበ ። ከሬፑብሊክ (ሶሺያሊስት) ወገን የሆነው ኢምብሪያኒ የሚባለው ፣ "እንደ አውራ ድመቶች ጨዋታ ክሪስፒ የሚያስከትለውን መዘዝ ሳያመዛዝን ዝም ብሎ እውር ጭፍ ትን ወደፊት ይገሠግሣል" ብሎ በወቀሰ ጊዜ ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ፣ "የቅኝ አገራችን ሥራ በደንብ ይራመዳል፣ ልማቱም ይስፋፋል ፣ ሰላሙም ተረጋግጧል" በሚል መልስ ከእውነት የራቀ አባባል ሰጥቷል ። ክርስፒም ቀጥሎ ፣ "እንደ አገራችን ያለ ታላቅ መንግሥት ፣ ትን ንሽ ጦርነት ቢያደርግና ለዚህም ወጭ ቢሰጥ መታሰብ የለበትም"

በሚል አነጋገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ ሰጥቶአል ። ለማናቸውም "የርሱን አመራር የሚደግፉና የማይደግፉ ይታወቁ" በተባለበት ጊዜ ሙራቶሪ የሚባለው ሶሺያሊስት ፣ "መንግሥት ይለወጥ" የሚል አሳብ (ሞሲዮን ደ ሳንሱር) አቅርቦ ለነበረው ከምክር ቤቱ አባሎች 131 ተቃዋሚ 267 ደጋፊ ስላገኘ ፣ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ የወረራ ሥራውን በደንብ ይቀጥል ዘንድ ተፈቀደለት ። ምክር ቤቱ ይኸን በወሰነ በስድስተኛው ቀን የአባጌ ውድቀት ፣ ከዚያም የመቀሌው መሸነፍ ቢሰማም ሁልጊዜ በቀኙ ክፍል ድጋፍ የተነጣ ክሪስፒ ከነአጋሮቹ ሊወድቅ አልቻለም [1] ነበር ። ክሪስፒንና አጋሮቹን ሊጥል የቻለው ይህ ያሁኑ የዓድዋ ጦርነት ብቻ ነው ። ይኸውም የዓድዋ መደምደሚያ ድል ለቀኞቹ ውድቀት ፣ ለግራዎቹ ማንሠራራት ምክንያት ሆኗል ።

ከዓድዋ የጦር ግንባር የሸሸው ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ የክሪስፒ የግል ወዳጅና የፖለቲካ ጓደኛው ፣ በጠቅላይ ጦር አዛዥነቱ ዓድዋ ላይ ድል እንደ ተመታ ፣ በሦስተኛው ቀን ለርሱና ለወገኖቹ መራራ የሆነውን የመሸነፍ ወሬ ለኢጣልያ መንግሥት በቴሌግራም ማስታወቅ ግዴታ ሆነበት ። ሲያስታውቅም ራሱ የነበረበትን የጦር ግንባር ሁኔታ፣ በምን አቅጣጫና አኳኋን ሌሎቹ ጄኔራሎች ጦርነቱን እንደ ጀመሩ ገልጾአል ። ነገር ግን ፣ ራሱ ከመከበብና ከመማረክ ለመዳን ሲል ስለ ሸሸና የሦስቱን ጄኔራሎች የዳቦርሚዳን ፣ የአሪሞንዲንና የአልቤርቶኒን ፍጻሜ ስለማያውቅ መግለጫው ከዚህ እንደሚከተለው ደበስበስ ያለ ነበር ።

> ቅዳሜ ዓድዋ ያለውን የሸዋ ጦር እንዲወጉ ጦሩን ከሦስት ላይ ከፍዬ አንዱን ተጠባባቂ አድርጌ እንዲዋጉ አዘዝሁ . . .የግራው ጦር ወደፊት ቀድሞ መቸገሩን ስለሰማሁ የዳቦርሚዳ ጦር እንዲረዳ ትእዛዝ አስተላለፍሁ . . . በዓድዋ በኩል ጦርነቱ ተጧጡፎ ነበር ።. . .በሌላውም በኩል በድፍረት ወደፊት እየተኰጐደጐዱ የሚዋጉትን የጠላት ወታደሮች ለማገድ ስለ አልተቻለ ሁሉም ሊበላሽ ቻለ . . . ከዚያ ወደተነሣንበት ወደ ማውሪያና ወደ ሰሜን ሁሉም ፊቱን መልሶ ሰፊ መተላለፊያ እየፈለገ ሔደ . . . ከኔም ጋር ኤሌናና ቫሌንዛኖ ወደ አዲቀይህ መጥተዋል . . . የዳቦርሚዳ ወሬ የለኝም ። የአሪሞንዲንና የአልቤርቶኒን ሁኔታም አላውቅም ። ወሬውም የተለያየ ነው . . . ስለመፍረሳችን አደገኛ ሁኔታም የማቀርበው አሳብ የለኝም ። የተዋጉትን የነጭ ወታደሮች እንደገና አዘጋጅቶ ለማዋጋት ግን አይቻልም ።
>
> የጥቁሩም ወታደር የበለጠ ተዘበራርቋል ፣ ሞራላቸው እንደነጮቹ ተበጥብጧል ። በዚህ ፈንታ የጠላቶቻችንና የሽፍቶቹ ሞራል ከፍ

1 Adua, E. Bellavita,P. 227



> ብሏል ። የአዲግራት ምሽግ በማይሸነፉ ሽፍቶች ስለተከበበ ምሽጉን ለቀው እንዲወጡ ማዘዝ የሚቻል አይመስለኝም ። ዛሬ ሴሊቴን ወደ ሰገነይቲና ወደ አሥመራ እሔዳለሁ ። በዚሁ ጊዜ ነገ ጧት አሥመራ የሚገባው ላምቤርቲ የቅኙን አገር አስተዳደር ይዞ ከመንግሥቱ ጋር ይጻጻፋል ።

ባራቲዬሪ [1]

በበኩሉ ይኸው የርሱ ምክትል ጄኔራል ላምቤርቲ ከባራቲዬሪ በፊት እ.ኤ.አ. በመጋቢት 2 ቀን ይኸንኑ የመሸነፍ ወሬ ለጦር ሚኒስትሩ አስተላልፏል ። በዚህ ጊዜ ሌተና ጄኔራል ባልዲሠራ ከሮማ ባራቲዬሪን ለመተካት ተሾሞ ሲመጣ በዓድዋ በኢጣልያ ጦር ላይ የደረሰውን አደጋ አያውቅም ነበር ። ወሬውን የሰማው የዓድዋ ጦርነት በሆነ በአራተኛው ቀን ምጥዋ የገባለት ነው ። እንደዚሁም የባልዲሠራን በርሱ እግር ተሾሞ ምጥዋ መግባቱን ባራቲዬሪ በትክክል ያወቀ አይመስልም ። የሆነ ሆኖ ፣ በዓድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ አሸናፊነት የኢጣልያ ተሸናፊነት በቅድሚያ ከላምቤርቲ ቴሌግራም የተላለፈውን ወሬ የስቴፋኒ የወሬ ወኪል በነዛው ጊዜ በመላው አውሮፓና ዓለም ትልቅ ያልታሰበ ቦምብ የፈነዳ ያህል መገረምን ፣ በኢጣልያ አገር ታላቅ ድንጋጤንና መሸበርን አፈራ ። በተለይ የዚህ የጦርነቱ አደጋ የሚመለከተው የቅኝ ግዛት አጥብቀው በመፈለግ የታወቁትን የመንግሥቱ መሪዎች የነበሩትን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ፍራንቼስኮ ክሪስፒን ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ብላንን ፣ የጦር ሚኒስትሩን ሞቼኒን የገንዘብ ሚኒስትሩን ሶኒኖንና መሰሎቻቸውን ስለሆነ ፣ ኃፍረቱ ሐዘኑና ድንጋጤው በተለይ በነዚህ ላይ በርከቶ የሚሆኑትን አሳጥቷቸው ነበር ። በዚህም ጊዜ የግራ ክፍሎች "ያልነው ደረሰ" በማለት ሐዘን የተደባለቀበት ደስታ ሲሰማቸው እነዚያ ራሳቸውን ዘቅዝቀው መደበቅ ግዴታቸው ሆኖ ነበር ።

ወሬው በየከተማውና በየባላገሩ በተሰማ ቁጥር ነጋዴው ሱቁን እየዘጋ ፣ ገበሬውም እርሻውን እየተወ ፣ ጥበበኛውም ከምድብ ሥራው እየወጣ በሩጫ ወሬ ወደሚገኝበት ሥፍራ እየሔደ ፣ አባትና እናት የልጆቻቸውን ፣ ሚስቶች የባሎቻቸውን ሞትና ደህንነት ለመጠየቅ እየተርገበገቡ ሲሸቀዳደሙ በየመንገዱና በየአደባባዩ ፣ "ወይ ልጄ! ወይ ባሌ!" የሚሉት ዋይታና ለቅሶ ይሰማ ነበር ። አንዳንዶቹ ጠና ያሉት እንደ ማበድ እያሉ በግድ እየተያዙ ታሰሩ ። አንድ ልጅዋ ባራተኛው ባታዮ ጦር ውስጥ የዘመተባት ሴት ያራተኛው ባታዮ ጦር ምንም አል ተረፈም የሚሉ ወሬ እንደ ሰማች ልበ በሽተኛ ነበረችና ወዲያው

1 Memoire d' Afrique P. 393

የልዒ ትርታ ቆሞ ሞተች ።[1] ከዓድዋ ቀደም ብሎ ከኢጣልያ ወታደሩ
እየተመለመለ በሚላክበት ጊዜ በሚላኩት ወታደሮችና በሸኝዎቹ
ልብ የነበረው ደስታ ካሁኑ ሐዘንና ለቅሶ ጋር ሲመዛዘን ነገሩ
የተለያየ ነው ። እነዚያው ጣልያኖች የዚያን ጊዜ የደስታቸውን ዋጋ
አሁን ከልክ ያለፈ በማዘን የበለጠ ሲከፍሉ ታዩ ። የፊተኛው የደ
ስታው መሠረት ፣ "የኛን ጦር አንድ የጥቁር ጦር አይደፍረውም"
በሚሉ እምነት ነበር ። አሁን ግን ፣ በናቁት ሕዝብ ተሸንፈው ያልታ
ሰበው ሲደርስ ሐዘኑን የበለጠ ጽኑ አደረገው ።

ከፍተኛውና መካከለኛው ሕዝብ ይኸን የመሰለ ሐዘንና ዋይታ
ሲደርስበት ፣ የወጣቶቹና የግራ ክፍሎች ሠራተኞች ሞልሚንቲ
ፖምፒዎ ዠራርዶ በሚባል የሶሺያሊስት አግካሪ (ዲፒቲ) እየተመሩ
በስድስት መቶና በሰባት መቶ እየተከፈሉ በሮማ "ሆ!" እያሉ እንዳ
ንድ ጊዜም የቀኝ ክንፎችን ለማናደድ ፣ "ምኒልክ ሕያው ይሁን"
እያሉ በጩኸት ሲዞሩ ከተማው የመሸበር መልክ ያዘ ። ነጋዴውና
የከተማው ሰው እየፈራ በሩን እየዘጋ ተደበቀ ። በሌሎችም ከተሞች
የተዛመተ መጠን ግርግሩና ግጭቱ በርክቶ ነበር ።[2] በሚላኖ
ወሬው በተዛመተ መጠን ግርግሩና ግጭቱ በርክቶ ነበር ።
በግራና በቀኝ ክንፎች መካከል ግጭት ተፈጥሮ አንድ ሰው ሲሞት
ዐሥራ አራት ቆሰሉ ። በፓቪያ ያሉ የባቡር ሠራተኞች ሁለተኛ የኢጣ
ልያ ወታደር ወደ ኢትዮጵያ እንዳይላክ ሐዲድ ያፈራርሱ ጀመር ።

ከሁሉ ከተሞች ግርግሩ የነበረው በዋናው ከተማ በሮማ ነበር ።
በዚያም ወጣቶቹ በጩኸት ትእይንት በሚያደርጉበት ጊዜ አዲስካ
ልኬ የሚባለው መስፍን በትሪቶኒ አውራ ጉዳና በጋሪ ተቀምጦ ሲያ
ልፍ አግኝተው በፊቱ ላይ ጭቃ እየረጩ ከበቡት ። ወዲያውም "ምኒ
ልክ ሕያው ይሁን" በል እያሉ አስፈራሩት ። እርሱም "ኢጣልያዊ
ስለሆንኩ ኢጣልያ ሕያው ትሁን እላለሁ እንጂ ምኒልክ ሕያው ይሁን
አልልም" እያለ ሲጨቃጨቅ ፣ በመካከሉ የንጉሡ ዘበኞች (ካራቢኒሬ
ዎች) ደርሰው በግድ አስጥለውት በጋሪው ለማምለጥ ቻለ ። በዚሁ ጊዜ
የመሸነፉ መዋረድ እንዶ አዳር ቆሞ የሚመለከተውን በጣም ያስገረ
መውና ያነደደው ፣ "ክሪስፒ ይውደቅ ፣ ምኒልክ ሕያው ይሁን" የሚ
ለው ጩኸት በወጣቶቹ ዘንድ መሰማት ነው ።

"ምኒልክ ሕያው ይሁን" ብለው ወጣቶቹ እየጮሁ መስፍኑም
እንዲጮህ ለማስገደድ የሞከሩበት ምክንያት የጦርነቱን አጀማመር
ከሥር ጀምረው በራሳቸው በሶሺያሊስት ጋዜጦች ይከታተሉ የነበሩት

1 La Prima Guerra d' Africa , R. Battaglia, PP. 793—800.

2 Douze ans en Abyssinie . . . PP. 528-530; Adua, Belavitta P. 394.



በተለይ የግራ ክንፎቹ ፣ የኢጣልያን መንግሥት አጥቂነትና የኢትዮጵ
ያን ተከላካይነት ፣ ያዩ ምኒልክን ያላሠለሰ እርቅና ሰላም ፈላጊነት ፣
የክሪስፒንና የአጋሮቹን አብሪትና ተጋፊነት በሰፊው ተረድተው በት
ችት ጊዜ ሁሉ ፣ "ምኒልክ ጥሩ ክርስቲያን ክርስፒ ግን አረመኔ ነው"
እያሉ ያትቱ ዠመር ። በዚህም ላይ በአላጌ የሞቱት የኢጣልያ ወራሪ
የጦር መኰንኖች በክብር መቀበራቸውን ፣ ኮሎኔል ጋልያኖ ከነጦሩ
ብዙ ደም አፍሶ ሞት ሲገባው ሳለ ፣ ከመቀሌ በሰላም ተሸኝቶ ወደ
አዲግራት ሔዶ ከወገኖቹ መደባለቁን ያውቁ ስለነበረ ፣ በዚህ ዓይነት
የተገፋው የኢትዮጵያ ጦር ማሸነፉ የሚገባ ነው በማለትና አላይ እን
ዳልነው ፣ "ምኒልክ ሕያው ይሁን! ምኒልክ ክርስቲያን፣ ክርስፒ አረመኔ"
እያሉ በመጮህ የፖለቲካ ባላጋራዎቻቸውን በንዴት ለማብሸቅ ነው ።
ከንጉሡ ጀምሮ መሳፍንቱ ሁሉ የቅኝ አገዛዙን የሚደግፉ ፣ "እኛም
ሔደን እንዋጋ" እያሉ የሚጋበዙ ነበሩባቸው ። ወጣቶች በዚህ ቀን
አዲስካልኬ የሚባለውን መስፍን ጭቃ እየረጩ ያጉላሉበት ምክን
ያትም ጠቅላይ ሚኒስትሩን ክሪስፒን በመደጋገፍ አገሪቱን እዚህ
አደጋ ላይ ያደረሱት የበለጠ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባሎች ጭምር
ናቸው በማለት ነው ።

እነዚሁ ወጣቶችና እንደዚሁም ወደ ኢትዮጵያ ለጦርነት የመ
ጡት የሹማምንቱም ፣ የወታደሩም ቤተሰቦች በጠቅላላው በዚህ ጦርነት
ያገራቸው ውርደት የተሰማቸው ሁሉ ተሰብስበው ፣ "አንድ ድል አን
ጡብቃለን" ወይም "አንድ የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚደመድም ድል
ሳታገኝ እርቅ የለም" እያለ ባራቲዬሪን በቴሌግራም ያጣድፍ ወደ
ነበረው ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ክሪስፒ ቤት ሔደው እያወኩ
የስድብ ናዳ በማውረድ ግማሹም ደንጊያ እየወረወረ ቤቱን በመደብ
ደብ አስቸገሩት ። በእንደዚያ ያለ መከራ ላይ ሳያስበው የወደቀው
ፍራንቼስኮ ክሪስፒ በፖሊስ ኃይል ተከላካይነት ትእይንተ ሕዝብ
አድራጊዎቹ ከተወገዱለት በኋላ ፣ "የወታደርዎን ደም ጊዜ ጠብቀው
ይበቀሉለት" የሚል ቃል ለንጉሡ ጽፎ ከጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ተሰና
በተ ።

የዓድዋ ድል ፣ በኢጣልያ አገር ይኸን የመሰለ ሽብር ሲፈጥር
በሌላው ዓለም የሰጠው ስሜት የተለያየ ነው ። የድሉ ወሬ በፈረንሣይ
አገር ሲሰማ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ በቀለምና በዘር አንድ
ነት ፣ የተነሣ ወይም በፖለቲካ ዝንባሌ ምክንያት የነጩ ዘር ወይም
የቀኙ ክፍል ጥቃት ቅር ያላቸው ባይጠፉም ፣ አብዛኛው የፈረንሣይ
ሕዝብና በተለይ የመንግሥቱ መሪዎች በደስታ ተቀብለውታል ።
ጣልያኖቹ ስሜን ኢትዮጵያ ከገቡ ጀምሮ የፈረንሳይን ወኪሎችና
ዜጎች ሰበብ አስባብ እየፈለጉ ያስቸግሩ ነበር ። በዚሁ ምክንያት

ባራቲዬሪ ኤርትራ ብሎ በያዘው ግዛት ይገኝ የነበረውን የፈረንሳይን የላ
ዛሪስት ሚሲዮን እ.ኤ.አ. ጥር 22 ቀን 1895 ዓ.ም. በትእዛዝ ካገር
እንዲወጡ ማድረጉ ይታወሳል ።[1]

በመስኮብ አገር ያለው ስሜት ከዚሁ ከፈረንሣይ ጋር ተመሳሳይ
ነው ። እንዲያውም የመስኮብ መንግሥት ወዳጅነቱን ለመግለጽ የቀይ
መስቀል ጓድ ወደ ኢትዮጵያ ልኮ በዓድዋ ጦርነት የቆሰለውን ሁሉ
በማከም ስለረዳ ፣ ምስጋና ከንጉሠ ነገሥቱ ተቀብሏል ። በዚሁ አጸፋ
የጀርመንና የእንግሊዝ መንግሥታት ግን ፣ የዓድዋን ድል የሰሙት
"ይኽ እንደምን ሊሆን ቻለ" በሚል የመገረምና የቁጭት ስሜት ፣
ነው ። በዚሁ ምክንያት የእንግሊዝ ምክር ቤት ተከፍቶ ጉዳዩ
በሚጠናበት ሰሞን የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ጆ
ናትናኤል የሚባለው ስለ ዓድዋ ድልና ስለ ኢጣልያኖች መሸነፍ
ንግግር ሲያደርግ ፣ "...የሐበሾች ማሸነፍ የኢጣልያንን ጦር መፍረስ
ብቻ ሳይሆን ለግብፅ አደገኛና በአፍሪካ ላሉው የአውሮፓ አቅዋም
አሥጊ ነው ። ስለዚህ ወደፊት ገፍቶ አደጋውን ማቆም የተከበበውንም
ከሰላን አድኖ የግብፅን ወሰን በደንብ መከላከል ያስፈልጋል...
ኢጣልያም ለባንዲራዋ ክብር ስትል ፣ እንደገና ተዋግታ የመሸነፍ
ብድሯን እንደምትመልስ እተማመናለሁ..." የሚል ቃል ይገኝ
በታል ። ይኽንንም የመጨረሻውን የድል በቀል በተናገረ ጊዜ የትልቁ
ምክር ቤት አባሎች አሳቡን በጭብጨባ ተቀበሉት ።[2]

ሔንሪ ስታንሌይ የሚባለው እንግሊዛዊ ፣ ስለ ኢትዮጵያና ስለ
ዓድዋ ድል አንድ የኢጣልያ መጽሔት አዘጋጅ ለጠየቀው መልስ
ሲሰጥ ፣ "...ኢጣልያኖች የደረሰባቸው ውድቀት አሳዛኝ ነው ። በመ
ላው የእንግሊዝ አገር መገረምን አትርፏል ። ከሰላን በእንዴት ያለ
ወታደራዊ ጥበብ የያዘው ባራቲዬሪ አሁን የደረሰበት በትር በራሳችን
እንደ ደረሰብን ቆጥረነዋል..." የሚል ቃል ይገኝበታል ። ከዚሁ አያ
ይዞ "ሥልጡኑ ዓለም ኢጣልያንና በአበሻ አገር ያሉትን የወታደሮቿን
ሁኔታ አተኩሮ ይመለከታል ። ያገሪቱ ክብር ስለተነካ ኢጣልያ በምት
ወስደው እርምጃ ክብሯ ወይም መዘበራረቋ ሊታይ ይችላል...የባ
ራቲዬሪ ድል መሆን ቢያሳዝነንም ፣ መጨረሻው አይደለም ...ተስፋ
እንደ ምናደርገው በብልሃቱ አሻሽሎ መሸነፍን ለምኒልክ መልሶ ሊሰ
ጠው ይችላል..."[3] ብሏል ።

1 Adua, Bellavita ,P. 167; Nota Al, Chap. XIV
2 Abyssinia ,E. Scarfoglio . . . PP.263-264
3 Precursori dell'Impero, R. Truffi, P. 195.
La Prima Guerra D, Africa-R. Bataglia PP. 705-710



ከሁሉ የበለጠ የኢጣልያ ተሸናፊነትና የኢትዮጵያ አሸናፊነት
በመላው ዓለም ፣ በገዥዎችና በተገዥዎች ዘንድ የሚያስከትለውን
የፖለቲካና ያገዛዝ ውዝግብ በትክክል የተመለከተ የሎንዶን ታይምስ
ጋዜጣን የሚመራው ጸሐፊ ነው ። እርሱም እንደዚህ ሲል አትቷል ።

"...የኢጣልያኖች በምኒልክ መሸነፍ በታሪክ ሲታወስ የሚ
ኖር ነው ። ይኸም ድል አድራጊነት እስከዛሬ አረመኔ እየተባለ በአው
ሮፖች ይናቅ የነበረውን የአፍሪካ መንፈስ የሚቀሰቅስ ነው ።"

ካለ በኋላ ከዚሁ አያይዞ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔ አውስቶ ፤

...ኢጣልያኖች ከሌሎቹ አውሮፓውያን ዝግንነትም አያያዝም
አንሷቸው አይደለም ። ወደ አፍሪካ ቅኝ አገር ለማግኘት ፊታቸውን
ባዞሩበት ሰዓት በቀላል ሊያዝና ሊገዛ የሚችለው ክፍል ቀደም ብሎ ስለ
ተያዘ ወደ አልተያዘው (ወደ አስቸጋሪው) ተመለከቱ ። ኢጣልያኖች
ንጉሡን የአሳመኑ መስሏቸው ሲታለሉ እርሱ ግን ፣ (ምኒልክ) በመጣ
ሪያ እየተዘጋጀ የአጸፋውን ኃይል አሳያቸው ። የርሱም ድል ማድረግ
የመላ አፍሪካ ድል ነው ። ይኸም ዓይነቱ አስተያየት ወደፊት እያየለ
ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነው ። በነዚህ አገሮች (አፍሪካውያን) ዘንድ
ወሬው በነፋስ ክንፍ በረሃውን ሁሉ አቋርጦ በፍጥነት የሚሮጥ
ስለሆነ ፣ ከጫፍ እስከ ጫፍ አሁንም ታውቋል ። ወደፊትም አፍሪካ
አውሮፓን ማሸነፉ ስለታወቀ ፣ ቁጥሩ ይኽን ያህል ተብሎ ሊገመት
ለማይችለው የአፍሪካ ሕዝብ የሕይወት ንቃትና የመከላከል ስሜት
ያሳድራል ። ስለዚህ ጉዳዩ አደገኛ ስለሆነ በኢጣልያኖች መሸነፍ
ተደሳቾች መሆን ምቹ አይደለም ። ይኸ መሸነፍ የሁላችንና የሌሎ
ችም ጭምር መሸነፍ ነው ። የሥልጣኔ መሸነፍም አይደለም ፤ የቅኝ
አገር ገዥ የሆነችውና የነገይቱም አውሮፓ መሸነፍ ነው..."[1]

ጸሐፊው "መደሰት የለብንም ። የሁሉም አውሮፓ ውድቀት ነው"
የሚለው ፣ በኢትዮጵያ ማሸነፍ በኢጣልያኖች መሸነፍ ፈረንሳዮችና
መስኮቦች መጠነኛ ደስታቸውን በየጋዜጣው ስለገለጡ ለማስጠንቀቅ
የሰነዘረው ነው ። መላው አውሮፓ በአንድነት ጉዳዩን በጽሞና አጢኖ
ወዲያውኑ ይህ የዓድዋ ድል በአፍሪካና በሌላውም ኋላቀር አገር ላይ ደ
ረሰው የኩራትና የትምክህት ስሜት ካሁኑ መፍትሔውን እንዲያበጅ
የሚጋብዝ ነው ።

ይኸ ሁሉ በጠቅላላው የሚያሳየን እንደ ስታንለይ አባባል ፣ "ኢጣ
ልያ በጥቁሮች ሐበሾች በመሸነፍ ኃፍረት ተከናንባ እንደዚሁ አትቀ
ርም ። ሌላ ቁጥሩ የበረከተ ጦር ልካ እንደገና ተዋግታ ክብሯን

1. L'Italia in Africa, Serie Storico Militare, Vol 1, Tome II, A Vitale ,PP. 122-123.

ትመልሳለች” የሚል ስሜት እንዳላቸው እንገነዘባለን ። የእንግሊዞችም ዋና ሥጋታቸው የኢትዮጵያ ያሸናፊነት ዝና በቅኝ አገሮቻቸው በአፍሪካና በተለይም በግብፅ አለተጋብቶ ያገዛዛቸውን እቅዋም እንዳያናጋባቸው ነው ።

በዚሁ ጉን ፣ የጀርመን መንግሥት ከኢጣልያ ጋር ባለው የስምምነት ውል ጋዜጦቹና ባለሥልጣኖቹ የኢጣልያን መሸነፍ በሐዘንና በንዴት እንደ ተቀበሉት የበለጠ በዚህ የመሸነፍ ውድቀት ለማጽናናትና የወዳጅነቱን ስሜት ለመግለጽ ራሱ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ዊልሄም ሮማ ድረስ ሔዶ የኢጣልያን ንጉሥ ጐበኘ ።[1]

እውነትም በመካከለኛው ምሥራቅና በግብፅ አገር ዓረቦቹ የኢትዮጵያን አሸናፊነት በደስታ እንደ ተቀበሉት ይታያል ። በዚሁ በድሉ ሰሞን የኢጣልያ መርከብ የዓድዋ ድል ወሬው ሳይሰማ ወታደር ጭና ወደ ምጥዋ ለመድረስ ፖርትሳይድ የቆመ ጊዜ በደረሰው የመሸነፍ አደጋ ምክንያት ወታደሩ ከመርከብ ወርዶ ፖርትሳይድ እንዳይታይ ተከልክሎ ነበር ። የጦር መኰንኖቹ ግን ፣ በፈቃዳቸው ወርደው ወዲያና ወዲህ ሲሉ በዚያ የነበሩ የፈረንሣይና የመስኮብ ፣ የግሪክና የሕንድ ተወላጆች እያዩ አፌዘውባቸዋል ። ዓረቦቹም ጠጋ እያሉ ፣ “ጣልያን አይረባም” እያሉ ይጮሁባቸው እንደነበረ ተመዝግቦ ይገኛል ።[2] የዓድዋ ድል አድራጊነት በተለይ በኢትዮጵያውያን ዠግንነት የተፈጸመ ቢሆንም የድሉን ደስታ የቅኝ አገዛዝ ቀንበር የተጫነውም ፣ ገና ያልተጫነውም የእስያም ፣ የአፍሪካም ሕዝብ ተካፍሎታል ማለት ይችላል ። በዓድዋ የምኒልክ አሸናፊነት ፣ “አውሮፓዊ በዕውቀት የገፋ ፣ በትምህርት የተራቀቀ ፣ በሀብት የለማ ስለሆነ በጥቁርና በብጫ ሕዝብ ፈጽሞ ሊሸነፍ አይችልም” የሚባለውን የቆየውን እምነትና አባባል ስለ አስተባበለው የቅኝ አገር ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ በየትኛውም ክፍለ አሀጉር ያለው የነጭ ዘር በነገሩ ታምበታል ። በአውሮፓም ድጋፍ ኢጣልያ በቶሎ ይኸን ውርደት መበቀል እንዳለባት ያብዛኛው አውሮፓዊ ምኞት ነበር ።

1 L' Italia in Africa, A Del Boca, P. 720.
2 Sul Campo di Adua, Ximenes, P. 2 L'Italia in Africa ,A. Del Boca, PP.694—701.



# ምዕራፍ ዐርባ ስምንት

## የጄኔራል ባራቲዬሪ ፍጻሜ

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አፍሪካ የመጣው እ.ኤ.አ. በ1887 ዓ.ም. ከጄኔራል ሳን ማርሳኖ ጋር ነው ። ወደ አፍሪካ እንደተሻገረ በዚሁ በሳን ማርሳኖ ሥር ሲሠራ ቆየ ። በሳን ማርሳኖ እግር ጄኔራል ጄኒ ባልዲሠራ ፣ ከርሱም ቀጥሎ ጄኔራል አሬሮ ፣ ከአሬሮም ጋንዶልፊ ተከታትለው በተሾሙበት ጊዜ ፣ ባራቲዬሪ ወደ ኢጣልያም አገር እየሔደና እየመጣ በነዚህ ሥር ሆኖ በኰሎኔልነት ማዕረግ በብዙ ክፍል ሲያገለግል ኖረ ። በኋላም በ1892 ዓ.ም. ጄኔራል ጋንዶልፊ ተሽሮ በርሱ እግር ኤርትራ በሚል ሥያሜ የያዙትን የሰሜን ኢትዮጵያን ክፍል ጠቅላይ ገዥነት ተሾመ ።

በማናቸውም ረገድ እርሱም እንደ ሥራ ጓደኞቹ ለድል አድራጊነቱ በመተማመን በጦርነቱ ዋዜማ ሮማ ላለው ወዳጁ ለጄኔራል ዳልቬርሜ በሚጽፍለት ደብዳቤ ውስጥ ፣ “ለሁሉም ተዘጋጅቻለሁ በመጋቢት ወር ላይ ትግሬን ለመውረር የሚያስችለኝ ኃይል አገኛለሁ” ይል ነበር ። በሌላው ደብዳቤ ደግሞ እውነቱን ደበቅበቅ እያደረገ እርሱን ጦርነት እያማረውና የሚዋጋው እንዳጣ ያህል በመቁጠር ፣ “...ጠላት ለመመከት እንዲገደድ አዘንግቼ ለመውጋት እስባለሁ... ለመዋጋትም ተስፋ አለኝ” ሊያለ ይጽፍ ነበር ።[1]

የዓድዋ ጦርነት በየካቲት 23 ቀን ሲደረግ ሲል ፣ በየካቲት 22 ቀን ማታውኑ ምክር ሲደረግ ግን ጄኔራሎቹ “እንበለው ጠላትን አለበት ድረስ ሔደን ፣ እኛው ፈልገን እንውጋው” ባሉበት ሰዓት እርሱ ፣ “ጠላት ኃይለኛ ነው ምክራችሁ የድፍረት ነው ። ለማንኛውም የጦር ሠራዊታችን ሞራል እንደምን ነው” ያለውን ስናስታውስ ፣ ውሎ አድሮ በቁርጠኛው ቀን ግን እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያን ጦር ከመናቅ እንደ ተቆጠበና በተቻለ ለመጠንቀቅ እንዳሰበ ይታያል ።

ዳሩ ግን ፣ ጦርነት መከፈቱ ግዴታም ውዴታም ሆኖበት ጦርነቱ ተጀምሮ የማንባር ቀደሙ ጦር ከተመታ በኋላ ፣ ከጦርነቱ ላይ እየሸሸ

1 Precursori del'Impero, R. Truffi, P.195.

በላዩ ላይ እየጋለበ የመጣበትን ያገር ተወላጅና የጣልያን ጦር እንደ ገና ልብ ሰጥቶ አቁሞ ለማዋጋት በፈረሱ ላይ እንደሆነ አንድ ጊዜ፣ "ቪቫ ኢታሊያ" ቀጥሎ "ሳቮያ"* ብሎ እየጮኸ በሞከረበት ጊዜ ባንድ ወገን በረኃብና ጥም፣ በሌላ በኩል የሌትና የቀን ጉዞ ድካም፣ በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያውያኑ ቁርጠኛ አወጋግ ያስደነበረው ጦሩ ሊቆምለት ስለአልቻለ በመጨረሻ በሽሽቱ እርሱም ተጋባበት ። እንዲያውም ከአብዛኛው በራሪ የግረኛ ወታደር እርሱና ጥቂት አጃቢ ሹማምንቱ በፈረስ ስለነበሩ ቀድመው አዲ ቀይህ ገብተዋል ።

ባራቲዬሪ፣ ከቅርብ የሥራ ጓደኞቹ ጋር በሚሸሽበት ጊዜ የቀኙ አዝማች ጄኔራል ዳቦርሚዳ ገና በመዋጋት ላይ ስለነበር፣ ፍጻሜውን ለመጠበቅ ያባራሪዎቹ ተጽእኖ አላስቻለውም ። በሽሽቱ ጊዜ እንቅልፍ ካጣ ውሎ አድሮ ነበርና በፈረሱ ላይ እርሱም ሌሎቹም እያንጐላጁ ሲሔዱ፣ መንገድ አሳስተው ወዳላሰቡት አቅጣጫ ርቀው ሔደው ነበር ይባላል ።

እንደዚሁም፣ በዚሁ በሽሽት ጊዜ አንዳንድ ጊዜ ፈረሱን እያስጋለበ ሲሔድ፣ መነጽሩ ከፊቱ ላይ ወድቆ ጠፋ ። ቆም ብሎም እንዳይፈልግ አባራሪዎቹ ስለሚያጣድፉት የዕውር ጭፍኑን ይጋልብ ዠመር ። በዚህም ጊዜ ከጭፍሮቹ አንዱ ቴኔንቴ ማሮዚ "እሾዐ አለ፤ ወደ ቀኝ አሁን ጫካ አለ፤ ወደ ግራ አሁን ራስዎን ዝቅ ያርጉ ወይም ከፍ ያርጉ" እያለ በአጠገቡ ሆኖ ይመራው ነበር ። በዚህ ዓይነት ችግር ከዓድዋ አዲቀይህ፣ ከአዲቀይህ ሰገነይቲ ደርሶ ዐረፍ ባለበት ሰዓት ከጦር መኰንኖቹ አንዱ ቴኔንቴ አሊሳንድሮ ሳፔሊ ቀረብ ብሎ ሊያጽናናው ሲሞክር፣ "...እኔ ከጉዳይ አልገባም፤ ኢጣልያ ግን መበቀሏ አይቀርም"[1] አለ ። ከሰገነይቲ ወደ አሥመራ ሔዶ አዲስ ተሾሞ ከመጣው ከጄኔራል ባልዲሠራ ጋር ከተገናኘ በኋላ ምጥዋ ሲደርስ እግሩ ተጥመለመለ ። ቆሞ መራመድም ስለ አቃተው የሚራመደው በሁለት ሰዎች ተደግፎ ነበር ። ጠጋ ብለው ጋዜጠኞች ለማነጋገር ሲፈልጉ፣ "ዕንቅልፍ ካጣሁ ስምንት ቀን ሆኖኛል" ከማለት በቀር ሊያነጋግራቸው አልቻለም ።[2]

የሆነ ሆኖ፣ ከዚህ በኋላ አሥመራ ላይ በጄኔራል ባራቲዬሪ ለመፍረድ አዲስ ልዩ የጦር ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ. ሐምሌ 14 ቀን 1896 ዓ.ም.

---

* "ቪቫ ኢታሊያ" ማለት 'ኢጣልያ ትኑር' ማለት ነው ። "ሳቮያ" ደግሞ የኢጣልያ ነጋሢዎች የሚጠሩበት የዘራቸውና የትውልዳቸው መደበኛ ሥፍራ ነው ።

1 Memorie d' Africa, A. Sapelli, P.122.

2 La Giornata di Adua, R.Mazzucconi, P. 355.



ተቋቋመ ። ክሱንና ፍርዱን ለመመልከት የተመደቡት አዲስ ከሮማ የመጡት ከፍተኛ የጦር ባለሥልጣኖች ፤

፩ኛ/ ሌተና ጄኔራል ደል ማይኖ ኮንቴ ሊኬኖ... ሊቀመንበር

፪ኛ/ " " ሐሽ ኒኮላ .......... አባል

፫ኛ/ ማዦር ጄኔራል ጋዙሬሊ ፊሊፖ ........ "

፬ኛ/ " " ቢዘስቲ ሉዊጂ ....... "

፭ኛ/ ካባሊዬሬ ራቤራ ሚኬሌ ............ ጸሐፊ

የመንግሥቱ ጠበቃ ፊስካሌ ሚሊታሬ የሚባለው ክሱን በሁለት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ከፍሎ እንደዚህ ሲል መሥርቶታል ።

፩ኛ/ ይቅርታ በማይደረግለት መንገድ እንዲመራው በውስጡ የተመደበለትን ጦር ሠራዊት በማያሸንፍበት አኳኋን መጋቢት 1 ቀን 'የካቲት 23' በጠላት ሠራዊት ፊት ወስዶ አጋፍጦ እንዲሸነፍ አድርጓል ።

፪ኛ/ ከጦርነቱ ሥፍራ በ12 ሰዓት ከ30 ደቂቃ (ስድስት ሰዓት ተኩል) ሸሽቶ በመሔድ ተዋጊውን ሠራዊት ከተሸነፈ በኋላ እስከ መጋቢት 3 ቀን ድረስ ያለምንም አዛዥና ያለምንም መሪ ትእዛዝ አደጋ ላይ ትቶት ሔዷል የሚል ነበር ።

ለዚህ መልስ ራሱ ጄኔራል ባራቲዬሪና ጠበቃው በሰጡት ቃል ፤

፩ኛ/ ጄኔራል በራቲዬሪ ሁኔታው አስፈሪ መሆኑን በመገንዘብ ከአዲግራትም ከሣውሪያም ወደኋላ ጦሩን ይዞ ከመረብ ወዲያ መመለስ ሲያስብ አራቱ አዝማች ጄኔራሎች ወደፊት ገፍተን እንዋጋ ብለው እንዳደፋፈሩት ፤

፪ኛ/ ከኢጣልያ አገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ፣ "እስካሁን ያደረጓቸው ጦርነቶች ወግ የሌላቸው 'Tisi Militare' ናቸው" በማለት በቴሌግራም ወቅሶ የታወቀ ጦርነት ለማድረግ መገፋፋቱን፣

፫ኛ/ አዝማቾቹ ጄኔራሎች የሰጣቸውን ፕላን ሳይከተሉ በየፊናቸው ሔደው ለየብቻ መዋጋታቸውን፣

፬ኛ/ የሸሸበት የአዲቀይህ አቅጣጫ ለተዋጊው ሠራዊት ማናቸውንም ትእዛዝ ለማስተላለፍ የቴሌግራፍና የመላከተኛ ድርጅት ስለሌለ፣ በዚህም ላይ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች በጠቅላላው ጦርነቱን ይፈልጉ እንደነበረ እርሱም በቂ እርዳታ ጠይቆ ሳይሳካለት

መቅረቱን ፡ ምጥዋም ያለው ስንቅ ግለቁን ስለተረዳ ፡ ከመዋጋት በቀር ሌላ ምርጫ እንደሌለው ብዙ የሰነድ ጽሑፍ በማቅረቡና ከሞትም ከምርኮም ፡ ተርፎ የተመለሰው የተጠባባቂው ጦር አዛዥ የነበረው ጄኔራል ኤሌና ከችሎቱ ላይ ቀርቦ የሰጠው የምስክርነት ቃል የርሱን አባባል ስለ ደገፈው ፤

ፍርድ ቤቱ ጠበቃውና ተከሳሹ ከዚህ በላይ ያቀረቡትን መልስ ከመረመረ በኋላ ፡ በጄኔራል ባራቲዬሪ አመራር ጉድለት ፡ ቸልተኝነትና ችሎታ ማጣት ቢኖርበትም ፡ በጠቅላላው ሆን ተብሎ የተፈጸመ የጦርነት ወንጀል አልሠራም ። ስለዚህ ከማንኛውም የጦር አዛዥነት ወርዶ በግሉ ሊኖር ይችላል ተብሎ በነጻነት ተለቀቀ ።[1]

ከዚያም ወዳገሩ ገብቶ የጦርነት ማስታወሻውን ጽፎ ከጨረሰና ካሳተመ በኋላ፣ በተወለደ በ60 ዓመቱ እ.ኤ.አ. በ1901 ዓ.ም. ሞተ ። ይህ ጄኔራል በመጀመሪያ ወቅት የከሰላ አሸናፊ ፡ የኮዓቲትና የሰንዓፌ ድል አድራጊ ተብሎ ከመረብ ምላሽ ወዲያና ወዲህ ሲል ሕዝቡም ፡ ሠራዊቱም በያለበት በሆታና በአክብሮት እየተሰለፈ ፡ ሚሲዮናውያኑ ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ሲቀበሉት ሥልጣናዊ ሕይወቱ በደስታ የተከበበ ነበር ። ባለፈው እንዳነበብነው ፡ ከኮዓቲትና ከሰንዓፌ ድል በኋላ ኢጣልያ አገር የተደረገለትን የክብር አቀባበል ያነበብነውን እንመለስበትም ። ወደዚህ አዱጋ የጣለውም ሲመረመር ያ አሸናፊነትና በዚህ አሸናፊነት ያገኘው ክብር ነው ። እንደ አብዛኛው የጦር መሪ ጄኔራል ኦሬስቴ ባራቲዬሪ ሕይወቱ በክብር ተጀምሮ በሐዘር የተፈጸመ ነው ።

1 Adua, E. Bellavita, PP.394-413; Memoire d'Afrique, PP.531- 540.





በዓድዋ ጦርነት የኢጣሊያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ባራቲዬሪ

ኢታሊያ ኢን አፍሪካ ከሚባለው መጽሐፍ

# ምዕራፍ ዐርባ ዘጠኝ

## በምክር ቤት የተነሣው ሁካታ — በሮማ የመንግሥት ለውጥ — ያዲሱ መንግሥት አዲስ ፖለቲካ—የክሪስፒ ፍጻሜ

በኢጣልያ አገር ክሪስፒ፥ ምንም እንኳን የሥራ ስንብቱን ለንጉሥ ኡምቤርቶ ቢያቀርብ ሹመቱን የሚቀበለው እስኪታወቅ ድረስ እርሱም ሚኒስትሮቹም በጣም የተጠሉ ቢሆኑም፥ በሥፍራቸው እንዲቆዩና የተለመደውን ሥራ እንዲቀጥሉ ተደረገ። በዚህም ጊዜ በዓድዋ መሸነፋቸውን ከሰሙ ወዲህ ቅኝ አገር ይቅርብን በሚሉት በሬፑብሊካኑና ቅኝ አገር ለኢጣልያ ያስፈልጋታል በሚሉት የቀኝ ክንፍ ቡድኖች መካከል ክርክሩ በውጭም በምክር ቤቱም አልበረደም ነበር። ብዙዎቹ የባራቲዬሪ ፍርድ ወደ ሮማ ይምጣና በርሱ ብቻ ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ በክሪስፒና በሚኒስትሮቹም ላይ ይፈረድባቸው የሚሉ ነበሩ።[1]

የቀኙ ክፍሎች ሌተና ዤኔራል ባልዲሠራ ይዞ በሔደው ጦር ላይ በርከት ያለ ጦር ተልኮ እንደገና የበቀል እርምጃ ይወሰድ የሚሉ ነበሩ። ክሪስፒም የዚህኑ ፖለቲካ ወደ ፍጻሜ የሚያደርስ ከራሱ ቡድን ውስጥ የተከበረው ሳራኮ ዡሴፒ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥፍራ እንዲይዝ ለንጉሡ አሳስቦ ነበር። ዳሩ ግን፥ በተደረገው ውይይትና በግራ ክንፎች መቃወም ባሁኑ ጊዜ የቀኝ የፖለቲካ ቡድን አባል የሆነው የርሱ ጠቅላይ ሚኒስትርነት በፍጹም እንደ ማይሆን ተወሰነ።

ከዚህ በኋላ፥ እ.ኤ.አ. በመጋቢት 4 ቀን (የካቲት 27) ምክር ቤቱ ተከፍቶ የምክር ቤት አባሎች ከሌላው ቀን በተሟላ አኳኋን ገብተው ስፍራቸውን ያዙ። ባንድ ወገን የዘማች ቤተ ዘመድ ስድብ፥ በሌላው ወገን የሬፑብሊካኖች ወቀሳ ያደከመው ክሪስፒ፥ የሥራ ጓደኞቹን ሚኒስትሮች እንዳስከተለ ራሱን ቁልቁል ደፍቶ ወደ መሬት እያየ በሐዘን መልክ በምክር ቤት ውስጥ ገብቶ በስፍራው ተቀመጠ።

---

1 Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca, PP. 709. La Prima Guerra d' Africa- R. Bataglia - PP.693 750,

በዚህ ጊዜ ፣ የፊተኛው ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ተነቦ የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ክሪስፒን ለንግግር ጋብዞት ወደ መናገሪያው ሥፍራ ሲወጣ ታላቅ ጸጥታ ሆነ ። ሁሉም ዐይኑን እርሱ ፊት ላይ ሰክቶ ይመለከተው ጀመር ። ወዲያው "ስንብት ጠይቄ ንጉሡም ስንብቴን እንደ ተቀበሉት ለምክር ቤቱ ሳስገነዝብ ክብር ይሰማኛል. . ." የሚለውን ቀዳሚ ቃል እንደ ወረወረ ሃምሳ ከሚሆኑ ከርሱ ወገኖች በቀር በምክር ቤቱ ያሉት በሙሉ ለመመልከት የገባው ጭምር አንድ ጊዜ በኅብረት ፣ "እንኳን ለቀቅህ! እንኳን ለቀቅህ! ውጣ! ውጣ!" በሚል ጩኸትና ስሜት የጭብጨባ ነጐድጓድ አወረዱበት ። በግራ በኩል ያሉት አግካሪዎች "አሶጣው አሶጣው"* የሚል የጩኸት ድምፅ አሰሙ ። ጩኸቱ ቆም ሲል ክሪስፒ ፣ "ካቢኔው የተለመደውን ተራ ሥራ ለመምራት በስፍራው ይቆያል" የሚል ድምፅ ሲያሰማ ዛቫታሪ የሚባለው አባል ፣ "ያንተ ነገር በቅቶናልና ልንሰማህ አንፈልግም" ብሎ ጮኸበት ። የቀሩትም ከመቀመጫቸው እየተነሡ ጣታቸውን እየዘረጉ የስድብ መዓት ያወርዱበት ጀመር ። ታላቅ ሁከት በምክር ቤቱ ሊፈጠር ሲል ፣ ፕሬዚዳንቱ ለማረጋጋት ሞክሮ በፍጹም የማይቻል መሆኑን ሲገነዘበው ፣ "ለዛሬው ይበቃል" ብሎ ምክር ቤቱን ስለዘጋው በግድ ሁሉም ተበተነ ።[1] በውጭም በአመራሩ የተበሳጩ ክሪስፒን ለመደብደብ በመንገድ ላይ የተጠባበቁ ነበሩ ። በጸጥታ ጠባቂዎች ብርታት ዳነ ። ሰሞኑንም እቤቱ ብቻውን በነበረበት ሰዓት ያለቅስ ነበር ይባላል ።[2]

ከዚያ በማግሥቱ ፣ በፍራንቼስኮ ክሪስፒ እግር የተከበረው ማርኬዜ አንቶኒዮ ዲ ሩዲኒ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሥፍራ እንዲይዝ ተሾመ ። በርሱም አቅራቢነት በዕድሜው ገፋ ያለው ሪኮቲ በንጉሡ ፈቃድ የጦር ሚኒስትርነቱን ሥፍራ ተሾመ ። በዚሁ ሰሞን ኤምቢሪያኒ የሚባለው የሬፑብሊካኖቹ ወገን በፊትም ቅኝ አገር ይቅርብን ይል ነበረ ፤ አሁንም ከአፍሪካ በፍጹም ለቀን እንውጣ የሚል አሳብ ለምክር ቤቱ አቅርቦ ነበር ። ነገር ግን ክርክር ተደርጎ አዲሱ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋትን ዓላማ ትቶ ከመረብ በመለስ ባለው ግዛት ብቻ መከላከልና ካፄ ምኒልክ ጋር የሰላም መንገድ ፈልጎ ምርኮኞቹን ማስለቀቅ በሚል ሐሳብ ላይ ፣ በዚሁ ክርክር ተደርጎ ይኸው አሳብ 219 የድጋፍ ድምፅ በ119 የተቃውሞ ድምፅ ሰጥተውበትና 72 ድምፅ ሳይሰጡ ቀርተው በአጠቃላይ የድጋፉ ድምፅ ብልጫ ስላለው ውሳኔው አልፎ ጸደቀ ።

* Alla Porta alla ! porta !

1 La Giornata di Adua,, R. Maz., PP. 323-325

2 Fracesco Crispi, Giuseppe Ardau. PP.393-395.



በዚሁ ጊዜ የቀኝ ክፍሎች ፣ "በጥቁር ወታደር ተሸንፎ መታረቅ ለኢጣልያ ታላቅ ውርደት ስለሆነ ፣ አስቀድሞ ክሪስፒ ባዘዘው መሠረት ማናቸውንም መሥዋዕት አድርገን ለጄኔራል ባልዲሠራ ጦር ልከ ምኒልክን መውጋትና ማሸነፍ ይገባል" እያሉ ይከራከሩ ነበር ። ለዚሁ መልስ ፣ አዲስ የተሾመው ሪኮቲ የሚባለው የጦር ሚኒስትር "ምኒልክ የማይሸነፍ ነው ፤ ጦርነቱን እንደገና ለመጀመር መቶ ሃምሳ ሺ ወታደር አንድ ሚሊያርድ ተኩል ሊሬ ያስፈልጋል. . . ስለዚህ ባልዲሠራ ከመረብ በለሳሙና ወዲህ እንዲመለስ ዐሥር የባታዮ ጦራችንም ወደ ኢጣልያ እንዲመለስ አዝዣለሁ ። ጠላትም ጠቡን የቀጠለ እንደሆነ ተመልሰው ይሔዳሉ" የሚል መልስ ሰጠ ። ይኸን የመሰለው መልስም ፣ በንዴት በቀል የፈለጉትን የክሪስፒን ወገኖች በፍጹም አላስደሰተም ። የሆነ ሆኖ ፣ በጣም ከሁሉም የተጠበቀው ንግግር ያዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የአንቶኒዮ ዲ ሩዲኒ ስለሆነ ፣ ለዚሁ መጋቢት 17 ቀን ምክር ቤቱ እንደገና ስብሰባ አደረገ ። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርም በፕሬዚዳንቱ ጋባዥነት ከመናገሪያው ላይ ወጥቶ ባደረገው ንግግር ውስጥ ፤

> ንጉሡ የፊተኛውን መንግሥት ስንብት ተቀብሎ ሪኮቲንና አዲሱን መንግሥት ሾሟል ።. . . በአፍሪካ ኢጣልያ ትኑር እያሉ የወደቁትን ዠግኖቻችንን እናስባቸው. . . ጄኔራል ባልዲሠራ በተሻለ መንገድ ከምኒልክ ጋር ንግግር አድርጎ ጉዳዩን በሰላም መንገድ እንዲጨርስ ትእዛዝ ተላልፎለታል ። ለኛ የሚጠቅመው እስኪረጋገጥ የጠቡ ሁኔታ ሊቀጥል ይችላል. . . ይሁን እንጂ ፣ በማናቸውም ረገድ የመስፋፋት ፖለቲካ እንደማናደርግ በምክር ቤቱ ፊት ዋስትናዬን እሰጣለሁ . . . ትግሬንም ለመውረር ምንም ዓይነት ዓላማ የለንም. . . ንጉሡ ትግሬን ውሰድ ብለው ቢሰጡን እንኳ ጥቅማችንን የሚቃወም መጥፎ ስጦታ ስለሆነ አንቀበልም . . . በትግሬ ሀብት አለ ብለው የሚያምኑ በመካከላችን እንዳሉ ኢትዮጵያን የማያውቁ ናቸው ፣. ."[1]
> የሚሉ ቃላት ይገኛሉ ።

ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ስብስብ ያለ ሰላማዊ አሳብ ፣ በብዙዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ በዚሁ እንዲፈጸም በምክር ቤቱ በድምፅ ብልጫ ከጸደቀ በኋላ ፣ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለጄኔራል ባልዲሠራ በአዲግራት ተከበው የተቀመጡትን ኢጣልያኖች እንዲያድንና አጋሜን ለቆ እንዲወጣ ካፄ ምኒልክ ጋር ግንኙነት አድርጎ እስረኞቹ የሚለቀቁበትን መንገድ እንዲፈልግ ትእዛዝ አስተላለፈለት ። ይኸም ባለፈው ምዕራፍ ዐፄ ምኒልክና ዠኔራል ባልዲሠራ በማገናኘር ሳልሳ በኩል የተጻጻፉበት ውሳኔ ያላገኘው መሆኑ ነው ።

1 Storia Diplomatica . . . Durante il |Regno di Menelik . . . , C- Rossetti, PP. 185- 186.

ይሁን እንጂ ፣ ይህ ውሳኔ በምክር ቤቱ ውስጥ ያሉትንም በውጭ ያሉትንም የቀኝ ክፍሎች አናዷቸዋል ። እነርሱንም በጣም የቆጫቸው ሰፊ ግዛት ከማጣቱ የበለጠ በጥቁር መንግሥት ተሸንፈው ታሪቁ የሚለው የውርደት ወሬ ነው ። ስለዚህ ለቀኝ ክፍሎች አንጋፋ የሆ ነው ክሪስፒ ምንም ከሥልጣኑ ቢሰናበት ፣ ለንጉሡ ከዚህ ቀጥሎ ያለ ውን የጸጸትና ወደ አዲስ ጦርነት የመገፋፋት ደብዳቤ ጽፎ ተሰናበተ ።

ግርማዊ ሆይ ፤

አለቃው ስለሆኑ ሠራዊትዎን ይበቀሉለት ፤

የሐበሻ በትር ሳይቀጣ ቢቀር ዝግንነትና የዝብዱ ሙያ በኛ ዘንድ እንደሞቱ ይቆጠራሉ ። በውስጥዎም ያሉት የሚታረድ የበግ መንጋዎች እንጂ ፣ መዋጋትና ማሸነፍ የሚችሉ የወታደር ቡድኖች አይደሉም ማለት ነው ። ይኸም ይዞታ የኢጣልያንን ኃይልና መከበ ሯን የማይፈልጉትን የውጭ ጠላቶችና እንደዚሁም ንጉሣዊው አገዛዝ እንዲወድቅ የሚፈልጉትን የውስጥ ጠላቶች* የሚረዳ ነው ። አሁን በአፍሪካ የደረሰው ከመጋቢት ወዲህ በፓርላማችን የጦር ሚኒስት ርዎ ያደረገው የፈሪ ዲስኩር** ውጤት መሆኑ ነው ። ምኒልክ የማይ ሸነፍ አይደለም ፤ የማይሸነፍ ያስመሰለው በጋዜጣና በምክር ቤታችን መንግሥታችን ሊወጋው አለመፈለጉ ስለ ተጻፈና ስለ ተነገረ ነው ።

ይኸንኑ የመሰለ ውድቀት በ1866 ደርሶብን ነበር ። በአድሚራል አልቤኒ ስንፍና የጠላት ድል ተረጋገጠ ። በዚሁ ዓይነት ስንፍናችን አውስትሪያ በባሕር ኃያል ለመሆን በቃች ። ግርማዊነትዎ ይኸን ፖለቲካ ይለውጥ ። ሁሉም ነገር መፍትሔ አለው ። ግርማዊነትዎ ከፈ ለገ መኖር የማይገባውን አረመኔ ሕዝብ ለመቅጣት የሚችሉ በሚሊ ዮን የሚቆጠሩ ክንዶች በግርማዊነትዎ ዙሪያ ይዘረጋሉ ። ያለዚያ በሥ ልጣኔ ላይ እውነተኛ ስድብ ነው ። ይች ደብዳቤዬ በልብዎ ውስጥ ለመግባት ኃይል እንደምታገኝ ተስፋ አለኝ ። በማናቸውም ረገድ ቃሌ ባይደመጥም ፣ እኔ ግን በወታደርነቴና በሠራተኛነቴ የተነሣ ለግርማዊነትዎ ይኸን በማሳሰብ ተግባሬን እንደ ፈጸም ሁ ዐውቃለሁ ።

ፊርማ ክርስፒ [1]

ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ፣ ኢትዮጵያ እንደልብ የሚጋለብባት አፍ ሪካዊት አገር እንደ ሆነች ያምን ነበር ። ባለፈው ፣ "የትግሬ አገር ለኢጣልያ ክፍት ነው ሳንይዘው ብንቀር የኛ ስንፍና ነው" ብሎ

---

*የግራ ክንፎች በዚህ ዘመን እንደ ፈረንሳዊ መንግሥት በሬፑብሊክ ለመተዳደር ጽኑ ፈቃድ ያላቸውን የውስጥ ጠላት ሲላቸው ፣ ኢጣልያ ኃያል እንዳትሆን የምትፈልገው የውጭ ጠላት የተባለችው ፈረንሳይ ናት ።

**የፈሪ ዲስኩር የሚለው አዲሱ የጦር ሚኒስትር ሪኮቲ "ምኒልክ የማይሸነፍ ነው" ብሎ በምክር ቤት የተናገረውን በመውቀስ ነው ።

1 F.Crispi, G. Ardali, PP. 396-398



የነበረውም በዚሁ መንፈስ ነው ። የአላጌን ውድቀት እንደ አንድ ትልቅ መደፈር ቆጥሮት አንድ ጊዜ ፣ "አንድ ድል እጠብቃለሁ" ሌላ ጊዜ "የኢትዮጵያን ጉዳይ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ የሚደመድም ድል ልታስገኝ ይገባል" እያለ አፍሪካ ላለው አዝማቹ ለባራቲዬሪ ቴሌግ ራም ያዥጐደጉድለት እንደነበረ የሚታወስ ነው ። አሁን ያ መን ፈስ በፍጹም ከድቶት ከመሰደብ ፣ ከመንጠጥ ፣ ከሽረትና ከውርደት አድርሶታል ። ይልቁንም ባልጠበቀው መንገድ አንድ ጊዜ ለዘለቄታው የውጫሌውንም ጉዳይ ፣ የኢጣልያንም የመስፋፋት ምኞት የሚደ መስስ የድል አድራጊነቱ ዕድል ከርሱ እጅ ወጥቶ በኢትዮጵያ እጅ ሲገባ ቢናደድ ቢበሳጭ እውነት አለው ። ነገር ግን በጣም የሚያ ሳዝነው ለንጉሡ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ፣ "መኖር የማይገባው አረመኔ ሕዝብ" በሚል ቃል የኢትዮጵያን ሕዝብ መሳደቡ ነው ። በነዳቦርሚዳ ደብዳቤ ላይ እንደ ተገነዘብነው ፣ ክሪስፒም በፍጹም የኢትዮጵያን ውስጣዊ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ታሪኳንም አያውቅም ማለት ነው ። በጥንታዊነት ፣ ኢትዮጵያ ከኢጣልያ ቅድሚያ ነበራት ። በአሁኑ ጊዜ ካለው ዘመናዊ ሥልጣኔ ወደኋላ ብትቀርም በጥንታዊ የአክሱም ሥል ጣኔ ከቀደምቶቹ አንዷ መሆኗን አላጤነውም ፤ ወይም በወረራ ምኞት አእምሮው ስለታወረ ሳያስበው በናቀው ሕዝብ መሸነፋም ስላደ ነዘዘው የሚያውቀውንም ላለማወቅ ዐውቆ ልቡን አደንድኗል ማለት ነው ።



የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ቀዳማዊ
ከፍራቴሊ ትሬንስ መጽሐፍ



የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንቼስኮ ክሪስፒ
ከፍራቴሊ ትሬቬስ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሃምሳ

## ዳግማዊ ምኒልክ መረብን አልፈው ያልሔዱበት ምክንያት ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በዓድዋ ጦርነት ዕለት ይኸን ከፍ ያለ ድል አድራጊነት ካገኙ ወዲህ ፣ ከመረብ እስከ ምጥዋ ድረስ ያለው የኢጣልያ ጦር "የምኒልክ ጦር መጣ መጣ" እያለ ሲሸበር ፣ እርሳቸውም ወደ ሐማሴን ለመዝለቅና ጨርሶ የኢጣልያንን ኃይል ከጠረፍ ለማጥፋት በአሳባቸው ሳይመጣ አልቀረም ነበር ። ወደ ሐማሴን ለመዝለቅ ከዓድዋ ወደ እንትጮና ወደ ፈረስ ማይ መሔዳቸው ለዚሁ አሳብ መሆኑን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረሥላሴም ፣ ግራዝማች ዮሴፍም ጠቅሰውታል ። ወደ ሐማሴን ያልዘለቁበትን ምክንያት ጸሐፌ ትእዛዝ ብዙ ሠራዊት የሚያሳልፍ መንገድና በቂ ውሃ በመጥፋት መሆኑን ገልጸዋል ። ይኸም የማይታበል መሆኑ በብዙ የኢጣልያ መጻሕፍት ተረጋግጧል ።[1] ግራዝማች ዮሴፍ ደግሞ የኢጣልያ መንግሥት ለእርቅ ሳልሳን በመላኩ ምክንያት መሆኑን እገለጹበት ላይ የመጣው ለተንኮል እንጂ ለእርቅ አለመሆኑን ጠቁመዋል ። በእውነትም ከአዲስ አበባ ሳይነሡ በተለይም ከአምባ አላጌ ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ ኢጣልያኖች ሲመጮቸው ውጊያ ፣ ሳይመቻቸው እርቅ ፈላጊዎች መሆናቸውን በሰፊው ተረድተውታል ። ከዓድዋ ድል በኋላ መረብን አልፈው ኢጣልያኖቹን ለማጥፋት ኃይላቸውን ቢተማመኑት ኖሮ የሳልሳ መምጣት መሠረት ሆኖ ወይም ለይሉኝታ ወይም ከኢጣልያ ጋር የእርቅና የዝምድና ነገር አምሯቸው ወደፊት መግፋትን አይተውትም ነበር ።

ከዚህ በፊት በ1879 ዓ.ም. ዶጋሊ ላይ ራስ አሉላ የኢጣልያንን ጦር ካሸነፉ በኋላ ምጥዋን ገሥግሠው አልያዙም ። ቢፈልጉ መያዝ ይችሉ ይሆናል ። በኋላ ግን የመዘዙን ብዛት አመዛዝነው እንደ ተዉት የታወቀ ነው ። አዲስ ጦር ካስመጡ በኋላ ፣ እንዲያውም ጣልያኖቹ ወደፊት አልፈው ሰሐጢን ይዘው መመሸጋቸውን ዐፄ ዮሐንስ ሰምተው እነሱን ለመውጋት በእሥመራና በጊንዳ በኩል ከሰማንያ ሺ ጦር የበለጠ ይዘው መጥተው የሰሐጢን ምሽግ መድፈሩም ካንድ ወር

---

1 La Prima Guerra d' Africa, Pal. Crispi, Chaps. VIII-IX

በላይ በዚያ ፀረሀማ ቀበሌ ለመቆየት የስንቁ፣ የውሀና የግሩ ጉዳይ
ሳያስችላቸው ቀርቶ ወደ ዓድዋ መመለሳቸውን ባለፈው ያነበብነው
ትዝ ይለናል ። የምጥዋን ወደብም ለመውረር አልከጀሉም ። የምጥዋን
ወደብስ ለጊዜው ቢይዙ ኖሮ የወደብ አስተዳዳሪነቱን የሚይዝና
ከባሕር በኩል የሚመጣን ጥቃት ለመከላከል ችሎታ ያለው ኃይል
ነበራቸውን? ብሎ ያጠያይቃል ። ለዚያውም ለዶጋሊው እልቂት
ተቆጥተው ያኮረፉት እንግሊዞች ዝም ብለው ይመለከቱ ነበርን?

እሁንም ዐፄ ምኒልክ፣ ከዓድዋ ድል በኋላ ወደፊት ለመግፋት
እንቅፋት የሆኑ ብዙ ችግሮች በፊታቸው እንደ ተደቀኑ አይጠረጠርም ።
ከነዚህም ውስጥ በትክክል የምንረዳቸው ፤

ሀ/ ከቤቱ ከንብረቱ ከተለየ ስምንት ወራት ያህል ያለፈው
የጦር ሠራዊትና ሹማምንት፣ ክረምት ከመግባቱ በፊት ወደ
ቤቱ መመለስን ከመናፈቅ በቀር አዲስ ጦርነት ለማድረግ
ምኞት አልነበረውም ። ቢኖረውም ችግሩ አላስቻለውም ።

ለ/ የተዋጊው ጦር ከነጓዙ ከገረድና ካሽከሩ ጋር ቁጥሩ ከመቶ
ሺ ስለሚበልጥ፣ ለዚህ ሁሉና ለከብቱ ጭምር የሚበቃ
ስንቅ፣ ሣርና ውሀ ይልቁንም በቆላማው በምጥዋ አካባቢ
ስለማይገኝ፣ ለመዋጋት ምኞት ቢኖረውም እንኳን አይች
ልም ። ከዓድዋ ጦርነት በፊት እንኳን በዚሁ የተነሣ
በወታደሩና በትግሬ ባላገር መካከል በዘረፋና በስንቅ ችግር
ግጭት እየተደረገ ቅርታ መግባቱን ተመልክተናል ።

ሐ/ ከግራኝ አህመድ እነሣሥ በኋላ ይልቁንም የጐንደር መንግ
ሥት ከደከመ ወዲህ፣ ከማዕከላዊው መንግሥት ሥልጣን
ቁጥጥር ውጭ ሲኖሩ በዐፄ ምኒልክና በስመ ጥር መኳንን
ቶቻቸው በነራስ ጐበና፣ በነደጃች በሻህ አቦዬ፣ በነራስ ወልደ
ጊዮርጊስ፣ በነራስ ተሰማ፣ በነራስ መኰንን ብርታትና ትጋት
በቅርብ ጊዜ በዘዴም በጦርነት ኃይልም ወደ እናት አገር
ቢተጠቃለሉት አውራጃዎች የየአካባቢው ገዥዎች ቀድሞ
የለመዱትንና አሁን ያጡትን ሥልጣን ለማግኘት የልብ
እምሮትና ምኞት እንደሚኖራቸው፣ እንደነበራቸውም ግልጽ
ነው ። የየአካባቢው ባላባቶች የሥልጣን እምሮታቸውን
ለመፈጸም ያፄ ምኒልክ ከውጭ አገር መንግሥት ጋር ሲዋጉ
መድከም እንደሚረዳቸው የታወቀ ነው ።



ስለዚህ፣ በዓድዋ የደከመውን ጦር እስከ ምጥዋ ድረስ እየ
መሩ ሲሔዱ፣ ከኋላቸው ምን እንደሚጠብቃቸው አይታወ
ቅም ። እንኳን የቅርበቹ ባላባቶች ይቅሩና አንዳንድ ተመል
ካቾች፣ "እርስዎ መረብን ሲሻገሩ ባባታቸው አልጋ መቀማት
ቅር ያላቸው ራስ መንገሻ የትግሬን ጦር ይዘው ከኋላ ሊወ
ጉዎት አስበዋልና ቢበቃዎት ይሻላል" ብለው የመከሩዋቸው
የትግሬ ተወላጆች አሉ ይባላል ። በአላጌ ጦርነት ጊዜ፣
"ያባቴን አልጋ ተቀምቻለሁና እርዱኝ" ብለው በምስጢር
ለእንግሊዝ መንግሥት ደብዳቤ የጻፉት አሁንም ቢመቻቸው፣
ይኸውም ማለት ዐፄ ምኒልክ ቢዳከሙ፣ ራስ መንገሻ ጉልበ
ታቸውን ቢተማመኑበት በኃይላቸው ለመጠቀም እንደማይ
መለሱ የታወቀ ነው ። ሁለቱ ቢዋጉ ደግሞ የሁለቱ ውጊያ
ለማን እንደሚጠቅም መረዳቱ ለማንም አያዳግትም ። ባለፈው
ጊዜ፣ የኢጣልያ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር የጠበ
ቀውና ያጣው ይኸንኑ የርስ በርስ ጦርነት ነው ። የርስ
በርሱን ጦርነት ቢያገኝ፣ እንደገና ለመመለስ ይችል ነበር ።
"እስካሁን ከጦርነት ያልተለዩት ራስ መንገሻ ከኋላ ሊወጉ
ዋቸው አይችሉም" ብለን ብናምንም፣ ከቀረው ችግር ጋር
የዚህ ወሬው መሰማቱ ብቻ ወደ ጥርጥር መውሰዱ የታወቀ
ነገር ነው ። በብዙ ድካም ተጠቃሎ የተሰባሰበው የኢት
ዮጵያ ግዛት ሳይናጋ እንዲረጋ የተፈለገ እንደሆነ፣ "ዐፄ
ምኒልክ ሠራዊታቸው ዓድዋ ላይ ጣልያንን ድል አደረገ ።
አሁንም እንዳለ ነው ፤ አልተነካም" የሚባለው ወሬ በትክ
ክል የሥልጣን ጕጕት ለነበራቸው ባላባቶች እንዲደርሳቸው
ያስፈልጋል ። ያለዚያ በስንት ድካም የተጠናከረው የግዛት
አንድነት እንደገና ይበታናል ብሎ የሚያሠጋ ይሆናል ።
በጠቅላላው የነጻነት ጥቅሙና ዋጋው፣ በባዕድ የተገዥነት
ጉዳቱ፣ የዚያን ጊዜ የዛሬውን ያህል እንኳን አልተሰበከም ፤
ብዙም አልታወቀም ። ጊዜው የፊውዳሊዝም (የባለጉልት)
ጊዜ ስለሆነ፣ እያንዳንዱ አገሩንና ነጻነቱን ቢወድም፣ አል
ጋን የመያዝ ምኞት በየአውራጃው መስፍንት ዘንድ ስለነ
በረ፣ ይህ እንዳይደርስባቸው ምኒልክና ታማኞቻቸው መጠ
ንቀቅ እንደ ነበረባቸው ይታወቃል ።

ከሁሉ የበለጠ ደግሞ በኢጣልያኖች ዘንድ ያለው የድርጅት
ሁኔታ አሥጊ ነበረ። ጄኔራል ባራቲዬሪ ድል በሆነ በአራተኛው

ቀን ጄኔራል ባልዲሠራ ቁጥሩ ዐሥራ አምስት
የሚደርስ አዲስ የጦር ወታደር ይዞ ምጥዋ ደርሶ የዓድዋ
ውጊያ ውጤቱን ሰምቶ ፡ ድንጋጤም ሽብርም እንደ ደረሰበ
ቢታወቅም ከዓድዋ ጦርነት የሸሹትን ሰብስቦ እንደ ምን
የጦሩን ቁጥር እስከ ሐያ ሺ አድርጎ ከመረብ ባሻገር ያለው
አገር ለመከላከል ቆርጦ ይጠባበቅ እንደነበረ ግልጽ ነው

በዚሁም ጊዜ ፡ ሳልሳን ለእርቅ መላኩን ምንም እንኳን አዲስ
ጠቅላይ ሚኒስትር ዲሩዲኒ ቢፈቅድለት ፡ የዓድዋ ድል ወሬው በሮ
እንደ ተሰማ ሕዝቡ በሐሳብ ተለያይቶ የነበረውን ባጠቃላይ መልስ
እናስታውስ ።

አንደኛው ክፍል ፡ መላውን ኢትዮጵያን መያዝ አልተቻለም ። ከ
ረብ ወዲያ ያለው ግዛት ደረቅ ስለሆነ ገንዘብ ከማስወጣት በቀር የ
ረባን ነገር የለምና ቢለቀቅ ይሻላል የሚል ፡

ሁለተኛው ክፍል ፡ ጄኔራል ባልዲሠራ ከመረብ ወዲህ ከአስ
እስከ ከሰላ ያለውን ይዞ መከላከሉ የሚገባ ነው የሚሉ ፡

ሦስተኛው ክፍል ፡ የትኛ አገር የማግኘቱና የማጣቱ ጉዳይ እንኳን
ወደጐን ቢተው ባንድ አፍሪካ ውስጥ በሚገኝ ባልሠለጠነ የጥቁ
መንግሥት የኢጣልያ ጦር ተሸንፎ ተመታ ተብሎ በታሪክ ወደፊ
ተጽፎ የሚኖረው ለሞራላችን አሳፋሪ ነገር ነው ። ቢያስፈልግ
ቁጥሩ ሠላሳ ሺ የሚደርስ የጦር ኃይል ለጄኔራል ባልዲሠራ ተጨም
ጦርነቱን መቀጠልና መበቀል አስፈላጊ መሆኑን ወትውተዋል ። በ
ብዳቤ ወይም በጋዜጣ ፡ "በሮማውያን ታሪክና ሐውልት መካከል ሆ
ይኸን ምኒልክ ከድሉ በኋላ ያቀረበልንን እርቅ ተቀብለን
ነቱን ብናቆም ያባቶቻችን ሐውልት ይታዘበናል ፤ ዐፅማቸውም ይ
ቅሰናል" እያሉ ከክሪስፒ በኋላ መንግሥቱን የሚመሩትን ጠቅ
ሚኒስትሩን ዲ ሩዲኒን ፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ኃይታኖንና የ
ሚኒስትሩን ሪኮቲን ገፋፍተዋቸው ነበር ።

ነገር ግን ፡ ባለፈው የታየው ዳግ ምኒልክ ፡ የመሳፍንቱና የመ
ንንቱም ኅብረት ፡ የሠራዊቱ ዝግጁነትና ብርታት ስላሠጋው የኢ
ልያ አዲሱ መንግሥት ወደ አፍሪካ እያከታተለ ጦር በመላክ
ውሮፓ የራሱን የኢጣልያንን መንግሥትና ግዛት ወደ ድካም
ሎም ወደ ውድቀት እንዳያደርሳቸው በማሰብ ለሕዝቡም ለምክ
ቤቱም ይኸንኑ በሰፊው እያስረዱ በማሳሰብ ጦርነቱን የመቀጠ
ነገር እንዲቆም አደረጉ ። ዲ ሩዲኒንና ወገኖቹን የቀኝ ክፍሎችና ጋዜ
ዎቻቸው ፡ "ኢጣልያ አገራችንን የኃፍረትና የሐዘን ጥቁር ል



ለዘለዓለም አከናነቧት ፡ ኢጣልያ በአባ ገሪማ ሸለቆ ተቀብራ ቀረች" እያሉ የወቀሳና የስድብ ናዳ ሲያወርዱባቸው መስንበታቸው የጸጸቱንና የንዴቱን መጠን ያስገነዝበናል ።[1]

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፡ በመሠረቱ በሶሺያሊስቶች እየተረዳ ከሕዝብና ከምክር ቤት የዓድዋን ጦርነት እንዲበቀል ሁካታ ጭምር ከአገር አፍቃሪዎችና ከቀኝ ክፍሎች እልህ ያስበትን የበቀል ማሳሰቢያ በዚህ ዓይነት ማባበልና ማስረዳት ለማቆም ሞከሯል ። ዳግ ምኒልክ ጦር መረብን አልፎ ምጥዋን ጭምር ልውሰድ ቢል ግን መንግሥቱ የሚደግፈው ጄኔራል ባልዲሠራ ያለውጊያ ሊለቅ አይችልም ። ውጊያም ቢደረግ ከዓድዋ በበለጠ መሥዋዕትነት እንጂ በዋዛ አይፈጸምም። ዓድዋ ድል የሆነው የጄኔራል ባራቲዬሪ የአራት ብርጌድ ጦር ነው ። ከዓድዋ በኋላ ምጥዋ ከባልዲሠራ ጋር የመጡት ጄኔራሎች ካለፉት በደረጃም በማናቸውም ብልጫ ነበራቸው ። ምናልባት ጄኔራል ባልዲሠራ ቢሸነፍ ፡ ሌላ ጄኔራል ለመተካት የኢጣልያ መንግሥት ለጊዜው ይችላል ። ዐፄ ምኒልክ ቢሸነፉ ግን ፡ በሰላም መንገድ የተደራጀ ጦር ይዞ ወዲያው የሚተካና የሚዋጋ መቅረቡ በዚያን ጊዜ እንደ ሕልም ይቆጠራል ። የዚያን ጊዜው የመንግሥታችን አቀዋምና ድርጅት ይኸን ዕድል ለማግኘት አይችልም ። ዐፄ ምኒልክ ቢሸነፉ ባራት ማዕዘን ባሉት መሳፍንት ዘንድ አልጋ ለመያዝ ፡ ከማዕከላዊ ሥልጣን ለማፈንገጥ በሚያሳዝን አኳኋን ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የርስ በርስ ጦርነትና ሁከት እንደሚኖር አይጠረጠርም ። በዚህም ሁኔታ እንደ ተለመደው የኢጣልያም ሆነ የሌላ መንግሥት በደንብ ይጠቀምበታል ።

በዓድዋ ጦርነት ፡ ዐፄ ምኒልክ ሙሉ ጦራቸውን ይዘው ከመሳፍንትና ከመኳንንት ጋር ሲዘምቱ ፡ ከኢጣልያ ወገን ጄኔራሎች እንጂ ንጉሡ የቀረው ቀርቶ የጦር ሚኒስትሩ እንኳን አልዘመተም ። የኛ ወገኖች የጦር መማሪያ የሚያገኙት በግዥና በደጅ ጥናት ሲሆን ኢጣልያኖች ግን ፡ ራሳቸው እየሠሩ እንደ ልባቸው ያገኛሉ ። በአፍሪካ ጦርነት የጥቁር ወታደር የነጭን ወታደር ተዋግቶ ነጻነቱን ያዳነ የለም ። እየተዋጋ አንድ ጊዜ ቢያሸንፍም ፡ መጨረሻውን እየተሸነፈ ሁሉም ከኢትዮጵያ በቀር ለፈረንጆች ተገዥ ሆኗል ። ባሁኑ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ከኢጣልያ በቀር የጀርመንና የእንግሊዝ ሕዝብ ተናደደ። ወሬውም በየቅኝ አገሮቻቸው ዘንድ በመሰማቱ አንድ ዓይነት የነጻነት ስሜትና የመዋጋት መንፈስ በተገዥዎቻቸው ዘንድ እንዳያሳድሩ ሥጋትም ጥንቃቄም ነበረባቸው ። ጊዜው በአፍሪካም በእስያም ለነጭ

1 Abyssinia ,Scarfoglio,PP. 342-345

ሕዝብ ያደላበት ዘመን ስለነበረ፣ የዚህ ዘመን ዕድል ነጭን ገዥ ሌላውን የቀለም ሕዝብ ተገዥ አድርጎ ስለ መደበው፣ ያሁኑ ያፄ ምኒልክ ድል አድራጊነትና የኢትዮጵያ ነጻነት በአፍሪካ የዓለም መስኮት ላይ ቦልኮ የታየ ወይም የተሰማ ድንቅና ብርቅ ነው። ከዚህ ድል በኋላ ምኒልክ ይበልጥ ገፍተው የምጥዋን ወደብ ቢወሩ ኖሮ እንኳን ኢጣልያ እንግሊዝም አይታገሥም ነበር።

ስለዚህ፣ ይኸን ሁሉ ስንመለከት ባፄ ምኒልክ መንግሥትና በረዳቶቻቸው ዘንድ የነበረውን ችግር ለማወቅና የተከተሉት ፖለቲካ ስሕተት የሌለበት መሆኑን እንረዳለን። ነገር ግን፣ “ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው” እንደሚባለው ባልዲሠራ አዲስ ይዞ የመጣውን ጦር አስከትሎ ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ ባሉት ቀኖች መረብን አልፎ ቢዋጋ እስከ ወሎ ያለውን አገር ሊይዘው ይችል ነበር” እያሉ ጣልያኖቹ በበኩላቸው ይቆጩ ነበር። ፖላሜንጊ ክሪስፒ የሚባለው ኢጣልያዊ ስለ አፍሪካ ጦርነት ባዘጋጀው የሰነድ መጽሐፍ ውስጥ፣

> በጦርነቱ አንደኛው ብዙ ሰው ያለቀበት ምኒልክ ያላሰበውን ድል ካገኙ በኋላ ስንቅ ስላጣ ወደ አሥመራ ወይም ወደ ጉራዕ ለመግፋት አልደፈረም። ጄኔራል ባልዲሠራ ባለው ጦር ከምኒልክ ሳይዋጋ ምኒልክ ወደ አገሩ (ወደ ሸዋ) ከተመለሰ በኋላ መላውን ትግሬንና አጋሜን ይዞ ዓድዋ ላይ ሆኖ ምርኮኞቹን መልስ እያለ መጭውን ጊዜ ዝም ብሎ ለመጠባበቅ በቻለ ነበር። ምኒልክም አሁን እንዳደረገው ሐበሻን ባንድነት ሰብስቦ እንደገና ለመዋጋት ብዙ ዓመታት በፈጀበት ነበር። እኛም በስሕተታችን ኀብረት የሰጠነው አገር (ኢትዮጵያ) ተለያይቶ ሲፈርስ ለማየት ጊዜ እናገኝ ነበር።[1]

ሲል ገልጿል።

በኛም በኩል፣ “የኢጣልያ ጦር ዓድዋ ድል እንደሆነ ዐፄ ምኒልክ ወዲያው ወደ አሥመራ ቢገሠግሡ ኖሮ፣ የኢጣልያን ጦር አጥፍተው የምጥዋን ወደብ እጅ ያደርጉ ነበር” እያሉ ያንጊዜም ዛሬም ብዙ ሰዎች ሲናገሩ በኢጣልያኖችም በኩል፣ “አዲስ ጦር ተልኮ እንበቀል” ሲሉ በዚያን ጊዜ የነበረውን ዝርዝሩን ችግር ለማይመለከት ወይም መመልከት ለማይፈልግ በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ቀና መስሎ መታየቱ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ፣ ወደዚህ ወደ አልተረጋገጠ ሁኔታ ለመግባት ሁለቱም የመንግሥታት መሪዎች ከሥጋት ጋር ጥንቃቄ ስለሚያደርጉበት፣ ሁለቱም ወገኖች ለጊዜው በመረብ ክልል መታረቅ የተሻለ ሆኖ

1 La Prima Guerra d' Africa, Pal. Crispi, Chaps. VIII-IX.



አገኙት። ጣልያኖችም የመሸነፍ ቁጭታቸውን ተሸክመው እንደ ታገዱ ዐፄ ምኒልክም መረብን አልፈው ኢጣልያን የመውጋት እምሮታቸውን ውጠው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በምክር ቤት ለመማክርቱ ሲያስረዳ፣ “...እንደገና ጦር ልኬ ትግሬን መያዝ አልፈልግም፣ እንኳን በጦር ለመያዝ ምኒልክ እንደዚሁ ውሰደው ብለው ቢሰጡኝም አልቀበልም” ያለው፣ በዚህ ዓይነት አነጋገር በቁጭትና በቁጣ “አዲስ ጦር ልከን እንበቀል” እያሉ ያስቸገሩትን ለማግባቢያ ያመጣው የንግግር ፈሊጥ ነው እንጂ፣ እንኳን ዐፄ ምኒልክ ውሰድ ብለውት አዲስ በተላከው በጄኔራል ባልዲሠራ ጦር ማሸነፍ እንደሚችል ቢተማመንና እርግጠኛ ቢሆን ኖሮ የመሸነፍ ኃፍረቱን ለብሶ ከሚቀመጥ ይልቅ፣ “ተዋጋ ተበቀል” የሚል ትእዛዝ ለጄኔራል ባልዲሠራ ከማስተላለፍ የሚቦዝን አልነበረም።

ዐፄ ምኒልክ ወደፊት ያልገፉበትን ምክንያት እንደገለጽነው ሁሉ፣ በኢጣልያንም ዘንድ የነበረው የወታደሩና የድርጅቱ አቅም ማነስ፣ የመንግሥቱ ሀብት መቀርቀዝ፣ የሶሻሊስቶች ጦርነት አለመፈለግ፣ የኢትዮጵያ ኀብረትና ተዋጊነት ሁሉም ተባብሮ ኢጣልያ መንግሥትም የመሸነፍ ኃፍረቱን ውጦ በመረብ ወሰን ለመዋዋል፣ የተዋጋበትን የውጫሌን ውል ሰርዞ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት ለማወቅ አስገደደው። ይኸውም ባለፈው እንዳነበብነው፣ የኢጣልያ መንግሥት አዲስ ጦር ልኮ የደረሰበትን ኃፍረት ሳይበቀል መስማማት በአውሮፓ፣ በተለይ በእንግሊዝና በጀርመን አገር ትዝብትን፣ በራሱ ሕዝብ ዘንድ ሮሮና ቁጭትን አሳድሯል።

# ምዕራፍ ሃምሳ አንድ

## የኢጣልያ ወታደር በሆኑት ያገር ተወላጆች ላይ የተፈጸመው ቅጣት

በየትም አገር ቢሆን አገሩን ከድቶ ከጠላት ጐን ተሰልፎ ወገኑን የወጋ ተወላጅ እንደ ትልቅ ከሐዲ ተቆጥሮ የሞት ቅጣት እንደሚፈረድበት የታወቀ ነው ። ነገር ግን ይኸን ፍርድ በሥርዓት መስጠት የሚቻለው በአንድ በሕገ መንግሥት በሚተዳደር አገርና መሠረቱ የጸና መንግሥት ሲሆን ነው ። በዚህ በ19ኛው መቶ ዓመት ላይ በሥልጣኔ ወደኋላ ቀረት ያለችው የኢትዮጵያ ሁኔታ ከዚህ ለየት ይላል ። በጽኑ ሕገ መንግሥት ላይ የተመሠረተና የተደላደለ መንግሥት ባለመኖሩ ጉልበት ያለው ከሌለው ላይ ዘውድን ለመቀማት የሚችልበት ፣ አንድ መስፍን የውጭ አገር መንግሥት እርዳታ ተደግፎ ሌላውን ጥሎ የራሱን መንግሥት የሚያቆምበት ዘመን ነው ።

ለምሳሌ ፣ የዘመነ መሳፍንት ጊዜ ያለፈው ዘውድና ሥልጣን በመቀማማትና በጦርነት ላይ ነው ። ዐፄ ቴዎድሮስም የራስ ዓሊን መንግሥት በሕጋዊ መልክ ሳይሆን በጉልበት ወረሱ ። ጉልበት ለማግኘት ባጀማመራቸው ጊዜ ላይ በሱዳን ጠረፍና በቋራ ቆላ ከሚገኙ ሽፍቶች ጋር ፣ "እናንተም እኔም ብንቀማ አብረን እንካፈላለን" ብለው ከሽፍቶች ጋር እስከ መማማል የደረሱበት ጊዜ አለ ።[1] ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር እንግሊዞች ሲዋጉ መንገድ በመስጠት ስንቅ በማቀበል ደጃች ካሣ(ዐፄ ዮሐንስ) እንግሊዞችን ረድተዋል ። ለዚህ ውለታ እንግሊዞች ወዳገራቸው ሲመለሱ ይዘው ለመሔድ ያልፈለጉትን የጦር መሣሪያ ለደጃች ካሣ ሰጥተዋል። በዚህ መሣሪያ ደጃች ካሣ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው የንጉሠ ነገሥትነትን ዘውድ ተቀዳጅተው "ዐፄ ዮሐንስ" ለመባል በቅተዋል ። ዐፄ ዮሐንስ ከእንግሊዞችና ከግብጾች ጦርነት ባገኙት መሣሪያ ከርሳቸው በፊት "የሸዋ ንጉሥ" እየተባሉ ቆይተው በኋላ ፣ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት" እያሉ ማኅተም በማሠራት ለንጉሠ

---

1 የቴዎድሮስ ታሪክ በቤርሊን እንደሚገኝ አብነት አሳታሚ ኢኖ ሊትማን ገጽ 6—8

ነገሥትነት ቀረብ ብለው የነበሩትን ምኒልክን አስገብረው የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣናቸውን ለማረጋገጥ ችለዋል ።

በመሣሪያ ብዛት ላይ ዮሐንስ የገበሩት ምኒልክ ፥ የተገዥነት ቁጭታቸውን በልባቸው አድርገው ከየትም በኩል መሣሪያ መሰብሰብን ዋና ዓላማ አድርገው ያዙ ። ኢጣልያኖች በምጥዋ በኩል መጥተው ካፄ ዮሐንስና ከራስ አሉላ ጋር ለጦርነት በተፋጠጡበትም ጊዜ ፥ ምኒልክ በአሰብና በአንኮበር በኩል ከኢጣልያኖች ፥ በጅቡቲና በድሬዳዋ በኩል ከፈረንሣዮች ጋር ግንኙነት በማድረግ የጦር መሣሪያ ይሰበስቡ ነበር ። ኢጣልያኖችና ዐፄ ዮሐንስ ለጦርነት በተፋጠጡበት ጊዜ "አስታርቃለሁ" ብለው ላፄ ዮሐንስም ፥ ለኢጣልያ ንጉሥም ደብዳቤ ጽፈው የነበረውን ተመልክተናል ።

በዛሬ ዘመን ይህ የመሳፍንትና የነገሥታት አቅዋም የሚያስኬድ አይደለም ። በአንድ ሕገ መንግሥትና ምክር ቤት ባለው በተደላደለ መንግሥት ውስጥ በምክር ቤት ፈቃድ መሪው ከውጭ ጠላት ጋር ለጦርነት በተሰለፈበት ሰዓት ያንድ ክፍል መስፍን "ላስታርቅ" ቢል ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው ። ከጠላት ጐን የተሰለፈም ቢኖር በከሐዲነት ያስጠይቃል ። በዘመኑ በመሳፍንትና በባለጉልት በተከፋፈሉ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ግን ፥ ሁሉም በየፊናው ወደ ዙፋን ለመውጣት በሚያደርገው ሙከራ እንደልቡ ከውጭ መንግሥት በመላላክ የራሱን አቅዋም ለማጠንከር ይጣጣራል ። ከዚህም በኋላ ምን አልባት በታሪክ ፊት ይወቀባል እንጂ ለጊዜው ተቀጣ የሚለው ኃይል የለም ።

ያፄ ዮሐንስ ሥልጣን ይበልጥ በተስፋፋበት በተለይ በትግሬና በመረብ ባሻገር የሐጼጋው ራስ ወልደ ሚካኤል ለሹም ተምቤን ምርጫ ልጅ አልታዘዝም ብለው ምጥዋ አካባቢ ለሚገኙት ለግብጾች ገብተው ዐፄ ዮሐንስን ይወጉ ነበር ። ደጃች ደብብ ያፄ ዮሐንስ እኁት የትልቁ ራስ አርአያ ልጅ ላፄ ዮሐንስ አልገዛም ብለው የኢጣልያኖቹ ዋና መሣሪያ ነበሩ። ጣልያኖች አሥመራ ሲገቡ ዋናው መሪ እርሳቸው ነበሩ ። ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ራስ መንገሻ የትግሬን ግዛት አስመርቀው በሚገዙበት ጊዜ የአጋሜው ባላባት ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስ ተፈሪ ፥ የራስ መንገሻን የበላይነት በመቃወም ለኢጣልያኖቹ ገብተው ዋና ባለሟል ሆነው ስብሐት የእንደርታን ፥ ሐጎስ የአጋሜን አውራጃ ተሾመው እንደነበር የሚታወስ ነው ። እንደዚሁም በጎጃም ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር የተቀያየሙት ልጆቻቸው ራስ በዛብህና ደጃች በለው ፥ ካፄ ዮሐንስ ጋር የተጣሉት እነደጃች ሥዩም አባኃያል ወደ ሸዋ መጥተው ካፄ ምኒልክ ጋር ይኖሩ ነበር ። የሸዋን ዙፋን የሚፋለሙት መርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤል ከፈረንሳይ ሰዎች ጋር ሲጻጸፉ ደጃች መሸሻ ሰይፉ



ደግሞ ምኒልክን ለመቃወም ወዳፄ ዮሐንስ ጠጋ ብለው ነበር ። በዚህ ዓይነት የከዳተኝነቱና የታማኝነቱ ጉዳይ በዚህ ዘመን ከዕለት ጥቅምና ከግል ምኞት ጋር የተያያዘ ነበር ። በያንዳንዱ ዘንድ ያገር ፍቅር ቢኖርም ፥ ነገሥታቱ በበለጠ ያገር ፍቅር የሚያድርባቸው የመንገሥ ፍላጎታቸውን ካሟሉና ሙሉውን የንጉሠ ነገሥትነትን ሥልጣን ከያዙ በኋላ ነው ። ከዚያ በፊት ግን ፥ የዙፋን ባላንጣውን ለማጥቃት ቢል ሁሉም ከአገር ጠላት ጋር እስከ መወዳጀት ይደርሳል ማለት ነው። በዚህም ዓይነት ነገሩ በትክክል ከታሰበ ዐፄ ዮሐንስም ፥ ዐፄ ምኒልክም ፥ ራስ መንገሻም ዳኛ ከተገኘ ሁሉም የሚያስጠይቃቸውን ሠርተዋል ማለት ይቻላል ።

ስለዚህ ፥ የኢጣልያ መንግሥት እ.ኤ.አ. በ1879 ዓ.ም. አሰብን ከሩባንቲና ኩባንያ በግዥ ፥ በ1885 ዓ.ም. ምጥዋን በወራሪነት ከያዘ ወዲህ በየጊዜው ወደፊት እየገፋ በሐማሴን ፥ በአከለ ጉዛይና በሠራዬ በመስፋፋት ከዚያም ለመግፋት አቅም እንዳልነበረው ሲረዳ በውጫሌ ውል እሳቦ እስከ አሥመራ ድረስ ያለውን ለመያዝ እንደቻለ ግልጽ ነው ። ከዚህ በኋላ የኢጣልያ መንግሥት በዚህ ባይወሰን በየአውራጃው ጣልያኖቹን የበላይ ፥ ያገር ተወላጆቹን መኳንንት የበታች አድርጎ እየሾመ ፥ ካገር ተወላጅ ውስጥ ለወታደርነት እየመለመለ መለዮ ፥ ኮትና ሱሪም እያሰፋ ፥ የወር ቀለብ እየወሰነ በመስጠት በባታዮ የተከፋፈለ ልዩ ልዩ ያገር ተወላጅ የጦር ወታደር አቋቁሞ ነበር ። ከራሱ የመንግሥት መሪዎች ምንም አበል የማያገኘውም ወታደርና ባላገር በዚህ አበልና ጥቅም እየተደለለ ወደ ጠላት ይሔዳል ።

ለነዚህም ሁልጊዜ አዛዡ ኢጣልያዊው መኰንን ሲሆን ፥ ካገር ተወላጅም ውስጥ እየመረጠ "ሙንጣዝ ፥ ቡልቅ ባሻና ባሻ ብዙቅ" እያለ እየሾመ ቅጥረኛውንም በምጥዋ ፥ በጊንዳ ፥ በአሥመራ ፥ በከረን ፥ በከሰላ ፥ በአዲ ውግሪ ፥ በሰገነይቲና በአዲ ቀይሀ እየደለደለ ያስቀምጣል ። በአስፈለገበት ጊዜና ቦታ እየላከ ከነራስ አሉላና ከነራስ መንገሻ ጋር ሲያዋጋቸው ኖሯል ።

የወር ቀለባቸው ፤ ለእግረኛ ወታደር በቀን አንድ ፍራንክ* ከሃምሳ ሳንቲም ፥ ለመድፈኛና ለፈረሰኛ ወታደር በቀን አንድ ፍራንክ ከሰላሳ ሳንቲም ፥ ለሙንጣዝ በቀን አንድ ፍራንክ ከዘጠና አምስት ሳንቲም ፥

* በዚሁ ጊዜ አንዱ የማሪያቴሬዛ ብር ባገር ውስጥ ፍራንክ አምስት ሊሬ መመንዘሩንና ይህ ምንዛሬ በየወደቦቹ ላይ የሚለዋወጥ መሆኑን ዶ.ሉሲ.ባር ያመለክታል ። ጽሑፉ ፍራንክ ያለው በፈረንሳይ እንጂ በኢጣልያኖቹ ሊሬ ነው ።

ለቡልትባሽ በቀን ሁለት ፍራንክ ፣ ከሠላሳ አምስት ሳንቲም ፣ ለባሻ ባዡቅ በቀን አምስት ፍራንክ ይከፈላቸዋል ።[1]

ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ፣ የኢጣልያ ጦር መረብን አልፎ ወደ አጋሜ ፣ ወደ እንደርታ እየገባ በአዲግራት ፣ በእንትጮ እየመሸገ በተቀመጠበት ሰዓት እነዚሁ ያገር ተወላጆች ባለቆቻቸው የኢጣልያ ሹማምንት እየተመሩ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር በኮአቲት ፣ በሰንዓፌ ፣ በደብረ ኃይላ ያደረጉትን ውጊያ ፣ በኋላም በአላጌና በመቀሌ ከነራስ መኰንን ጋር ያደረጉትን ጦርነት ሁሉ በየምዕራፉ አንብበነዋል ። ያገር ፍቅር በአውሮፓው ዓይነት ባልተሰበከበት በዚህ ዘመን እነዚህ ሁሉ ያገር ተወላጆች ለጠላት ተቀጥረው ሲዋጉ ፣ ሲሞቱም ፣ ሲገደሉም አገርንና ወገንን መክዳታቸው በትክክል የሚታወቃቸው አይመስልም ። ዘመኑ "ላለበሰኝና ላበላኝ ጌታዬ እሞትለታለሁ" የሚባልበት ዘመን ነው ። የኢኮኖሚ አለመስተካከል ፣ የልማትና የሕግ እጦት ፣ የጉልተኛነቱ ዘመን ራሱ ይኸን ያሰኛል ።

የዓድዋ ጦርነት የተደረገ ዕለት ፣ ከኢጣልያኖች ጋር ግንባር ቀደም ሆኖ በጄኔራል አልቤርቶኒ አዝማችነትና በሌሎቹም አዝማቾች ውስጥ ተሰልፎ ወገኑን የተዋጋው ያገር ተወላጅ ቁጥሩ 6000 ይደርሳል ። እነዚህም በመካከላቸው አንድ አንድ የሱዳን ተወላጅ ቢኖርም ፣ አብዛኞቹ ግራዝማች ዮሴፍ በደብዳቤአቸው እንደ አመለከቱት ፣ ከሦስት የደጃዝማች አገሮች ከሐማሴን ፣ ከሠራዬና ከአከለ ጉዛይ ተሰብስበው የሰንዓፌንና የኮዓቲትን ፣ የአምባ አላጌንና የመቀሌን ጦርነት የተካፈሉ ናቸው ። አሁንም በአለቆቻቸው እየተመሩ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. በተደረገው የዓድዋ ጦርነት በኪዳነ ምሕረት ፣ በአምባ ራዓዮ ተዋግተው ብዙ የኢትዮጵያን ጦር ፈጅተዋል ። እንዲያውም በኮንቲ ሮሲኒ መጽሐፍና በሌሎችም እንደሚገኘው የነጩ ወታደር በመንገድም ፣ በረኃብና በውሀ ጥምም እየደከመ ለውጊያ ሲላላ እነርሱ በብርታት እየተዋጉ በብዙ ወገኖቻቸው ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሰዋል ። ከጋልያኖ ጋር በመቀሌ ምሽግ ሲዋጉ ቆይተው በኋላ ወጥተው ከርሱ ጋር ተለቀው የሔዱት የዓድዋ ጦርነት ለት እየፎከሩ በሚያስደንቅ አኳኋን ተዋግተው ጉዳት ማድረሳቸውን ኮንቲ ሮሲኒ የመዘገበውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ።

---

1 Douze an en Abyssinie De. Laulibar P.84



የሆነ ሆኖ ፣ ድሉ የኢትዮጵያውያን ስለሆነ ጣልያኖቹና እነዚሁ በኢጣልያ የተመለመሉ ያገር ተወላጅ ወታደሮች ግማሾቹ በሞትና በሽሽት ሲያመልጡ ግማሾቹ ተማረኩ ። ዐፄ ምኒልክ የካቲት 24 እና 25 ቀን ሬሳ በማስለቀምና በማስቀበር የሁለት ቀን ጊዜ ካሳለፉ በኋላ ፣ በነዚህ በተማረኩት ያገር ተወላጅ ወታደሮች ላይ ለመፍረድ በየካቲት 25 ቀን ችሎት አደረጉ ። በነርሱ ላይ ዐፄ ምኒልክ የእስራት ቅጣት ብቻ ለመፍረድ አስበው እንደ ነበርና በዚሁ እቴጌ ጣይቱ ፣ አቡነ ማቴዎስ ፣ ራስ ወሌና ይልቁንም ከነርሱ ጋር ሲዋጉ የኖሩት ራስ መንገሻና ራስ አሉላ አይሆንም ብለው እንደ ዘመኑ ከፍ ያለ ቅጣት እንዲቀጡ እንዳስፈረዱባቸው በየመጽሐፉ ተጠቅሶ ይገኛል ። በተለይ ራስ መንገሻ ፣ "የነዚህ ከዳተኞች እጅና እግራቸው ይቆረጥልኝ" ብለው ላፄ ምኒልክ አጥብቀው አቤት ማለታቸውን ግዚሜኔስ የሚባለው የኢጣልያ የጦር መኰንን መዝግቦታል ።[1]

ስለዚህ ፍርድ በኢጣልያን ጦር ውስጥ ሆኖ ዐሥራ ሁለት ዓመት ያገለገለው ዶ ሉሊባር የሚባለው በበኩሉ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ጽፎ ወደ አማርኛ የተረጐምነውን ከዚህ ቀጥሎ እንመልከት ።

> የቀብሩ ጉዳይ ካለቀ በኋላ ፣ ከጦርነት በተማረኩት አንድ ሺ ሁለት መቶ ያገር ተወላጅ ወታደሮች ላይ ስለሚሰጠው ፍርድ ንጉሡ ታላላቅ የመንግሥቱን አለቆች ሰበሰቡ ። ምኒልክ በጠባያቸው ምሕረትን የሚወዱ በመሆናቸው ቅጣቱ ቀላል ይሁን የሚሉት ወገኖች ዋና መሪ ነበሩ ። ነገር ግን እቴጌ ጣይቱ በራስ ወሌ ፣ በራስ መንገሻ ፣ በራስ አሉላ ፣ በአቡኑም እየተደገፉ እነዚህ በፈቃዳቸው በኢጣልያ ተቀጥረው ራስ መንገሻን ፣ ራስ አሉላን ፣ ደጃች ባሕታ ሐጐስን ሲወጉ የኖሩ አሁንም የንጉሠ ነገሥታቸውን ጦር የፈጁ ስለሆኑ ሞት እንጂ ምሕረትና ይቅርታ አይገባቸውም ብለው ተናገሩ ።
>
> በዚህም ብዙ ክርክር ሲደረግ ከቆየ በኋላ ፣ አብዛኛው መኳንንት የጣይቱን አሳብ ስለደገፈ እግራቸውን የከዱ ፣ ወገናቸውን የወጉ ናቸውና ፍትሐ ነገሥት እንደሚለው ይፈረድባቸዋል ብሎ ጉባዔው ወሰነ ። ፍትሐ ነገሥቱም አገሩን የከዳ ቀኝ እጁና ግራ እግሩ ይቆረጣል ስለሚል ይኸው ቅጣት ተፈጸመባቸው ። 2

እነዚህ ያገር ተወላጅ ወታደሮች የዕለት እንጀራና ቀለብ ለማግኘትም ሲሉ ፣ ካገራቸው መሳፍንትና መኳንንት ከነራስ መንገሻ ፣ ከነራስ አሉላ ጋር ሆነው ከሚያገኙት የበለጠ ፣ ከኢጣልያኖች ጋር በመሆን ቀለብና ልብስ በማግኘት የተሻለ ምቾት ተስምቷቸው

---

1: Sul Campo Di Adua - PP. 35 - 36.
2: Douze ans en Abys. P. 623; I Riccordi di un prigionre di'Meoelik,
C. Tedone, PP.44-48-; Menelik II Le Relazioni con L' Italia,E. Falcone,P.133

ነበር ። የኢጣልያ መንግሥት ያሉበትን አገርና አካባቢውን ስለ
ያህ ፣ "ምንም ቢሆን ራስ መንገሻም ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ምኒልክም
ፈረንጅን ተዋግተው ሊያስለቅቁት አይችሉምና ለኑሮ የሚያዋጣው
ጣልያኖቹን ማገልገል ነው" ብለው በማመንና በመዋጋት በመጨረሻ
እዚህ ዓይነቱ አሠቃቂ ቅጣት ላይ ለመውደቅ መብቃታቸው ያሳዝ
ናል ።

ግራዝማች ዮሴፍ ፣ ለሙሴ ሞንዶን ባስተላለፉት ራፖር ላይ ስለነ
ዚህ የአገር ተወላጅ ምርኮኞች እንደዚህ ሲሉ ጠቅሰዋል ። "ባሻ
ባዙቆች ግን ጦርነት ሲጀመር ባዩ ጊዜ ምንም ገንዘባቸውን ብንበላ
አገራችንንና ንጉሣችንን እንወጋም ብለው አስቀድመው ሸሹ ። የቀረ
ውን እላጌ ላይ የተማረከውን ምረውት ነበርና በድሉ (የጦርነት ዕለት)
የተገኘው ብርቱ ቅጣት ተቀጣ ።"

ከአላጌ ጦርነት ወዲህ ንጉሠ ነገሥቱ በትግሬ ግዛት እንደገቡ ፣
"...ከጠላቱ ጋር ሆነህ የወጋኸኝ ያገር ተወላጅ ወታደር እይቀጡ
ቅጣት እቀጣሃለሁ ፣ እርስትህን እነቅልሃለሁ" የሚል ዓዋጅ ዓውጀው
በዚህም ዓዋጅ መሠረት ፣ እነራስ ስብሐት መጥተው እንደ ገቡላ
ቸው እንብበናል ። የዐድዋ ጦርነት ዕለት በግራዝማች ዮሴፍ ራፖር
እንደ ተገለጸው ፣ ግማሾቹ ወገኖችንን እንወጋም ብለው የሸሹት በዚሁ
ምክንያት መሆን አለበት ።

ነጋድራስ አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ ፣ ዳግማዊ ምኒልክን በብዙ ረገድ
ካመሰገኑ በኋላ በነዚህ ያገር ተወላጆች ላይ በተሰጠው ፍርድ ብቻ
ነቅፈዋቸዋል ።[1] ነቀፋቸውም የሰው አእምሮ የሚቀበለው ትክክለኛ
ነቀፋ ነው ። ነገር ግን ዐፄ ምኒልክ በዚያን ሰዓት ለነዚያ የጠላት
ወታደሮች ቅጣቱ ይቅለልላቸው ባሉበት ጊዜ በሐሳብ ያልደገፏቸውን
እቴጌ ጣይቱንና ራስ ወሌን በተለይ ደግሞ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከ
ታቸውን ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ተቃውመው ለነዚህ ፣ "የቀለለ
ቅጣት ይሰጥ" ብለው በንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣናቸው ቢያዙ
ኖሮ በላያቸው ላይ ቅርታ ሊፈጥርባቸው ይችል ነበር ። ቅርታውም
መንግሥታቸውን ሊያናጋባቸው ይችላል ። ራስ መንገሻንና ራስ
አሉላን ወደ ጭከናው ያዘነበላቸው ፣ ባለፈው ዓመት በኰዓቲትና በሰን
ዓፌ ጦርነት ጊዜ ያገር ተወላጁ የኢጣልያ የቅጥር ወታደር በነርሱ ወታ
ደርና ሹማምንት ላይ በውጊያ ያደረሰውን ጉዳት በማስታወስ ነው ።

እንደዚህ በመሰለ ጉዳይ ፣ በሥልጣናቸው በመጠቀም ከራሶቻ
ቸው የተለየ ውሳኔ ማድረግ በዳግማዊ ምኒልክ ዘንድ የተለመደ አይደለም

---

1 ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ፡ ፡ ፡ ገጽ 102—106



እንዳንድ ጊዜ ራሶቹ በርሳቸው ሲመሩ ብዙውን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ
በራሶቹ ፈቃድ ይመራሉ ። ይኸን የመሰለው አቀዋም ሁሉን ባንድነት
አስተሳስሮ የዓድዋን ድል ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ዘመናቸውም ዘመነ
ሰላም እንዲሆን ረድቷቸዋል ።

በፍርድ ሰዓት ፣ በችሎቱ አደባባይ በንጉሠ ነገሥቱ ዥርባ የዓድዋ
ለት ሲዋጉ የዋሉት መኳንንትና ወታደሮች አለቃቸው ፣ ዘመዳቸውና
ጓደኞቻቸው የሞቱባቸው ሁሉ "ይቆረጡ ይቆረጡ" እያሉ ያውኩ
ነበር ይባላል።[1] እነዚህንም እምቢ ብሎ ማሳዘኑና የፍትሐ ነገሥቱንም
ቃል ለውጦ ማሻሻሉ በዚያን ጊዜ አስቸጋሪ ነው ። በሁኔታው ፍርድ
ሊሰጥ የሚገባው በዛሬው መንፈስ አይደለም ። በዚያን ዘመን ሁኔታ
ብቻ ሳይሆን በዚያን ቀን በነበረው የንዴትና የቁጭት መንፈስ ነው ።
ፍርድ የተደረገው ከጦርነቱ በኋላ በሁለተኛው ቀን ነው ። ይኸም
ቀን ሬሳው ተሰብስቦ እንኳን ያላለቀበት ቀን ስለሆነ ፣ በጸጥታና በጽሞና
ወንጀልንና ቅጣትን እመዛዝኖ ትክክለኛ ፍርድ መስጠቱ አዳጋች
ሆኖ የሚታይ ይመስላል ።

ስለዚህ የሚዛናዊውን ፍርድ የቁጭትና የንዴት ስሜት ተጭኖ
በዛሬ አእምሮአችን ሊያስቅቀን የሚችለውን ቅጣት ያን ጊዜ በእነ
ዚህ ባልታደሉ ሰዎች ላይ አስፈጽሟል ። ይኸን የመሰለው ቅጣት
ዋናዎቹን ባላጋራዎች ጣልያኖቹን ስላልነካ ለጠላቶቻቸው የሚላሉ ፣
በወገኖቻቸው ላይ የሚጨክኑ ፍርደ ገምድል አስመሰሏቸዋል ። የዚህ
ዓይነቱ ቅጣት እንኳን ጣልያኖቹን ተቀጥረው የተዋጉትን ሱዳኖቹን
እንኳን አላገኛቸውም ። የፍርዱ መሠረት እነዚህ ወገናቸውን የከዱ
ሲሆኑ ፣ እነዚያ ግን ጠላትነታቸው የታወቀና መንግሥታቸው አዟቸው
ነው ፤ አይፈረድባቸውም የሚል ነው ።

---

1 Empress Taytu and Menilek II Chris Prouty — p. 158.

# ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

## የምሥራቅ ለሙሴ ሞንዶን—የስሞታ ደብዳቤ ለርም ጳጳስና ለመስኮብ ንጉሠ ነገሥት

ዘመኑ የነጭ ዘር የገነነበት ፡ ሥልጣኑን በእስያም ፡ በአሜሪካና በአፍሪካ የዘረጋበት መሆኑ ግልጽ ነው ። በተለይ ከአምስቱ ክፍለ አህጉር በማናቸውም ረገድ ወደ ኋላ የቀረው አፍሪካ ለተገዥነት የተጋለጠ ነበር ። ቀደም ብለው ኃያላኖቹ እየተሽቀዳደሙ በመፋለም በፋሾዳ እንደ ደረሰው ፡ ለውጊያ እየተፋጠጡ አንዳንድ ጊዜም እየተዋጉ ቆዩ ። በመጨረሻ ደግሞ ፡ አፍሪካን በጠብና በውጊያ በመያዝ ፈንታ በሰላምና በስምምነት እንከፋፈል ብለው እ.ኤ.አ. የካቲት 26 ቀን 1885 ዓ.ም. በ38 አንቀጽ ላይ የሠፈረ የርስ በርስ ውል በጀርመን ከተማ በቤርሊን የተዋዋሉት ይታወሳል ። ዘመኑ እንኳን የብዙ ጦር መመታትና መሞት ፡ የብዙዎች በምርኮ ተይዞ እንደ መንጋ መነዳት ይቅርና ያንድ ነጭ በአፍሪካ ውስጥ መቁሰል ከዚያም አልፎ መገደል ያንን ነጩ የሞተበትን አገር በኃይል ለመያዝ እንደ በቂ ምክንያት ያስቆጥር እንደነበረ ግልጥ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፡ ምንም እንኳን የአጥቂነቱና የወራሪነቱ በደል ከኢጣልያ ወገን መሆኑ ቢታወቅም ፡ በዓድዋ ዘመቻ በኢጣልያን ጦር ላይ በድል አድራጊነት በመውጣትና ከፊሉን በመግደልና በማቁሰል ፡ የቀረውንም በመማረክ ስለ አዋረዱት ፡ የነጭ ዘር ሁሉ በዚሁ ተናዶ እንዳይዘምትባቸው ሥጋት ያደረባቸው ይመስላል ። በእርግጥም የዚህ ጦርነት ውርደት በቅኝ አገዛዝ ሥር ለወደቁት የደስታና የእለኝታ ስሜት ሲያሳድር ፡ በገዥዎች ዘንድ ውርደትንና ኃፍረትን ማሳደሩን ፡ በተለይ በእንግሊዞችና በጀርመኖች ዘንድ የደረሰውን የጸጸትና የበቀል ስሜት ተመልክተናል ። በኢጣልያም አገር በመንግሥቱ መሪዎች ዘንድ ተሸንፎ መታረቁ መራራ ጉርሻ ሆኖባቸው ነበር ። እንደገና "ከቀድሞው የበለጠ አጥፍ ጦር ይላክ" እያሉ ሲወተውቱ ፡ አዲሱን ካቢኔ ለማቋቋም የተመደቡት ባለሥልጣኖች ፡ የእርቅ እጅ መዘርጋት ግዴታ የሆነባቸው ሌላ የመውጫ መንገድ ስለጠፋ እንጂ በልብ ፈቃድ አለመሆኑ ግልጽ ነው ። በዚሁ ጊዜ ኤድዋርዶ ስካርፎሊዮ የሚባለው ጸሐፊ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ማርኬዝ ዲ ሩዲኒ አንቶኒዮ

ስታራባ ካ፦ ምኒልክ ጋር በመልእክት የእርቅ ድርድር ለማድረግ መወሰኑን በሰማ ጊዜ ፣ ለሮማ ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት የሚከተለውን ጽፎ አስተላልፎአል ።

> የሐበሻ ኢትዮጵያ በመሆን ፋንታ የኢጣልያ ኢትዮጵያ እስከ አልሆነች ድረስ ማናቸውንም መፍትሔ አልቀበልም . . . ባንድ አሽ ናፊ ጠላት ፊት የሚሸሽ ንጉሥስ ምን ይረባናል? ኢጣልያ ጦርነቱን ካልፈለገች በወገቧ አጕንብሳ ላሸናፊው አረመኔ (የኢትዮጵያ ንጉሥ) እጅ መንሣት አለባት ። ስለዚህም የጦር ሠራዊት ድርጅታችንና የመር ክብ ኃይላችን ይፈታና እኛንም የሮማው ሊቀ ጳጳስ ያስተዳድረን ፣ የቀረው ቢቀር በልባችን ከእንግሊዝ ቅኝ አገር የሰፋውና የታመመው ልባችን መድኃኒትና ሰላም ያገኛል ።[1]

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፣ ባገር የውስጥ አስተዳደር ጣጣ የተከበቡት ዳግማዊ ምኒልክ በዓድዋ ድል አድራጊነት መንፈሳቸው ቢረካም የዠኔራል ባልዲሠራ አዲስ ጦር ይዞ ምጥዋ መግባት ደስታቸውን ጥር ጣፊ ባለበት ሥጋት በርዞታል ። ከሁሉ የበለጠ በኢጣልያኖች መሸ ነፍ ጉዳይ ይነስ ይብዛ አውሮፓውያን ሁሉ በዘርና በቀለም አንድ ነት ምክንያት በነገሩ መታመም ገብቷቸዋል ።

በተለይ "እንግዲህ ንጉሡ ተሸሮ ፓፓው ያስተዳድሩን" ብሎ ስካር ፎሊዮ የጠቀሳቸው የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በመላው የኢጣልያ ሕዝብና በካቶሊክ አገሮች ሁሉ ተደማጭነት ያላቸው ስለሆኑ ምኒልክም የልባቸውን ወቀሳ ለርሳቸው በደብዳቤ ገልጸዋል ። በዚህ ጊዜ የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የቀድሞ መጠሪያ ስማቸው ዮአኪም ፒቹ በስመ ጵጵስና ሊዮን 13ኛ የተባሉት ናቸው ። እርሳቸውም እ.ኤ.አ. ከ1878 እስከ 1903 ዓ.ም. ድረስ የሮማ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ተብለው በመን በረ ጴጥሮስ ተቀምጠዋል ። ለርሳቸው ምኒልክ ሮሮአቸውን ለመግለጽ የላኩት ደብዳቤ ለመስኮብ ንጉሥ ከጻፉት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ እዚህ ላይ ማስፈሩን ትተን ለሞስኮብ ንጉሥ የጻፉትን ደብዳቤ በዚሁ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ አስፍረነዋል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዓድዋ በዘመቱበት ሰዓት አዲስ አበባን የሚጠብቁት አጐታቸው ራስ ዳርጌ መሆናቸውን ፣ እርሳቸውም አዲስ አበባ ባሉት ፈረንጆችና በንጉሠ ነገሥቱ መካከል ሆነው ከንጉሠ ነገሥቱ ለፈረንጆቹ የሚላከውን ፣ ከፈረንጆቹ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የሚ ሔደውን በመቀበል ያስተላልፉ ነበር ። እንደዛሬ የስልክ መስመርና

---

1 Abyssinia (1888 - 1896) E. Scarfolio, vol. II PP. 253-258; Gli Italiani in Africa Orientale, A Del Boca, PP. 706 - 708.



የሬዲዮ መገናኛ በሌለበት በዚያን ዘመን መልእክቱ ሁሉ በእግረኛና በጋማ ከብት በተቀመጡ የሰው መልክተኞች ብቻ እንደነበረ የታወቀ ነው ። ለዚህ ግን ፣ የተደራጀ የአዋላና የፖስተኛ አመላላሽ ነበረ ። ለማንኛውም የዓድዋን ድል እነራስ ዳርጌ በስንተኛው ቀን እንደሰሙ እናውቅም ። ምናልባት እንደ ጉዳዩ ትልቅነት መልክተኛው ፈረስ በመለዋወጥ ወሬው ባጭር ጊዜ ውስጥ ደርሶ ይሆናል ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከዘመቱበት ከጥቅምት ወር ጀምረው እዋናው ከተማ በቀሩትና በሌላውም አውራጃ ባሉት አገራቸውንና ንጉሣቸውን ወዳ ጆች ዘንድ ሐዘንና ጭንቀት እንደነበረ ፣ በየአብያተ ክርስቲያኑና በየገዳማቱ ጸሎትና ምሕላ እንደሚያዝ እርግጥ ነው ።[1] ስለዚህ በዚ ያው በጭንቀቱ መጠን አሁን ደግሞ የድሉ ወሬ ሲሰማ ደስታው የዚያን ያህል መሆን አለበት ። የዚህን ሁኔታ የሚዘረዝር ጽሑፍ ደራ ሲው አላገኘም ። የዚህንም የድል ብሥራት ያበሠረው ለራስ ዳርጌ የተጻፈው የንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ እንደሚሆን የታወቀ ሲሆን ፣ ደብ ዳቤው የት እንደሚገኝ አይታወቅም ወይም በፍጹም ጠፍቶ ይሆናል ። በሌላ በኩል ግን ለሙሴ ሞንዶን ቢዳዬ ንጉሠ ነገሥቱ የጻፉለት የምሥ ራች ደብዳቤ በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት የተገኘው እንደዚህ የሚል ነው።

> ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚ አብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን እንዴት ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። የምሥራች በእግ ዚአብሔር ቸርነት የየካቲት ቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት ኢጣልያንን ድል አድርጌ መታሁት ። አልሆን ስፍራ ላይ ካብ ከቦ ለጦርነት አልመቸኝ ብሎ ነበር ። ሠራዊት ቢራብብኝ ዓድዋ ላይ ስፍሬ ሠራዊቱን ቀለብ ሰድጄ ተበትኖ ሳለ ፣ ያን ሲሰማ ሌሊት በጨረቃ ሲገሠግሥ አድሮ እስፈሬ ድረስ መጥቶ ገጠመኝ ። እምላከ ኃያላን ረድቶኝ ፈጀሁት ። ደስ ብሎኛል ደስ ይበልህ ። መጋቢት በ3 ቀን በእንትጮው ሰፈር ተጻፈ በ1888 ዓመተ ምሕረት ።

እንደዚሁም ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የጻፉት እንደዚህ የሚል ነው ።

> ይድረስ ከወዳጄ ከሙሴ ሞንዶን ። እንዴት ነዎ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። የምስራች ኢጣልያኖችን ዳግመኛ እንዳይነሡ አድርገን ድል መታናቸው ። ታሪኩም እንዲህ ነው ። እንትጮው ከሚ ባለው አገር ላይ ካብ ከቦ ለጦርነት የማይመችን ቢሆን ወደ ሐማሴን ልንገዝ ዓድዋ ላይ ስፍረን ሳለ ፣ ሠራዊት ተርቦ ነበርና እህል ዘረፋ

---

1 መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፣ መንግሥቱ ለማ በዚህ መጽሐፍ ገጽ 145—146 የአለቃ ወልደ ያሬድ ጭንቀት የቀሩትንም እንመለከታለን ።

ሠራዊታችን እስከ ሽሬ ድረስ ተበተነ ። ኢጣልያ ግን ይኸን ቢሰማ እህል ዘረፋ የሔደው ሳይመለስ ልፍጀው ብሎ ሌሊት በጨረቃ ሲገሠግሥ አድሮ እሑድ የየካቲት ጊዮርጊስ እለት በአንድ ሰዓት ዐድዋ እፋፍ ላይ ዘለቀ ። የኛም ሰው እየተሰለፈ በየግንባሩ ሔዶ ከገጠመው ። ወዲያው መድፍና ወጨፎ ፣ የወዲሁ ውኸግራ በተተኰሰ ጊዜ የዚህን ግርማ እግዚአብሔር ያሳይዎ ኢርቱእ ናስተማስሎ (ከምን ጋር እናመሳስለው ዘንድ እንችልም) እንዳለው ልንተወው ይገባል ። ነገር ግን በየበሩ እንገት (ምቹ ሥፍራ) እየያዘ ከሶስት ላይ ተሰልፎ ነበር ። የፊተኛው ሲሻር ደግሞ ሁለተኛው ከቢ ገጠመን ። ደግሞ ይህ ሲሻር ሦስተኛው ከቢ ገጠመን ። ሦስተኛው ግን ሲሻር ሁሉም ጀርባ ሰጠ ። ወእርኃብኩ መከየድየ በመትህቴየ ወኢደከመ ሰኰናየ እንዳለው ሆነ ።[1] ወታደር እደከመ ድረስ እባሮ ሲመለስ ደግሞ ባላገር ተቀብሎ መረብ ድረስ ፈጀው ። ደግሞ ደልዳላውን ወሬ ከግራዝማች ዮሴፍ ደብዳቤ ያገኙታል ። በመጋቢት በ3 በዓድዋ ሰፈር ተጻፈ ።

ማኅተም ዘእለቃ ገብረ ሥላሴ

ዘውእቱ ጸሐፌ ትእዛዝ[2]

በዚህ ደብዳቤያቸው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፣ "የፊተኛው ሲሻር ደግሞ ሁለተኛው ከቢ ገጠመን ፣ ደግሞ ይህ ሲሻር ሦስተኛው ከቢ ገጠመን ፣ ሦስተኛው ግን ሲሻር ሁሉም ዠርባ ሰጠ. . ." ያሉት መዠመሪያ ግንባር ቀደም ሆኖ በእምባ ኪዳነ ምሕረትና በአባ ገሪማ በኩል የተዋጋውን የዤኔራል አልቤርቶኒን ጦር ነው ። "የፊተኛው ሲሻር ሁለተኛው ከቢ ገጠመን" ያሉትም ፣ የመዠመሪያው ብሪጌድ ጦር ከኋላ የተጠባባቂውን የዤኔራል ኤሌናን ጦር ጨምሮ በእምባ ራዓዮ የተዋጋውን የዤኔራል አሪሞንዲን ጦር ነው ። "ሦስተኛው ሲሻር ሁሉም ጀርባ ሰጠ" ያሉትም ፣ የሁለተኛውን ብሪጌድ ጦር ይዞ በማርያም ሸዊቶ የተዋጋውን የዤኔራል ዳቦርሚዳን ጦር ሲያስታውሱ ነው ። እንደ እውነቱ ግን ፣ ሁሉም በየግንባሩ የገጠመው የዤኔራል አልቤርቶኒም ፣ የዤኔራል አሪሞንዲም ጦር ዠርባውን እየሰጠ የሸሸው የራሱ ጦር እየተመታ በፈረሰበት በተለያየ ሰዓት እንጂ ፣ ሁሉም በያለበት የዘመተው ጦር ሲመሽ የፈረሰውን የዳቦርሚዳን ውጊያ አልጠበቀም ። ሁሉም በየበኩሉ የተዋጋውም ፣ የሸሸውም የሌላውን ዕድል ሳይጠብቅ በተለያየ መንገድ ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ የጻፉት ከእንትጮ ሲሆን ፣ ጸሐፌ ትእዛዙ የጻፉት ከዓድዋ ሆነው ነው ። ሁለቱም የጻፉበት ቀን አንድ ነው ። ምናልባት

1 የዳዊት መዝሙር 26.12

2 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቁ. 82 ፣ ደልዳላውን ወሬ ከግራዝማች ዮሴፍ ደብዳቤ ያገኙታል ያሉት ፣ ፍሬ ነገሩ ወደ አዲስ አበባ በተደረገው የመልስ ጉዞ ላይ ይገኛል ። ግማሹም ባለፈው ምዕራፍ ላይ የተወሳ ነው ።



ንጉሠ ነገሥቱ ከጦሩ ጋር ወደፊት ሲያልፉ ፣ ጸሐፌ ትእዛዙ የጦር ሰው ስላልሆኑ ወደኋላ ወደ ዓድዋ ከዋናው ጓዝ ጋር ቀርተው ይሆናል ። ዳግማዊ ምኒልክ የድል አድራጊነታቸውን ወሬ ለፈረንሳይ መንግሥትና ለመስኮብ ንጉሠ ነገሥትም ጽፈዋል ።

የመስኮብ መንግሥት ፣ ገና ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት በመፈለግ በ1878 ዓ.ም. መልክተኛ ልኮ ነበር ። አሁንም ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተቋረጠውን ወዳጅነት ለመቀጠል በ1887 ዓ.ም. ሊዎንቴቭ የሚባለውን አንድ ሐኪም አንድ የመድፈኛ ሹም ፣ አንድ የቤተ ክህነት ሰው ጨምሮ አዲስ አበባ ልኮ ዐፄ ምኒልክም ለዚሁ መልስ በዐድዋ ጦርነት ሕይወታቸውን የሠውትን ፊታውራሪ ዳምጠውን ዋና መልክተኛ አድርገው ልከው እንደነበረ የሚታወስ ነው ።

አሁን ዐፄ ምኒልክ ፣ በዓድዋ ኢጣልያኖችን አሸንፈው ወደ ከተማቸው ተመልሰዋል ማለትን ወሬ ስለሰሙ ፣ በመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ አንድ ዤኔራል ፣ አራት ከፍተኛ የጦር መኰንኖች ስድስት የፈረሰኛ ፣ ዐሥራ አንድ የመድፈኛ መኰንኖች ፣ ሐያ የሚሆኑ ዝቅተኛ መኰንኖች ፣ አራት ሐኪሞች ፣ አንድ የቤተ—ክህነት ሰው በድምሩ ዐርባ ሰባት የሚሆኑ መስኮቦች ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከንጉሠ ነገሥቱ ተገናኝተው እንደ ዘመኑ ለሁሉም ቤት ተሠርቶላቸው ተቀመጡ ። ሐኪሞቹም በትጋት ኢትዮጵያውያኑንና ኢጣልያኖቹን ቁስለኞች በማከም አገልግሎት አበርክተዋል ። ንጉሠ ነገሥቱም የወዳጅነትና የእርዳታ መልክ ያሳዩዋቸውን የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ኒኮላን ደስ ለማሰኘት ብለው በልደታቸው ቀን ሃምሳ የኢጣልያ ምርኮኞች በነጻ ለቀው በኮንት ሊዎንቴቭ መሪነት ወዳገራቸው በሰላም እንዲመለሱ አድርገዋል ።

በዚሁ ወዳጅነት ዳግማዊ ምኒልክ ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ መቀሌ በነበሩበት ሰዓት ስለዓድዋ ጦርነትና ስለድሉ አንድ ደብዳቤ ጽፈውላቸዋል ። ደብዳቤው ሲነበብ ከደስታና ከምሥራች ይልቅ የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶና መንግሥቱ በርሳቸው ላይ የዋለውን የግፍ ሥራ የሚገልጽ ነው ። ይኸም ምንም እንኳን የወዳጅ አገር ንጉሥ ቢሆንም ፣ ዞሮ ነጭ በመሆኑ ምናልባት ቅርታ እንዳይገባው ጦርነቱ ለማድረግ የተገደዱት ኢጣልያ በእብሪትና በግፍ ስለ መጣባቸው መሆኑን ለማመልከት ይመስላል ። የደብዳቤውን ትክክለኛ ግልባጭ ከዚህ እንደሚከተለው እናንብብ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ኒቆላዎስ ቄሳር ሁለተኛ ፤

ሰላም ለርስዎ ይሁን

ክቡር ንጉሠ ነገሥት ሆይ ፣

በዚህ ደብዳቤ የሚጻፈውን ግፌን አስታውቀዎታለሁ ። የኢትዮጵያን ነጻነቷን ፣ ራሷን የቻለች መንግሥት ባጠገቧም ወዳጅ የሌላት መሆኗ አስቀድሞ በሮፓ ነገሥታት ሁሉ የታወቀ ነው ። ከግራኝ ጀምሮ እስከ አሁን በአሕዛብ እጅ ተከባ ዘወትር በጦርነት ድካም ነው ኑሮአችን ። ከሮፓ የጦር መሣሪያ አስመጥቼ ሠራዊቴን ዘወትር ከጦርነት ድካም አሳርፋለሁ ስል ከንጉሥ ኡምቤርቶ አባት ጋር የፍቅርን ነገር ጀመርኩ ። ንጉሥ ኡምቤርቶም መንግሥት በያዙ ጊዜ እንደ አባቱ ፍቅርን እወዳለሁ ብለው ቢልኩብኝ እኔም እንዳባትዎ ታፈቀሩኝ እሺ ብዬ ፍቅርን ተቀበልኩ ። ኮንት አንቶኔሊ የሚባል የኢጣልያ ሰው በገንዘብዎ ጠበንጃ ልግዛልዎ ቢለኝ ብዙ የዝሆን ጥርስና ወርቅ ሰጥቼው ይዞ ሔዶ ከንጉሥ ኡምቤርቶ አስፈቅዶ ገዝቶልኝ ቢመጣ ከመንግሥት ፈቃድ በማግኘቱ እጅግ ደስ አለኝ ። ሁለተኛም ንጉሥ ኡምቤርቶ ኮንት አንቶኔሊን የመንግሥት መልክተኛ አድርገው ወደኔ ሰደዱት ። ተልኮ ያመጣውም ቃል ይህ ነው ። ነጋዴም እንዲነግድ የጦር መሣሪያ እንዳይከለከል ይፈቀድልዋል ። እርስዎም ባሪያ እንዳይሸጥ ያስከለክላሉ ። በሌላ መንግሥት ያለ መሣሪያ ሁሉ ብትፈልጉ በኛ በር ይመጣላችኋል አይከለከልም ። እንደ ሮፓ ነገሥታት የተጠላው ውል ባምስት ዓመት ይሰወጣል ፤ የተወደደው ይረጋል ። ምጥዋ ሐሩር ሆኖብናል ። ለሰዎች ማሳረፊያ ጥቂት ነፋስ ያለበት ስፍራ እንዲሰጡን የፍቅርን ውል ይህን እናድርግ ብለዋል አለኝ ። እሺ ይሁን ብዬ እኔም ለመንግሥቴና ለኔ የሚስማማ የሚጠቅም ቃል በአማርኛ በትክክል አድርጌ አስጥፌ ብሰጠው ዐሥራ ሰባተኛው ክፍል ላይ ቃሌን በኢጣልያ ቋንቋ ለውጠው ከጥንት ጀምሮ ነጻ የነበረውን መንግሥቴን የሚያዋርድ የማይስማማኝ ቃል ቢሆንብኝ እኔ ባስጣፍኩት በአማርኛው ቃል ይርጋ ፤ የኢጣልያ ቋንቋ ከኔ ከአማርኛው ጋር ያልተካከለ ነው ። አሁንም በትክክል እናድርገው ብዬ ወደ ንጉሥ ኡምቤርቶ ብልክባቸው ምላሽ ሳይሰጡኝ ቀሩ ። እኔም ነገሩ ለተንኮል እንደሆነ ዐውቄ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ አስቀድሜ ለሮፓ ነገሥታት ሁሉ ከንጉሥ ኡምቤርቶ በውሉ ነገር እንዳልተስማማን አስታወቅሁ የውነት ፍርድ አገኛለሁ ስል ። ሁለተኛም አምስት ዓመት ሲደርስ የጠላነው እንዲቀር የወደድነው እንዲረጋ ሰው ይላኩልኝ ብዬ ብልክ ፣ እስከ ወረቀቱም ምላሽ አስቀሩት ። ከዚህ ወዲህ ይልቅ ክፉ ነገር እየበረታ ሔደ ። አሽከሬን ደጃች መሸሻን አለፍርድ አሰሩት ። አገር አልፈው የሾምኩትን ሹም ራስ መንገሻን ወግተው አባረው አገሬን ትግሬን በሙሉ ያዙት ። ከዚያ አልፈው ላስታ መሬት እስከ እሸንጌ ድረስ ወጡ ። ከዚያ ወዲያ አገር የሚጠብቁ መኳንንቶች ከኔ ብሰድ ፣ አላጌ ላይ በር ይዘው ቆይተው ተዋጉአቸው ። የእግዚአብሔር ኃይል በኔ ሰዎች አድሮ ድል አደረጓቸው ። እኔም ወደዚያ ተከትዬ ብሔድ መቀሌ እርድ ገብተው አገኘሁ ። ጦርነት ከሆነ ከትልቁ



ጋር እዋጋለሁ እናንተ ክርስቲያኖች በውሀ ጥም አትለቁ ብዬ እስከ መሣሪያቸው ከእርድ አስወጥቼ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ሰደድኩለት ። እኔም ከዚያ ተጉዤ ዓድዋ አከተማዬ ስፍሬ ጄኔራል ባራቲዬሪ እውነት የመሰለ የእርቅ ቃል ላከብኝ ። እኔም እርቅ ከፈለጉ ብዬ ሠራዊቴን ቀለብ ሰድጄ ሳለ ፣ እንደ ሮፓ ነገሥታት ሥራት ሁሉ ጠብ መፈለጋቸውን ሳያስታውቁኝ *እንደ ወምበዴ ሥራት ሌሊት ሲገሠግሥ አድሮ ሲነጋ ግምባር ካደረው ዘበኛ ጋር ጦርነት ዠመረ ። ጥንት ከአሕዛብና ከአረመኔ አገራችንን ጠብቋት የሚኖር አምላክ ከኛ ባይለይ በእግዚአብሔር ኃይል ድል አደረኳቸው ። ከዚያ ሔጄ እሥመራንም የኔን አገር ሁሉ በሙሉ አስለቅቃለሁ ብዬ ተጉዤ ሳለሁ ጄኔራል ባልዲሠራ በኢጣልያ ሠራዊት ሁሉ ላይ ተሾሜ መጥቻለሁ ። ንጉሥ ኡምቤርቶም ሲሰዱኝ እርቅ ነውና እምፈልግ እርቅ አድርግ ብለውኛል ብሎ በማዦር ሳልሳ እጅ ወረቀት ቢልክልኝ ፣ እኔ በወደድሁት ከታረቃችሁ የሚስማማኝ ቃል ከሆነ እውነተኛ ሰው አዲስ አበባ አከተማዬ ድረስ ይምጣና ይጨርስ ብዬ እኔም ወደ ከተማዬ ተመለስኩ ። እስካሁን በትግሬ አለሥራት ያለቀው መኳንንትና ባላገር የሮፓ ነገሥታትና መኳንንት ሁሉ የተደረገውን ግፍ አመለከታለሁ ። የኢጣልያ ገንዘብ በላያችን ላይ የለብን ። ካገራቸውም ድምበራችን የራቀ ነው ። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ነጻነቱና እራሱን የቻለ መንግሥት የሆነውን በተንኮል ሊወስዱት እንዴት ይቻላቸዋል ። ይህንን የግፍ ፍርድ በሙሉ ልቦናዎ በውል እንዲመለከቱት ተስፋ አለኝ ። ኢጣልያኖች ግን ፣ ይኸን ሁሉ ግፍ ሲያደርጉብኝ እነሆ እኔ የማደርገው የነበረው እነሱን ማክበር ሲመጡ በሥራት መቀበል ፣ ሲመለሱ በሥራት መሸኘት ደግሞ በተሰጠኝ ሥልጣን ሁሉ የባሪያ ንግድ መከልከል በኔ መንግሥት አፈንዴ መሐመድ ብቻ የባሪያ ንግድ አልተው ብሎኝ ስለዚህ አውሳ ጦር ሰድጄ አሶጋሁት ። ይህ ፈቃድ የኔ ብቻ አይደለም የሞላ የአውሮፓ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ ። በመጋቢት 23 ቀን በመቀሌ ሰፈር ተጻፈ በ1888 ዓመተ ምሕረት ።[1]

* (Ultimatum) የጦርነት ማስጠንቀቂያ ሳያስቀድሙ ለማለት ነው ።

1 ማዳም ራይት ከሰጡኝ ሰነድ ውስጥ ገጽ 152—157



የጼ ምኒልክ አማካሪ ሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ
ከምኒልክ ኤኑ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

## የኢጣልያ ምርኮኞችና ወደ አዲስ አበባ ጉዟቸው

የካቲት 23 ቀን በተደረገው ጦርነት ተሸናፊው የኢጣልያ ወታደር ዕድሉ ከሦስት ላይ የተከፈለ ነበር ። ከፊሉ በጦርነት ላይ የቆሰለና የሞተ ፤ ከፊሉ ከጦርነቱ ላይ የሸሸ ፤ የቀረው ደግሞ የተ ማረከ ነው ። ከነኝህ ከሦስቱ መደቦች ለወታደሩ የትኛው እንደሚሻል ለማወቅ ሲፈለግ ለዝግንነትና ለታሪክ የሞቱት ሲሻሉ ነፍሳቸውን ለማዳን ደግሞ የሸሹትና የተማረኩት ናቸው ። ሸሽተው አሥመራ ከገ ቡትና እጃቸውን ሰጥተው በመማረክ እስከ አዲስ አበባ ከመጡት የየትኞቹ ዕድል እንደሚሻል በትክክል አይታወቅም ።

የእስረኞቹ በብዛት መማረክ ፤ ለኢትዮጵያ መንግሥት ለወደፊት የክርክር አቅዋም በጣም ረድቷል ። ጣልያኖች ቀድሞ እምቢ ያሉትን የውጫሌን ውል ለመሰረዝ የተገደዱትና አዲስ የመጣው የገኔራል ባልዲሠራ ጦር መረብን አልፎ እንዳያጠቃ ከመንግሥቱ መሪ ትእዛዝ የተቀበለበት ሰበብ አንዱም በምርኮኞቹ ምክንያት ነው ።

ምንም እንኳን የሚቹ ፤ የምርኮኛውና የሸሸው ቁጥሩ ገና ባይታ ወቅ የዘማቹ በተለይም የምርኮኞቹ ቤተሰቦች በተጫጫሁበት ሰበብ መንግሥቱ የምርኮኞቹን ሕይወት ለማዳን ሲል የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት በውል ለማወቅ የተገደደው ፤ በጦርነት ከመሸነፉ ጋር አንዱም ምርኮኞቹን ለመረከብ ይመስላል ። ቤላቪታ ፤ "በእስረኞቹ መለቀቅ በጣም አሥጊ ከነበረው ከእስረኞቹ ጉዳይ አገሪቱ (ኢጣልያ) ካንድ ቅዠት ነጻ ወጣች" ሲል አትቷል[1] ። ለኢጣልያ ሕዝብ የእስረኞቹ ጉዳይ እያያዘ የመንፈስ ዕረፍት አሳጥቶት ነበር ማለት ነው ።

የሆነ ሆኖ ፤ የጦርነቱ ዕለትም በማግሥቱም የተማረከው የኢጣልያ ወታደርና ሹማምንቱም ፤ እዚያው ዓድዋ ሳሉ በመጀመሪያ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንዲያልፉ ተደርጓል ።

ቴኔንቲ ሮቤርሲ ከማዦር ሳልሳ ጋር በእርቅ ሰበብ ከንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር አምስት ቀን በቆየበት ጊዜ የተመለከተውን ሲገልጽ ፤

---

1. Tante Anzie sulla sorte dei prigienieri . . Al paese parve di essersi liberate da un incubo, Adua, Bel. P. 445.

> በደረስንበት ቀን ገና ለሹማምንት ያልታደሉት እርዛትና ድካም ረኃብ ያጠቃቸው የኢጣልያ ምርኮኞች ወዲያና ወዲህ እያሉ ከሐበሾቹ ምጽዋት ይለምኑ ነበር ። ይኸንንም ማየቱ ለኛ ሥቃይ ሆኖብን ነበር ። . . .

ሲል በማስታወሻ ያመለክታል ።

ከሁሉ የበለጠ ስለ እስረኞቹ ጉዳይ ዘርዘር አድርገው የጻፉት ግራዝማች ዮሴፍ እንደ ተለመደው ለሞንዶን ቪዳዬ ባስተላለፉት ባንድ ራፖር ላይ ፤

> . . . ንጉሠ ነገሥቱ የተማረኩት ኢጣልያኖች በአንድ ሰው ትእቢት* በግድ ታዘው የመጡ ወታደሮች መሆናቸውን ያውቃሉና እንደ ሹመታቸው ሹማምንቱን ወታደሩን እንደ ማዕረጉ በሚገባ አድርገው ልብስ የሌለውን ልብስ አልብሰው የቆሰለውንም ከሞት የተረፉትንም ሐኪሞች ሰብስበው እያስታመሙ አስቀምጠውታል ።

የሚል ጽፈዋል ።

ከዚህ እያይዘው በመንገድ ላይና በሰፈር ላይ ሳሉ ፤ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ በኩል የተደረገላቸውን ቸርነት ሲያመለክቱ ፤

> . . . የጁ ስንደርስ ከላስታ የመጣው ምርኮኛ ሁሉ ከሰፈራችን ተቀላቀለ ። ጃንሆይም በያገሩ ዳቦ እስጋግሩ ብለው ግብር ሲያገቡ ለኢጣልያ ምርኮኞች ሁሉ ቀቅሉ እያሉ ባንድ ወገን ለኢጣልያ ወታደር ባንድ ወገን ለኛ ወታደር መንገድ ለመንገድ ግብር እያስገቡ ይዘውት መጡ ። የዛሬው ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ እቴጌ ጣይቱ ለኛም ወታደር ለኢጣልያም ወታደር የሠሩት የበጎነት ሥራ እያደረ የሚያስደንቅ ነው ። . . . ለኢጣልያኖችስ ያደረጉላቸው ርኅራኄ እናታቸውም ቢኖሩ እቴጌ እንደ ሠሩላቸው ርኅራኄና በጎነት የሚሠሩላቸው አይመስለኝም ። መንገድ ለመንገድ ስንመጣ ጧት ጧት እንዳይርባቸው ሠላሳ ከረጢት ዳቦ እየተቆረሰ ሰፈር እስኪሆን ድረስ መንገድ ለመንገድ ላገኙት ኢጣልያ ሁሉ ሲያድሉት ይውሉ ነበር ። ሰፈር ሲሆን የነዚያው ወጥ ከእቴጌ ቤት እየተሠራ ይሔድላቸው ነበር ። መንገድ ለመንገድ የኢጣልያ ቆብ ያደረገ ወታደርና ገረድ ያገኙ እንደሆነ እያስገፈፉ ቆብ ለሌለው ይሰጡት ነበር ።** የደከመውንም የታመመውንም የኛ ወታደር በእግሩ እየሔደ ከመንገድ ወድቆ እንዳይቀር አገር በሌለበት ሥፍራ ከመንደር እስኪደርስ ያስጉዙት ነበር ። አገር ሲደርስ በብርቱ ትእዛዝ በጣም እንዲያስታምሙ ደብዳቤ እየተጻፈ ተመራ ። ጧት ጧት ዳቦውን ከለመዱ በኋላ ቀን ሲርባቸው ስንጓዝ እቴጌን በሩቅ ባዩ ጊዜ የኢጣልያ ወታደሮች ሁሉ ኤኮ ኤኮ አልዳቦ (ባለዳቦዋ ያቻት) እያሉ ወደ እቴጌ ይሮጡ ነበር . . . እንደ ለማዳ አውሬ ግማሹ የእቴጌ አጀብ የኢጣልያ ወታደር ነበር ። የወንጌል ቃል በእቴጌ ሲፈጸም አየን . . .

ብለዋል ።

---

* ባንድ ሰው ትእቢት ታዘው የመጡ ያሉት ይህ ሰው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ እንደሆነ ይገመታል ።

** ከኢጣልያኖች የተማረከውን መለዮ የኛ ወታደርና ገረዶች አድርገው ሲሔዱ እያስጣሉ ለኢጣልያኖቹ ይሰጡ ነበር ማለት ነው ። የኢጣልያኖቹን ቆብ ገረዶች ሲያደርጉት ጣልያኖቹ ሳያፍሩበት አይቀሩም ።



በዚህ ዓይነት ፤ ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ የተጓዙት የኢጣልያ ምርኮኞች ፤ እነዚያ ልብሳቸው አልቆ በውስጥ ሱሪ የተጓዙት ፤ ጫማቸው አልቆ በሻሽ አስረው ፤ በመውደቅና በመነሣት በስንት ጣር ወደ እሥመራ የሸሹት የኢጣልያ ወታደሮች ፤ ከጦርነቱ በፊት ጦርነት ከልክ ያለፈ ያማራቸው ነበሩ ። የጦርነቱ ቀን በመራዘሙ የተበሳጩም ነበሩ ። ኢጣልያ አገር ላሉት ለዘመዶቻቸው ፤ "ከንጀራ ጠንካራ ነው ሺዎችን ለመፍጀት ቸኩያለሁ" ወይም "ሳልጽፍ የቆየሁት መጀመሪያ ካበሾቹ ጋር ተዋግቼ ዝግንነት ከሠራሁ በኋላ እጽፋለሁ ብዬ ነው" አንዳንድ ጊዜም ፤ "ባበሾቹ ላይ ዝግንነት ሠርቼ ኒሻን መሸለም አምሮኛል" የሚሉ በአሽናፊነታቸው የተማመኑ ፤ ዝብዱ ሠርተው ኒሻንና ክብር የናፈቃቸው እንደነበሩ ወደኋላ መለስ ብለን እናስታውስ ። አሁን ይኸ ሁሉ መና ቀርቶ ከናቁት ሠራዊት ምጽዋት እየለመኑ ፤ በናቁት ሠራዊት እየተነዱ የወታደርነት መለዮዋቸውን ገረድ አድርጋው ስትሔድ ሲያዩ በልባቸው እንደሚገረሙ የታወቀ ነው ። አንዳንዶቹ መኰንኖች አፋቸውን አውጥተው በጉዳዩ ተወያይተው ፤ ተሣሥቀውበት ወይም ተላቅሰውበት እንደሆነ አይታወቅም ። በታላቅ የሥነ ጽሑፍና የሥነ ጥበብ ሥራ የተደነቁት የነሚሽል አንጀሎ ፤ የነራፋኤል ወገን የሆኑት ጣልያኖች እንደ አንግሎ ሳክሶኖች ደስታንና መከራን በመሸከም ከበድ ብለው መታየት አይሆንላቸውም ።

አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ ፤ ስለ ምርኮኞቹ እኚሁ ያስተርጓሚ ጸሐፊ የሆኑት ግራዝማች ዮሴፍ ሲያትቱ እንደዚህ ብለዋል ።

> . . . አንድ ሻብጣን (ካፒቴን) አዲስ አበባ ላይ ታሞ ሞተ ። የቀሩት ወታደሮች በያገሩ ተመሩ ። ምግቡን እንደጠገበ አብሉ ብለው አዘዙ(ምኒልክ) ። ዛሬ ከባላገር ጋር በጣም ተስማምቷል ። ልብሱንም እንዳገሩ እየተሰፋ ሰጡት ። ሹማምንቱም ትልልቆቹም አዲስ አበባ የገባን ጊዜ በየሹማምንቱ ቤት ተመሩ ። ሰባት ሰባት ብር ደመወዛቸውን ሰጧቸው ። ቀለባቸውን ከጐተራ እያወጣ ሥጋ ሳይቀር መኳንንቱ እየተቀበለ ተጠንቅቆ ይቀልባል ። ከመንገዱም ላይ የኢጣልያው ሹማምንት የወደደውን እንዲገዛ ብለው አራት አራት ብር ሰጥተዋቸው ነበር ። ከገባን በኋላ እንደ ሹመቱ እንደ ትልቅነቱ ዐሥርም ዐሥራ አንድም ለትንሽ ስድስት ብር ላማራቸው ነገር መግዣ ሰጧቸው ።

በቀረው ሠራተኛው ሥራው እየተጠየቀ በየሥራው ለሠራተኛው አከፋፈሉት ። ደመወዙንም ምግቡንም እንደ ሥራው ሰጡት ። ደግሞ ከወዲያ አገር ፖስታ ሲመጣ ስማቸው እንዳይጠፋ ቢያሉበት አገርም ለመስደድ ስማቸውን አጽፈነዋል ። ለሠራተኛውና ለመኳንንቱ ልብስ ሁለት መዘውር* የኢጣልያ ስፌ ሲሰፋ ይውላል ። ጫማቸውም

---

* መዘውር የሚሉት ጣቃውን ይመስላል ።

ሲመጡ አልቆ ነበርና የእንጨት መዝገብ* እንደ የሮፓ ሥራ እነዚያ ጠርበው አበጅተው የነዚያ ሰፊና የኛው ሰፊ ወሳፍቻው እንደ ፈረንጆች ተበጅቶ ሲሰፉ ይውላሉ ። ማስም(ቀዳም) እገሩ ሁሉ እያለፋ ያገባል ። በገበያ ያለ እየተገዛ ይገባል ። በገበያ የተገኘው ባርኔጣ ሁሉ እየተገዛ በራስ በራሱ እየለካህ መርጠህ ውሰድ ብለውት እየመረጠ ሲወስድ ይውላል ።

ጄኔራል አልቤርቶኒን ግን ፣ ከእዛዥ ዛማኔል ቤት ማለፊያ ቤት ሰጥተውት ምንጣፉንም ፣ አልጋውንም ከምድር የሚነጠፈውም ምን ጣፍ የሌሊት ልብስም ሰጥተውታል ። የጄኔራል ባራቲዬሪ ወጥቤቶች ከወታደሩ ውስጥ ቢገኙ እንዳገሩ ወጥ እየሠሩ ያበሉታል ። እንደዛሬ ያለውን ጌትነት ከጭፍሮቹም መሐል አግኝቶት አያውቅም ። እርሱ ግን ቁጡ ሰው ነው ቢደላውም እንደሆነ አያውቅም ። ይህንም እንዳልል ዓድዋ ላይ የተማረከ ጊዜ ጃንሆይ ጠርተው ቢጠይቁት ይቆጣ ጀመር ። ጃንሆይ ግን "ቁጣ ትናንትና የጦሩ ዕለት ነበር እንጂ የዛሬ ቁጣ ይረባል?" አሉት ።

ዛሬ በአዲስ አበባ ያሉት ጣልያኖች ሥራቸውን ሲፈቱ አዲስ ሙዚቃ እያበጁ ሲዘፍኑ ይውላሉ ። እንኳን ይጉላሉና የኛ ወታደር እንደነዚያ አልደላውም ። ጃንሆይ የምርኮኛ ቅምጥል አበጅተውልናል።

አንድ ነገር ብቻ የሚያስፈራ ነገር አለ ። እጅግ ጠግቧልና የሠራተኞችን የኢጣልያ ዲቃሎች ሰናሳድግ ፣ ሁለት ሺ የኢጣልያ ኢትዮጵያ ጥለውብን የሔዱ እንደሆነ ከዚህ ጃንሆይ ብዙ አሳብ አለብዎት (አለባቸው) ። ያሥመራ ባለጋዜጦች ተሰለቡ ይላሉ ፤ መሰለባቸውም በዚህ ይገኛል ።[1] . . .

በማለት ግራዝማቹ ስለ እስረኞቹ ጽሑፋቸውን በዚህ ይደመድማሉ ።

ዳግማዊ ምኒልክም ፣ እቴጌ ጣይቱም ለነዚህ ምርኮኞች ይኸን የመሰለ መንከባከብ ለማድረግ የሚገደዱት ፣ ግራዝማች ዮሴፍም ይኸንኑ በዝርዝር ለሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ ለመግለጽ የሚጣጣሩበት ዋናው ምክንያት ስለምርኮኞቹ በአውሮፓና በኢጣልያ አገር ፣ "የኢትዮጵያ መንግሥት ባይፈጃቸውም በረኃብና በእርዛት ያጉላላቸዋል" የሚል ከፍተኛ ሥጋት ነበር ። እንደዚሁም አዲስ አበባ ያሉት የውጭ አገር ተወላጆች በተለይ ፈረንሣዮቹ ምንም እንኳን የኢትዮጵያና የንጉሠ ነገሥቱ ወዳጆች ሆነው የኢጣልያኖቹ መሸነፍ ምናልባት ቢያስደስታቸውም ፣ ዘራቸውና ወገናቸው በሆኑት በነዚህ ጣልያኖች ከተማረኩ በኋላ የመጉላላት ሁኔታ ቢያዩባቸው አይወዱም ። በጠቅላላው በዚህ በ19ኛው መቶ ዓመት ላይ አውሮፓ የዓለም አዛዥ ፣ የዓለምን ዕድል እንደልቡ የሚወስን መሆኑ ግልጽ ነው ። ከጃፓን በቀር አውሮፓ የብጫንና የጥቁርን ሕዝብ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ በበላይ

* የእንጨት መዝገብ የእግር ልክ መለኪያ (ሞዴል) ሳይሆን አይቀርም ።

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት በሞንዶን ዶሲዬ ፣ ቁጥር 82



የሚያስተዳድርበት ወቅት ነበር ። በዚህ ወቅት ጥቁሮቹ ኢትዮጵያውያን አሸናፊዎችና ማራኪዎች ፣ ነጮቹ ጣልያኖች ተሸናፊዎችና ተማራኪዎች ሆኖ መገኘት ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ በአድናቆት የሚታይበት ዘመን ነው ። እስያና አፍሪካ ነጻነታቸውን ባገኙበት በዚህ ባሁኑ ዘመን (1960—1975 ዓ.ም.) የዚህ ዓይነቱ ድልና የምርኮኛ አያያዝ ቢፈጸም ላያስደንቅ ይችላል ። ያን ጊዜ ግን ሁኔታው ካሁኑ የተለየ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ በአሸናፊነታቸውና የነጮች ምርኮኞች በእጃቸው በመውደቃቸው በአውሮፓ የሚሰጠውን ስሜት ከሚያስከትለው መዘዝ ጋር ተገንዝበውታል ። በፊተኛው ጊዜ ከጦርነቱ በፊት እርቅና ሰላም ያለመታከት ይፈልጉ እንደ ነበር ፣ አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ የዓለምን ደንብና ሕግ የምታከብር መሆኗን ለማሳየት ሲሉ ፣ ስለ ምርኮኞች ሁኔታ በኢጣልያና በአውሮፓ የተቀሰቀሰውን ሥጋት ለማርጋት እነዚህ ምርኮኞች በልብስ እንዳልታረዙ በምግብ እንዳልተጐዱ እንዲያውም የሙዚቃ መሣሪያ እያበጁ የምርኮኝነታቸውን አሳዛኝ ሊሆን የሚገባውን ጊዜ በደስታ እንደሚያሳልፉ በአስተርጓሚያቸው አማካይነት ለሙሴ ሞንዶን ፣ በሞንዶንም አማካይነት ፓሪስ ለሚታተመው "ለታ" ለሚባለው ጋዜጣ እንዲደርስ አድርገዋል ። በዚህም ጋዜጣ አማካይነት የኢጣልያና የአውሮፓ ሕዝብ የምርኮኞቹን ሁኔታ እንዲረዳው ለማድረግ ይጣጣሩ ነበር ። ምርኮኞቹ ራሳቸው ከየዘመዶቻቸው ጋር እንዲጻጻፉ ስለ ተደረገም በመጀመሪያ ጊዜ "ተገደሉ ፤ ተሰለቡ ፤ ተራቡ ፤ ተራቆቱ" እየተባለ በኢጣልያ ጋዜጦች ተወርቶ የነበረው ሁሉ ፍጹም ሐሰት መሆኑ ሲገለጽ ሁኔታው የኢትዮጵያን መንግሥት ፣ የዚህን ዘመን መሪዎቿንና ሕዝቡን ጭምር በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገምታቸው ችሏል ።

ለአለመስለባቸው ግራዝማች ዮሴፍ እንደ ማስረጃ አድርገው የጠቆሙት ምርኮኞች ከኢትዮጵያ ሴቶች ጋር በመገናኘት የክልስ ዲቃላ ማበርከታቸውን ሲሆን ፣ ይኸውም የክልስ መበርከት ሁኔታ ለወደፊቱ አሥጊ መሆኑን አውስተዋል ። ይኸ ሁሉ በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች በኩል እየተፈጸመ ምርኮኞቹና ቤተሰቦቹ በሚጻጻፉበት ጊዜ የምርኮኞቹ ቤተሰቦች የኢትዮጵያን ሕዝብ ገና እንደ አረመኔ መቁጠራቸው ያሳዝናል ። ያንድ ምርኮኛ እናት ከአዲስ አበባ ደህንነቱን ለጻፈላት ልጅዋ መልስ ፣ " . .በሕይወት መኖርህን ማወቄ ደስ አለኝ . . .ከሚወዳችሁ ቤተሰብ ተለይታችሁ በአረመኔ ሕዝብ እጅ ወድቃችሁ ምን ዓይነት ሕይወት እንዳላችሁ ማን ያውቃል" ብላ የጻፈችለት የቤተሰቦቹን ውለታቢስነት ያስታውቃል ። ወይም እርሱ በሕይወት መኖሩን ብቻ ይሆናል የጻፈላት ።

ግራዝማች ዮሴፍ ፣ የፊተኞቹን ራፖርች ለሞንዶን ቪዳዬ ይጽፉ የነበረው ከትግሬ ግዛት መሆኑን እናስታውሳለን ። ይኸኛውን የሚጽፉለት እርሱም ፣ እርሳቸውም አዲስ አበባ ባሉበት ጊዜ ነው ። ምናልባት ወደ ፓሪስ ለጋዜጣ የሚልከውን እንዲረዳው አዘጋጅተው ያቅርቡልኝ ብሏቸው ይሆናል ። ሞንዶን ቪዳዬ በኢትዮጵያ ያሳለፈው ጊዜ ፣ እ.ኤ.አ. ከ1891 ዓ.ም. ዠምሮ እስከ 1897 ዓ.ም. ድረስ ሰባት ዓመት ነው ። ዓድዋ በተዘመተ ባመቱ ወዳገሩ ተመልሷል ።

ከዚህ ድልና ምርኮ በኋላ ፣ ለኢጣልያ መንግሥት ያለው ምርጫ ፣ "እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ያለው አገር ያስፈልገኛል ፤ ኢትዮጵያን በጠቅላላው በበላይ ሆኜ በጠባቂነት ስም እገዛለሁ" የሚለውን የሕልም እንጀራ በግድ ሰርዞ ይንቀው ከነበረው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ራሱን በማስተካከል በእኩልነት እግር ቆሞ ውልና ስምምነት ማድረግ ነው ።



# ምዕራፍ ሃምሳ አራት

## የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ መመለስ — ያዲስ አበባው አቀባበል

ዳግማዊ ምኒልክ ከዓድዋ ጦርነት በፊት መቀሌን እጅ ካደረጉ በኋላ ፣ በየጊዜው እየተዘዋወሩ የሰፈሩባቸው እንደ ቅደም ተከተሉ መቀሌ ሐውዜን ፣ ፈረስ ማይ ፣ ሳውሪያ ፣ ገንደብታ ፣ ዓድዋ ሲሆኑ ፣ ከድሉ በኋላ ደግሞ ዓድዋ እንትጮ ፈረስ ማይ እንትጮ መቀሌ ናቸው ። ስለዚህ ወደ አዲስ አበባ የተመለሱት ከእንትጮ በመቀሌ በኩል ነው ማለት ነው ።

ባለፈው እንዳነበብነው ማዦር ቶማሶ ሳልሣ ፣ በመጨረሻ ያቀረበውን እሳብ ሳይቀበሉት ከቀሩ ወዲህ በትግሬ ላይ የራስ መንገሻን ሹመት አጽድቀው ለአክሱም ንቡረ እድነት በእጨጌ ቴዎፍሎስ ፋንታ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም ይኖሩ የነበሩትን መነኩሴ መምህር ወልደ ጊዮርጊስን ሾሙ ። መምህር ወልደ ጊዮርጊስ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሲኖሩ ከዚያ ወደ ጐጃም ተሻግረው በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ዘንድ ተከብረው የሚኖሩ ነበሩ ። በእምባቦ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በሚዋጉበት ጊዜ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጦር ውስጥ ሆነው ሰይፋቸውን ታጥቀው ወዲያና ወዲህ እያሉ የሚሸሸውን በግዝት እየገሠፁ በርትተው ማዋጋታቸው ይነገርላቸዋል ። በኋላ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ አዲስ አበባ የመጡ ጊዜ ላፄ ምኒልክ አደራ ብለው ትተዋቸው ስለሔዱ ፣ በየጊዜው ልዩ ልዩ የቤተ ክህነት ሹመት ይዘው ቆይተው አሁንም የዓድዋውን ጦርነት ከአቡነ ማቴዎስ ጋር ሆነው ተዋጊውን በማበረታታትና በማጽናናት አስደስተው ነበርና የአክሱምን ንቡረ እድነት ተሾሙ ።[1]

እንደዚሁም ንጉሠ ነገሥቱ የትግሬን ጠቅላላ ግዛት ለራስ መንገሻ አጽድቀው ፣ የትግሬም ሕዝብ በጦርነቱ ሰዓት ስለ ተጐዳ ፣ ለርዳታ ይሆን ዘንድ 30,000 ጥሬ ብር ሰጥተው ሁሉንም ከደለደሉ በኋላ ወደ ሸዋ ጉዞ ተጀመረ ። በዚህ መካከል ከራስ መንገሻ ጋር ተጣልተው

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 269

ለኢጣልያኖች ገብተው የነበሩትና በኋላ ወዳጄ ምኒልክ መጥተው የዓድዋን ጦርነት የተካፈሉት ራስ ስብሐትና ጓደኞቻቸው ደጃች ሐጎስ በዚህ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ ምን እንደ ተሾሙ የሚናገር ጽሑፍ አልተገኘም ። ምንም በጽሑፍ ባይገኝ ንጉሠ ነገሥቱ ቀድሞ ጠበኞች የነበሩትን ሁለቱን ራሶች አቃርበው ያስታረቁዋቸውና ራስ ስብሐትም በራስ መንገሻ ውስጥ የአጋሜን ሹመት የተሾሙ ይመስላል ።

ያፄ ምኒልክ ከዓድዋ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ፣ ለጊዜው የኢጣልያ መንግሥት ከዓድዋ ድል በኋላ አሳቡ በትክክል ስለ አልታወቀ ጥቂት ጊዜ ዕረፍት አድርገው እንደገና አዲስ ጦርም ፣ ስንቅም ጨማምረው ከአዲስ አበባ ወደ ትግሬ በመሔድ ኢጣልያኖቹ እርቅ እምቢ ብለው ጦርነቱን የቀጠሉ እንደሆነ ለመዋጋት መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ ። እስከዚያም ድረስ ራስ መንገሻ ከጄኔራል ባልዲሥራ ጋር በተቻለ መጠን ሳይዋጉ እየተስማሙ እንዲቆዩ ትእዛዝ ሰጥተዋቸዋል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የእርቅ ስምምነት እስኪያደርጉ ባለው ጊዜ ውስጥ ፣ ሬሳ በማስለቀምና የባከነ ምርኮኛ በመሰብሰብ ረገድ የራስ መንገሻና የጄኔራል ባልዲሥራ ሹማምንት ሁሉንም በኅብረትና በስምምነት ይሠሩ ነበር ። [1]

ስለዚህ ፣ "ትግሬን ለልጄ ለራስ መንገሻ ሰጥቻለሁ" የሚል ዓዋጅ ነግረው ምናልባት ጣልያኖችም እንደገና ጠብ ቢያነሡ ፣ ራስ መንገሻን ይረዱዋቸው ዘንድ ራስ ወሌን አዘው ከጦርነቱ የተማረኩት ጣልያኖች በየሹማምንቱ ተደልድለው አብረው ወደ አዲስ አበባ መልስ ሆነ ። በዚህም ጉዟቸው ንጉሠ ነገሥቱ ከእንትጮ መቀሌ የገቡለት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መቀሌ ላይ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው በሳምሬ በኩል አድርገው ወዳገራቸው ወደ ጐጃም ሔዱ ። ከዚያም ንጉሠ ነገሥቱ ማይጨው ደረሱ ። ቀድሞ ወደ ዓድዋ ሲዘምቱ ከዚያ ሰፍረው ሳሉ የከብት በሽታ ገብቶ ይፈጅ ስለነበረ ፣ ለማይጨው አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተስለው የነበረውን ለመፈጸም ብዙ መሬት ብዙ ላምና በሬ ሰጥተው ዳሩ እሳት መካከሉ ገነት ብለው እንደ ገደሙት ፣ ከዚያ በያደሩበት ግብር እያበሉ በግንቦት 15 ቀን አዲስ አበባ መግባታቸውን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ይገልጻሉ ። [2]

1 Sul campo di Adua, E. XimenesXII, PP. 154 - 168

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ምዕራፍ 64



በዚህ ጐን ሊቀ መኳስ አባተ ፣ ከጦርነቱ ላይ የተማረከውን 60 መድፍ ፣ ጥይትና ጠበንጃ ከየጦርነቱ ሜዳ አሰባስበው የተበላሸውን በተቻለ መጠን እያስበየዱ በ500 ሚስንጀር በቅሎ አስጭነው በትጋትና በታላቅ ጥንቃቄ ከዓድዋ በተምቤን በኩል አድርገው አዲስ አበባ በደህና ገቡ ። ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ ፣ ሠራዊቱም ሁሉ ከፍ ካለ አድናቆት ጋር እንዳመሰገኗቸው ይገልጻሉ ። ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ የንጉሠ ነገሥቱን ጉዞ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በዚህ ዓይነት ሲያመለክቱ ፣ በበኩላቸው ግራዝማች ዮሴፍ እንደዚህ ሲሉ ጨምረዋል ።

> . . . ከትግሬ መሬት ተመልሰው ጃንሆይ ሲነሡ ትግሬ ለቀረው ጦረኛ የሰጡት ብር ከዐሥር እልፍ* በለጠ ። አገሩም እጅግ ጥጋብ ሆነ፤ ማድጋ ማድጋ ተሸመተ ። የትግሬ ሰው ግን ፣ ከኢጣልያ ጋር በብርቱ ደም ተቃባ ። እንትጨው ከእርድ ውስጥ የነበረውን እይርና ገንዘብ ሁሉ የኛ ጦር ሳይደርስ የትግሬ ባላገር ተሻማው እንጂ ፣ የሸዋ ሰው ከድሉ ላይ ካገኘው ነፍጥና እይር በቀር ሌላ አላገኘም ። ራስ መንገሻም ባላገር የወሰደውን ነፍጥና እይር ጠበንጃና ጥይት ሸዋ ከገባን በኋላ ልቅም አድርገው ከባላገር ተቀበሉት ።[1]

ከዚህ አልፈው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም ፣ ግራዝማች ዮሴፍም ንጉሠ ነገሥቱ ከነሠራዊታቸው ሲመለሱ አሸንጌ አካባቢ ዞቢል ውስጥ ሲደርሱ ፣ የአዘቦ ኦሮሞዎች ሸፍተው ሰፈር ለመምረጥ ወደፊት ቀድመው የነበሩትንና የእቴጌይቱን ገረዶች እንደ ተተናኰሏቸው ሲገልጹ ፣ ኤድዋርድ ዘይሜንስ የሚባለው ጸሐፊ በበኩሉ ምኒልክ ለራስ መኰንንና ለራስ ወሌ ትእዛዝ ሰጥተው በሺ የሚቆጠሩትን ሽፍቶች እንዳስቀጧቸውና ቀጥሎም ደጃዝማች እንዳርጋቸው የሚባሉት የራስ መንገሻ (ዮሐንስ) ሹም እዚሁ ወረዳ ተቀምጠው እንደ ዘረፉዋቸው ያመለክታል ። [2]

* አንድ እልፍ ዐሥር ሺ ፣ ዐሥር እልፍ መቶ ሺ ስለሆነ ፣ በቁጥር ግራዝማቹ ከጸሐፊ ትእዛዙ ተለያይተዋል ። ምናልባት ጸ.ት.ገ. ሥላሴ ለራስ መንገሻ የተሰጠውን ብቻ ሲጽፉ ግራ.ዮሴፍ ለሌሎችም መኳንንት የተሰጠውን ደምረው ይሆናል ።

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ቁ.82

2 Sul Campo di Adua . . .PP. 74 -75.

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ በገቡበት ቀን ፣ በሊቀ መኳስ አባተና በጭፍሮቻቸው ትጋት ቀደም ብለው አዲስ አበባ ደርሰው በደንብ ተጠምደው የሚጠባበቁት መድፎች የደስታ ድምፃቸውን አሰሙ ። በተረፈ ምንም ተጽፎ ባናገኘው ከመናገሻ ከተማ ውጭ ከሰባት ወራት በላይ በዘመቻ ያሳለፉት ንጉሠ ነገሥት ከነጦራቸው የድል አድራጊነትን ግርማ ተጐናጽፈው ከከተማው ሲገቡ ወንዱ በሆታ ፣ ሴቱ በእልልታ ፣ በታላቅ የደስታ ግርግር እንደተቀበሉዋቸው የታወቀ ነው ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የቤተ ክህነቱን አቀባበል ሲያመለክቱ በዚህ ታላቅ አገባብ ላይ የከተማውን ሕዝብ የሞቀ አቀባበል አልዘረዘሩትም ።

በካህናቱ በኩል የተደረገውን አቀባበል ግን ፣ የእንጦጦ ማርያምና የራጉኤል ፣ የሥላሴና የዑራኤል እንደዚሁም የጊዮርጊስ ካህናት ልብሰ ተክህኗቸውን እየለበሱ ቀደም ብለው በሰፊው ጃንሜዳ ተሰብስበው ይጠብቁ ስለነበረ ፣ " ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ኢጣልያ "መሬቷ በኢጣልያ ደም ታጥባ ፋሲካ (ደስታ) አደረገች የሚለውን ጠቅሰው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት አሸበሸቡ ሲሉ አመልክተዋል ።*

ለዚህ ለዓድዋ ድል ተስማሚ የሆነ ቅኔ የአክሱሙ አለቃ መንክር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መወድስ ቅኔ ለንጉሠ ነገሥቱ አበርክተዋል ።**

አመ ተክለ አሚን ጸለየ በልማደ ኖኅ
ሥላሴ ይኅድሩ ውስተ ቤተ ምኒልክ ሴም
ወሎቱ ይክሥቱ መጽሐፈ ዕዳሃ ለሮም
ምኒልክ ክዓወ በላዕለ ሮሜ ምሉዓ ጽዋዓ መዓቱ ዘቱሱሀ በደም
ምረረ ሐሞቱ ለምኒልክ እስከ ነጥዒም ሐደገ ወዳግመ ኢይጥዕም

ለዓለም

ለምኒልክኒ አመ ኃበ ዓጽሙ ዘተክለ ሃይማኖት ዓጽም
ምኒልክ ለእመ ሐመ ተክለ ሃይማኖት የሐምም
ባህቱ ኢይሕምም ይብል ተክለ ሃይማኖት ፍጹም
ምኒልክ ይህየወኒ ወኢይመውትኒ ለዓለም ። (1)

---

* በድጓ ዜማ ውስጥ "ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ" የሚለውን በደመ ኢጣልያ ብለውታል ።

** የቅኔው ፍሬ አሳብ በላይኞቹ መለመሮች በተክለ ሃይማኖት ጸሎት ሥላሴ ከምኒልክ ቤት አድረው የሮማን የመከራ የዕዳ ጽሑፉን እንደ ገለጹላቸው ያመለክታል ።

1. መጽሐፈ ቅኔ መልአከ ብርሃን አድማሱ ገጽ 312



ከሁሉ የበለጠ የጐጃሙ ሊቅ መምህር ወልደ ሥላሴ እንደ መልክ አድርገው ፣ ላዔ ምኒልክ በግእዝ ደርሰው ያበረከቱት የደራሲውን ሊቅነት ብቻ ሳይሆን ፣ እኝሁ ምሁር የፖለቲካውንም የጦርነቱንም ታሪክ በትክክል የተከታተሉት ይመስላል ። ድርሰታቸውንም ብላንሻር የሚባለው የፈረንሣይ ሊቅ ወደ ፈረንሳይኛ ተርጕሞት ሙሴ ፉርኔ የሚባሉት ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ በጻፉት የሁለት ቅጽ መጽሐፍ ላይ ጨምረው በሕትመት አራብተውታል ። ሁሉን በዚህ ምዕራፍ ለማስፈር ስለማይቻል አጀማመሩን ብቻ ከዚህ ቀጥለው ባሉት መስመሮች ብንመለከት የሁሉንም አሳብ ይገልጽልናል ።

ጣልያን በትግሬ አገር ስለ መሸነፉ

1/ ሰላም ለዝክረ ስምከ መልእክተ ኵሉ ዘኮነ
ወበግርማሁ ግሩም እንተ አጥፍዓ ጣልያነ
ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ መድኅን
ቀተልኮ ለዓላዊ ከምድረ ትግሬ መካነ

የእንግሊዝ መንግሥት ለኢጣልያ መደረቡን በመጥቀስ ደግሞ እንደዚህ ብለዋል ።

2/ ሰላም ለአእናፊከ ከመ ጼና ገነት ምዑዝ
ሱራፌሆን ሠናይ ወጥቀ ሐዋዝ
ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ዘኢትዮጵያ አርዝ
ሶበ ተለቅሃ ኢጣልያ ወርቀ አይሁዳዊ እንግሊዝ
ዘይከፍል ሰዕነ አሐዘ ትካዝ ።

በዓድዋው ጦርነት ጠቅላይ አዝማች በገኔራል ባራቲዬሪና በንጉሡ በኡምቤርቶ ላይ ሲተቹ ደግሞ ፤

3/ ሰላም ለአፉከ ለፈጣሪ ዘየአኵቶ
ኢይትናገር ሰላቀ ወኢይነብብ ከንቶ
ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ለኢትዮጵያ ማኅቶቶ
ኃልቀ ማንጀር (ማገሮር) ወሰዕነ ፍኖቶ
ገኔራል ባራቲዬሪ ሶበ ገብዓ ደንገፀ ኡምቤርቶ

ከዚያ ወዲያ በየጊዜው ለዳግማዊ ምኒልክ ፣ ለእቴጌ ጣይቱ ፣ ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ የተደረሰው የአማርኛ ግጥም ብዙ ነው ። የአብዛኞቹ ገጣሚዎቹ ስም አይታወቅም ። ከብዙው በጥቂቱ ከዚህ የሚከተለው ነው ።

1/ ጣልያን ገጠመ ከዳኛው ሙግት
አግቦ አስመሰለው በሥራው ጥይት
አሁን ማን አለ በዚህ ዓለም
ጣልያን አስደንጋጭ ቀን ሲጨልም
ግብሩ ሰፊ ነው ጠጁ ባሕር
የዳኛው ጌታ ያበሻ ባሕር

ሼዋ ነው ሲሉት ዓድዋ የታየው
ሺናሻ መላሽ ወንዱ አባ ዳኛው
አይኰረተም እጁ የዘናው
ወንዱ ምኒልክ ዝንታለም ይቅናው
ወዳጁም ሣቀ ጠላቱም ከሳ
ተንቀሳቀሰ ዳኛው ተነሣ
አራቱ አህጉር ለሱ እጅ ነሣ
ፈረሱ ዳኘው ሚስቱ ጣይቱ
ምጥዋ ወርዳ ቀዳች ወጥ ቤቱ[1] (ከሐሰን አማኑ)

2/ ምኒልክ ተወልዶ ባያነሣ ጋሻ
ግብሩ እንቁላል ነበር ይኸን ጊዜ አበሻ ።
በሠራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ
ተፈጠመ ጣልያን አበሻ እንዳይደርስ ።
ምኒልክ ተጉዞ የምትጠይቁኝ
ፊትም አላለፈ ኋላም አይገኝ ።
መድፉን መትረየሱን ባድዋ መሬት ዘርቶ
እንክርዳዱን ነቅሎ ስንዴውን ለይቶ
የዘራውን እህል አጭዶና ወቅቶ
ላንቶኒሊ አባየው ፍሬውን አምርቶ ።
እንዳቀና ብሎ ለምኖ መሬት
ንግድ ሊያስፋበት ሊዘራ አትክልት
እየመጣ ሊሰጥ ግብሩን ለመንግሥት
ለጓዙ ማረፊያ አገር ቢሰጡት
ተጠማኝ ሰንብቶ ሆኖ ባለርስት
ወሰን እየገፋ ጥቂት በጥቂት
እውነት እርስት ሆነው ተቀበረበት ።
ባሕር ዘሎ መምጣት ለማንም አትበጅ
እንደ ተልባ ስፍር ትከዳለች እንጂ
አትረጋምና ያለተወላጅ ።
የዳኛው አሽከሮች እየተባባሉ
ብልት መቆራረጥ እንድነት ያውቃሉ
ዓድዋ ከከተማው ሥጋ ቆርጠው ጣሉ ።
የእስክንድር ፈረስ መቼ ተወለደ*
የምኒልክ ፈረስ በክንፎቹ ሔደ ።
ደንገላሳ ሲዘል እየተንጓደደ
የሮማውን ኩራት በእግታ አሰገደ ።
አገርህን ምኒልክ እንዳሁን ፈትሻት
አጁን ቀምሼ አላውቅ እያለ ሲያማህ
ቀመስና እጅህን መጥቶ ጠላትህ
ሮም ላይ ተሰማ ለጋስ መሆንህ ።

1 ዝክረ ነገር ፣ ብላቴን ጌታ ማኅተም ሥላሴ ፣ ገጽ 879—880
* ትልቁ እስክንድር በክንፋማ ፈረስ ወደ ሰማይ ወጣ ከተባለው ጋር በማመሳሰል



አባተ በመድፉ እምሳውን ሲገድል
ባልቻ በመትረየስ ነጥሎ ሲጥል
የጐጃሙ ንጉሥ ግፋ በለው ሲል
እቴጌ ጣይቱ እቴጌ ብርሃን
ዳዊቷን ዘርግታ ስምዓኒ ስትል
ተማራኪው ባዙቅ ውሀ ውሀ ሲል
ዳኛው ስጠው አለ ሠላሳ በርሜል ።
እንደ በላዔ ሰብእ እንደመቤታችን
ሲቻለው ይምራል የኛማ ጌታችን[1]

1 የኢትዮጵያ ታሪክ ካፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ. (9ነኛ እትመት) ገጽ 148

# ምዕራፍ ሃምሳ አምስት

## የአዲግራት ምሽግ መለቀቅ

አዲግራት የአጋሜ አውራጃ ከተማ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ የስመ ጥሩው ባላባት የደጃች ሰባጋዲስ ተወላጆች ራስ ስብሐት ፣ ደጃች ሐጐስ ተፈሪና ሹም አጋሜ ተስፋዬ በአጋሜ ግዛት ሲጣሉበት ቆይተው በመጨረሻ ለኢጣልያ ያደሩት ሐጐስ ተፈሪ ፣ በ1887 ዓ. ም. ከኢጣልያ መንግሥት ተሾመው ይዘውት ነበር ። ጄኔራል ባራቲዬሪ አዲግራት ከገባ ወዲህ ምንም እንኳ ዋና ተቀማጭነቱ አሥመራ ቢሆን ፣ አዲግራትን በደንብ አስመሽጎ የወታደርና የስንቅ ዋና መከማቻ አድርጎ መላውን ትግሬን ለመያዝና ለመቆጣጠር መነሻና መገስገሻ አድርጎት ነበር ። እነቶዜሊ ደብረ ኃይላ መጥተው ከነቀኛዝማች ኃይለማርያም ጋር ያደረጉት ጦርነትና አላጌ መጥተው እየተዋጉ የሞቱት ከአዲግራት የጦር ሰፈር ተነሥተው ነው ።

በመጨረሻ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ወደ ሰሜን ተጉዘው በመጀመሪያ መቀሌ ቀጥሎ ዓድዋ ገብተው የጦርነቱ ጉዳይ በተፋፋመበት ሰዓት ጄኔራል ባራቲዬሪም ከነጦሩ መጥቶ የተቀመጠው በዚሁ በአዲግራት ነበር ።" ዳግማዊ ምኒልክም ከነጦራቸው መጥተው ቢከቡን ከምሽግ ውስጥ ሆነን ለማጥቃትና ለማሸነፍ እንችላለን " በማለት ብዙ ቀን በተስፋ ተጠባብቆ ሳይሔዱለት ቀሩ ። በዚህ ፈንታ ከርሱ ጋር የነበሩት ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጐስ ከዚሁ ከአዲግራት ምሽግ አምልጠው ወጥተው ከወገናቸው እንደ ተደባለቁ ባለፈው አመልክተናል ። ዐፄ ምኒልክም በበኩላቸው ፣ የኢጣልያ ጦር ከአዲግራት ምሽግ ወጣ ብሎ በሜዳ ሊገጥማቸው ባለመቻሉ ተናደው ፣ " የሰው አገር ሊፈልግ የመጣ ሰው ጉድባ ገብቶ ይደበቃልን " ብለው ወደ ሐማሴን ለማምራት ከዓድዋ ወደ ገንደብታ የተንቃነቁ ጊዜ ፣ ባራቲዬሪም በበኩሉ በማጆር ፕሬስቲናሪ የሚመራ ያንድ ሻለቃ ጦር እዚያው አዲግራት ትቶ የንጉሡን ጦር እርምጃ ለማገድ ከአዲግራት ወደ እንትጮ ተዛውሮ መሽጎ ተቀመጠ ።

ጄኔራል ባራቲዬሪ ከዓድዋ የጦር ሜዳ ያመለጠ ጊዜ፣ ወደ አዲግራት ምሽግ በመሸሽ ፈንታ የተጓዘው አዲግራትን ወደቀኝ ትቶ በረቢ አርአየኒና በእንትጮ አድርጎ ወደ ሰንዓፌ ከዚያም ወደ አዲቀይህ በመጨረሻም ወደ አሥመራ ነው ። ሌሎች ሃምሳ አምስት የሚሆኑ የጦር መኰንኖችና ወታደሮች ግን በስንት ድካም ከዓድዋ ተጉዘው አዲግራት ምሽግ ገብተው ሕይወታቸውን ከሞትና ከምርኮ ለማዳን ችለዋል ።የዓድዋ ድል ከተሰማ በኋላ ደግሞ፣ ከምሽግ ውስጥ እየወጡ ለመጥፋት ከሞከሩት ያገር ተወላጅ ወታደሮች ውስጥ አንዳንዶቹ ማምለጥ ሲችሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በኢጣልያኖች እየተመቱ ሞተዋል[1] ። ስለዚህ ከዓድዋ ድል በኋላ የአዲግራት ምሽግ በነራስ ስብሐት ጦር ተከቦ እንደ ተቀመጠ ብዙ ጊዜ ቆይቷል ።

ንጉሠ ነገሥቱ፣ ወደ አዲስ አበባ ከመመለሳቸው በፊት ጄኔራል ባልዲሠራ ለእርቅ ድርድር ማጆር ሳልሳን የላከው ጊዜ የተስማሙበትን የእርቅ አሳብ በመለወጥ፣ "ዐፄ ምኒልክ ለኛ እምቢ ያሉትን የጠባቂነት መብት ለሌላ መንግሥት እንዳይሰጡ ቃል ይግቡ" የሚል አሳብ ስለ አመጣ፣ የፊተኛውን የተስማማንበትን ጽሑፍ እስከታመጣ ድረስ እዚሁ እኔ ዘንድ ትቆያለህ" ብለውት ይኸንኑ በጽሑፍ ለባልዲሠራም እንደ ገለጹለት እናስታውሳለን ።

በዚህ ምክንያት፣ እርሳቸው ወደ ሸዋ ተመልሰው የደከመውን የጦር ኃይላቸውን እንደገና አደራጅተው በአዲስ ኃይል ወደ ትግሬ እስኪመለሱ ድረስ ራስ መንገሻን በትግሬ ግዛት አደላድለዋል ። በግዛት የሚዋሰኑዋቸው ራስ ወሌ ብጡል፣ ምናልባት ኢጣልያኖቹ እንደገና አንሰራርተው በራስ መንገሻ ላይ ጦርነት ቢያነሡ እንዲረዱዋቸውና እንደ ደብረ ኃይላው ጊዜም አይለውባቸው ወደ የጁ ቢያፈገፍጉ እንዲቀበሉዋቸው አድርገው፣ በዚሁ ጊዜ በየሰነዱ ላይ እንደምንገነዘበው፣ ዐፄ ምኒልክ ለራስ መንገሻ ማገርር ሳልሳን አስረክበው የሰጧቸው ትእዛዝ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

፭ኛ/ ጄኔራል ባልዲሠራ ከደብረ ኃይላው ጦርነት ቆስለው የተማረኩትን እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን በነጻ ሲለቅ፣

፮ኛ/ የኢጣልያ ትራፊ ጦር ከውጭ እንደ ተከበበ የተቀመጠበትን የአዲግራትን ምሽግ በሰላም አስረክቦ ለቆ ሲወጣ፣

፯ኛ/ በማገርር ሳልሳ እጅ የተላከውን የእርቅ ድርድር የሚያመለክተውን የጽሑፍ ሰነድ ሲመልስ ማገርር ሳልሳ ወደ ወገኖቹ እንዲመለስ፣

1 Sul Campo di Adua . .PP. 98 -99.



፰ኛ/ እኛ ከሸዋ እስከንመለስ ድረስ ባልዲሠራ ጠብ እንዳይጭር በተቻለ መጠን የስምምነት መልክ እያሳየህ የሆነውን ሁሉ ቶሎ ቶሎ ላክልን የሚል ነው ።[1]

በዚሁ ጊዜ፣ ምንም ተጽፎ ባናገኘው፣ በፊት ጠበኞች የነበሩት እነራስ ስብሐት፣ እነደጃች ሐጐስ ተፈሪ እነደጃች ተድላ አባ ጉበን በስምምነት በራስ መንገሻ ውስጥ ሆነው በሕብረት እንዲሠሩ ያስማሙዋቸው መሆኑን ሁኔታው ያስታውቃል ።

ንጉሠ ነገሥቱ፣ በሚያዝያ ወር ላይ ከትግሬ ወደ አዲስ አበባ ካመሩ ወዲህ ከላይ በተጠቀሰው አሳብ መሠረት፣ ጄኔራል ባልዲሠራና ራስ መንገሻ በዓድዋ፣ በዩሃና በእንትጮ ስለ ወደቁት የኢጣልያኖች ሬሣና ዓፅም ማስለቀም፣ በትግሬ መኳንንት እጅ በምርኮ ወይም ቆስለው በምሬት ስለ ተቀመጡት ጣልያኖችና ስለ አዲግራት ምሽግ መለቀቅ ጉዳይ በየጊዜው በጽሑፍና በመልክተኛ አማካይነት ግንኙነት ጀመሩ ። በራስ መንገሻ በኩል የዚህን ጉዳይ ለመፈጸም የተወከሉ በፊት ከኢጣልያኖች ጋር የነበሩት ደጃች ተድላ አባ ጉበን፣ ወጣቱ ልጅ አብርሃ፣ * በጅሮንድ ብሩ፣ አሳላፊ ኃይሉና ሌሎችም ሲሆኑ፣ ከኢጣልያኖች ወገን ደግሞ ኮሎኔል አሪሞንዲ የሟቹ የጄኔራል አሪሞንዲ ወንድም፣ ማገርር አንጌራና ሞንታናሪ ናቸው ።በነርሱ ውስጥ ደግሞ፣ ዋናው አስተርጓሚ አቶ ገብረ እግዚአብሔርና ሌሎችም የባንዳ ሹማምንት አሉ ። ባንድ ወገን ደግሞ የራስ አሉላ ሰዎች ፊታውራሪ ፈንታ፣ ልጅ ተሰማ፣ ልጅ ተስፋዬ የሚባሉት ከራስ መንገሻ ወኪሎች ከነአሳላፊ ኃይሌ ጋር በማስረከቡ ረገድ ጠብ እየተቀሰቀሰ እኛ የራስ አሉላን እንጂ፣ የራስ መንገሻን ትእዛዝ አናውቅም በማለት ከርክር ይደረግ ነበር ።ሆኖም በመጨረሻ የጠቅላይ ገዥው የራስ መንገሻ አሳብ ተፈጻሚነት ስለነበረው፣ በማናቸውም ጣልያኖቹ በራስ መንገሻና በሹማምንቶቻቸው አያያዝ ተደስተው ነበር ።በዚህ ጊዜ ከሁሉ የበለጠ ለኢጣልያኖቹ ወዲያና ወዲህ እያሉ በትጋት የዚህን ጉዳይ ይፈጽሙላቸው የነበሩት ገብረ እግዚአብሔር ናቸው ። ስለዚህም በዚሁ ሰዓት የነበረው ዘይመንስ የሚባለው በጻፈው ውስጥ፣ "ወጣቱ ታማኙ፣ ብልሁ ቀልጣፋው ገብረ እግዚአብሔር ለኛ አልማዝ ነው ። እርሱም የሳንጉይኔቲ

1 Storia Diplomatica . . C. Rossetti, P . .187, Adua, Bellavita, P. 432.

* ልጅ ተድላ አባ ጉበንና ልጅ አብርሃ ሁለቱም ያፄ ዮሐንስ እኅት የትልቁ የራስ አርአያ ልጆች ናቸው ። አብርሃን በታላቅ ወንድማቸው በደጃች ደብብ አማካይነት ኢጣልያኖች በልጅነታቸው ወስደው በቶሪኖ ከተማ ቢያስተምሩዋቸውም ባሁኑ ጊዜ ኈራቸውን ከራስ መንገሻ ጋር አድርገዋል ።

አስተርጓሚ ነበር ። ባሕታ ሐጐስ ሳንጉይኔቲን ያሰረው ጊዜ በእስረኝነት አብሮ ከመካፈሉ በቀር በብዙ ጥበብና በወንድምነት መንፈስ እንዲያመልጥ አድርጐታል ።ገብረ እግዚአብሔር በኮዓቲት እንዳደረገው አሁንም በዓድዋ ተዋግቷል ”[1] ብሏል ።

ስለዚህ አሁንም እንገኔራል አሪሞንዲ የሞቱበትን ስፍራ በመጠቆም ምርኮኞቹና ቁስለኞቹ ተለቀው ወደ አሥመራ በነጻ እንዲሔዱ ለራስ መንገሻ በቃልም ፣ በጽሑፍም በማሳሰብ ከሹማምንቶቻቸውም ጋር ተባብረው በመሥራት ገብረ እግዚአብሔር ለኢጣልያኖቹ አገልግለዋል ። ስለቁስለኞች ጉዳይ ለራስ መንገሻ ደብዳቤ ጽፈው ኖሮ ለዚሁ ከራስ መንገሻ የተሰጣቸውን መልስ ከዚህ እንደሚከተለው እናነባለን ።

> መልእክት የራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ይድረስ ከገብረ እግዚአብሔር ካሳላፊ ኃይሉ ። እንዴት ሰነበታችሁ እኔ ደህና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን ። የሰደድህልኝ 'ገብረ እግዚአብሔር' ደብዳቤ ደረሰኝ ። የመምጣታችሁን ነገር አንድ ጊዜ አይባል ሁለት ጊዜ ሦስት ጊዜ ከራስ አሉላ ደብዳቤ ሰድጀአለሁ ። የኢጣልያ ቁስለኞች እስተእሁን የዘገዩም በጣም እስቲድን ብዬ ነው እንጂ በሌላ ነገር አይደለም ። አሁንም በዱሃ በንትሙው ያሉ ቁስለኞች እሺ ይውሰድዋቸው ። ለራስ አሉላም ይስጧቸው ብዬ ልኬባቸዋለሁ ። ከናንተ ጋር ለመጡ መኳንንት በብዙ ሰላምታ ስጡልኝ ። ተጻፈ አመ 20 ወ 6 ለግንቦት (፲ 888 ዓ.ም.)

“ከናንተ ጋር ላሉት መኳንንት ሰላምታ ስጡልኝ” ያሉት እላይ ለተጠቀሱት የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ለነኮሎኔል አሪሞንዲ መሆን አለበት ። “ለራስ አሉላም ይስጧቸው ብዬ ጽፌአለሁ” ያሉት በራስ አሉላ ሰዎች እጅ የሚጠበቁ ስምንት የኢጣልያ ምርኮኞች ከነዚሁ አንዱ ሌሪ የሚባል የመቶ አለቃ ያለበት ነበሩ ። ሁለት ሦስት ጊዜ ከራስ መንገሻ ተጽፎላቸው ሳለ ፣ ራስ አሉላ ምርኮኞቹን ለመልቀቅ ቅር ያላቸው ይመስላል ።ከዶጋሊ ጀምሮ እስከ ዓድዋ ከኢጣልያኖቹ ጋር ሲዋጉ የኖሩት ዝግናው አሉላ አባ ነጋ ፣ ምናልባት ለጠቅላላው ወረራና ጦርነት አንድ ውልና ገደብ በይፋ ሳይበጅለት ምርኮኛን ለጠላት ማስረከቡ ቅር ብሏቸው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ፣ የምርኮኞቹና የቁስለኞቹ ጉዳይ በነራስ ስብሐት በነደጃች ሐጐስ ተፈሪ እጅ ያሉትም ጭምር ባንዳንድ ምክንያት

1 Sul Campo di Adua, Ximenes, PP. 227-228.



እየተወዛገበ በሚቆይበት ጊዜ፣ ጄኔራል ባልዲሠራ አዲስ ከኢጣልያ አገር ይዞት የመጣው ብዙ ጦር ነበረውና በዚያ እየተመካ የማስፈራሪያ ቃል ለራስ መንገሻ በደብዳቤ ጽፎ ላገሬውም እንደዚህ የሚል ቃል በአማርኛ አጽፎ እንዲበተን አደረገ ።

> እኔ ዠኔራል ባልዲሠራ ትልቁ የመንግሥት መኰንን የኤርትራ ቅኝ አገር ገዥ ለአጋሜና ለትግሬ ሕዝብ ፣ ስሙኝ እኔ የመጣሁት ምርኮኞቼን ለመውሰድና ሰላም ለማድረግ ነው ። ራስ መንገሻ ምርኮኞቼን ካልሰጠኝ ጦርነት አድርጌ አገሪቱን ለማፈራረስ ግዴታዬ ነው። መንግሥት የሚለው ይኸን ነው ። ምርኮኞቼን ስጡኝ ፤ እናንተም ወደ የቤታችሁ ተመልሳችሁ አሁን የዝናም ጊዜ ስለሆነ እርሻችሁን እረሱ እኔ ወታደሮቼን እንጂ መሣሪያም አልፈልግ ...ወታደሮቼን እስከ ሦስት ቀን ካላገኘሁ አጋሜን በሙሉ አጠፋዋለሁ ።

ይኸም የተለመደውን የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ጉራ ለመንዛትና በዚህ ዓይነት አስፈራርቶ በማወናበድ በአዲግራት ምሽግም በውጭም ያሉትን ጣልያኖች በቶሎ ከነሕይወታቸው ለመረከብ ነው እንጂ ፣ ካለበት ቦታ ተንቃንቆ ጦርነት ለማድረግ ሁኔታው አያመችውም ። የመንግሥቱም መሪ ትእዛዝ ልክ በኢትዮጵያ በኩል እንዳለው ከነራስ መንገሻ ጋር በተቻለ መጠን በሰላም ለመቆየት ነው ።

አዲግራት በውጭ በራስ ስብሐትና በደጃዝማች ሐጎስ ጦር እንደተከበበ እምሽጉ ውስጥ ያሉትም ኢጣልያኖች ፣ “ከውስጥ እየተዋጋን እናልቃለን እንጂ ፣ ምንም ቢሆን እጃችንን ለነራስ ስብሐት አንሰጥም” ብለው ሁለቱም ወገኖች በዚህ ዓይነት ተፋጠው ሳለ ፣ በመካከሉ ራሱ ጄኔራል ባልዲሠራ ከአሥመራ ከነጦሩ በሌተና ጄኔራል ዴል ማይኖንና በሌተና ጄኔራል ሐሽ ታጅቦ ወደ አዲግራት አቅራቢያ መጥቶ በአቅራቢያው በቸርሰበር ሰፈረ ። ከዚያም ጄኔራል ዴል ማይኖን ካንድ ክፍል ጦር ጋር ወደ አዲግራት ልኮ ከባቢዎቹ እነራስ ስብሐት በኢጣልያ ጦር እንዲከበቡ ሞከረ ። ይኸውም ሁልጊዜ ለማስፈራራት ካልሆነ የውስጠኞቹም ፣ ዴል ማይኖም እነራስ ስብሐትን ለመውጋት አልደፈሩም ። ሁለቱም ወገኖች በማስፈራራት ሲጠቀሙ ፈልገዋል ። ቢሆንም የጄኔራል ባልዲሠራ ዓላማ ቢቻል በሰላም ባይቻል አስፈራርቶ ፣ ሁለቱም ሳይዝ የቀረ እንደሆነ በግዴታ ተዋግቶ የተከበቡትን ነጻ አውጥቶ ለመመለስ ነው ። ስለዚህ አልፎ አልፎ ምንም እንኳን አንዳንድ ግጭት ቢፈጠርም ፣ ሁለቱም ወገኖች የጦርነቱን ጉዳይ በማስፈራራት ደረጃ ብቻ እየተጠቀሙ በዚያው ጊዜ ሁለቱ ጠቅላይ አገረ ገዥዎች (መንገሻና ባልዲሠራ) በቁም ነገር መሠረታዊ የሆነውን ምሽጉን የመልቀቁንና እስረኞቹን የመለዋወጡን ጉዳይ በሰላም ጨረሱ ። ከዚህ በኋላ ጄኔራል ባልዲሠራ እ.ኤ.አ. ግንቦት 4 ቀን 1896 ዓ.ም “ለመያዝ የሚቻለውን

ንዝና መሣሪያ ይዛችሁ ውጡ” የሚል ትእዛዝ ለምሽጉ አዛዥ ለማዦር ፕሬስቲናሪ በጽሑፍ አስተላለፈለት ።

ከምሽጉ ውስጥ ያሉት 1500 የሚሆኑት የኢጣልያና ያገር ተወ ላጅ ወታደሮች ፣ ዐሥራ ሁለት መድፍ ከሦስት መቶ ሃምሳ ጥይት ጋር ፣ ስድስት መትረየስ ከመቶ ሰማንያ ሺ ጥይትና ከብዙ ጠመንጃ ጋር ናቸው ። እነሱም ከምሽጉ ውስጥ ሆነው እንደ ተከበቡ የሚደር ስባቸውን ሲጠባበቁ ከውጭ በጄኔራል ባልዲሠራና በራስ መንገሻ መካከል ስለ እነርሱ ዕድል የሚደረገውን ንግግርና ስምምነት እያውቁም ነበር ። ስለዚህ ከስምምነቱ በኋላ የጄኔራል ባልዲሠ ራን መምጣትና ለመውጣት የሚችሉ መሆናቸውን ያበሠረው ሌተና ቦድሮቦ የሚባለው ነው ። ቀጥሎ በጄኔራል ባልዲሠራ ትእዛዝ ሌተና ጄኔራል ዴል ማይኖ ወደ ምሽጉ ገብቶ በታየ ጊዜ ታላቅ ደስታ ሆነ ። ከዚህ በኋላ የኢጣልያ ባንዲራ ወርዶ ከምሽግ ውስጥ ያለው የቆሰ ለውና የታመመው በቃሬዛ ፣ ግማሹ በከብት እየሆነ ደህነኛው መሣሪያውን እየያዘ በሰልፍ መውጣት ጀመረ ። ሲወጣም ጠብ እንዳ ይነሣ ግራና ቀኝ የቀጥታ መሥመሩን ብቻ ይዞ ወደ አሥመራ መንገድ እቅጣጫ እንዲሔድ ታዞ ነበር ።

በዚህ ጊዜ ፣ ውጭ የከበበው ወታደርና ኢትዮጵያዊ ባላገር በብዛት ቆሞ በሚመለከትበት ጊዜ ፣ ግማሹ የሚወጡትን ወታደሮች ማጉላላ ትና መዝረፍ ፣ ግማሹም ወደ ውስጥ ገብቶ ዕቃ መሻማት ስለፈለገ ጣልያኖቹን በደንብ ሳይጉላሉ ለማውጣት የታዘዙት ሹም አጋሜ ተስፋዬና ደጃች ሐጐስ ተፈሪ ፣ ጭፍራ ጭፍራቸውን ይዘው ይጠብቁ ነበር ። ብዙ ጊዜም ወታደሮቻቸው በኃይል ዘራፊውን ይበትኑ ነበር።

በዚህ ዓይነት እጠባበቅና ጥንቃቄ ፣ በአዲግራት ምሽግ የነበሩት የኢጣልያ ወታደሮች ወጥተው ሲያልቁ ራስ መንገሻ በኢትዮጵያ መን ግሥት ስም ምሽጉን በሙሉ ተረከቡ ። በዚሁም ጊዜ በስምምነቱ መሠረት እነዚያ ምጥዋ ናኩራ ታስረው የነበሩት ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ፣ ልጅ ብሥራት መንግሥቱ ፣ መምህር ሐናንያ ፣ ሊቄ ወልደ የሱስ ለራስ መንገሻ ተሰጡ ። * እንደዚሁም ራስ መንገሻ በእጃ ቸው የነበሩትን ማዦር ቶማሰ ሳልሳንና ሌሎቹንም የኢጣልያ ምር ኮኞች በይፋ አስረከቡና ባልዲሠራም ከነጭፍራው ወደ አሥመራ

---

* ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ከሸዋ ሔደው በደብረ ኃይላ ጦርነት ቆስለው የተ ማረኩ ፣ መምህር ሐናንያና ሊቄ ወልደየሱስ ስለእርቅ ከራስ መንገሻ ዘንድ ተልከው ሳለ ጄኔራል ባራቲዬሪ ሰላዮች ናችሁ ብሎ ያሰራቸው መሆናቸውን እናስገነዝባለን። ልጅ ብሥራትም የታሰረው በዚሁ ሰበብ ሳይሆን አይቀርም ።



ጉዞውን ጀመረ ። ከተማው አዲግራትና አውራጃው አጋሜም በፍጹም ከኢጣልያ ቁጥጥር ነጻ ሆኖ ለራስ መንገሻ ተመለሰ ።

በርክክቡ ጊዜ የኢጣልያ መኮንኖች ፣ “ለሰላም ንግግር የተላከ ውን ሳልሳን ማሰር እንዴት ይገባል” ብለው ራስ መንገሻን ቢወ ቅሷቸው ፣ ራስም መልሰው ፣ “ እንደዚህ ያለውን የተማርነው ከናንተው ነው ። ከሳልሳ በፊት ስለእርቅ የላክናቸውን እነመምህር ሐናንያን በማ ሰር የቀደማችሁ እናንተ ናችሁ” ብለው በማሾፍ መለሱላቸው ይባላል ።

# ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት

## የመስኮብ የቀይ መስቀል ሐኪሞች አዲስ አበባ መድረስና ያበረከቱት የሕክምና አገልግሎት

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ፣ በጄኔራል ስቬይቭ የተመራውን የመስኮብ የቀይ መስቀል ሐኪሞች አመጣጥና አገልግሎት እንደዚህ ሲሉ ባጭሩ ጠቅሰው አልፈውታል ።

> በዚህም ጊዜ የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት በኢጣልያ ጦርነት የቆሰለውን የኢትዮጵያ ሠራዊት መድኃኒት እያደረጋችሁ አድኑ ብለው የቀይ መስቀል ማኅበር ሐኪሞች ሰደዱ ። ሐኪሞቹም በሐምሌ 28 ቀን 1888 ዓ.ም. አዲስ አበባ ገቡ ። ለቁስለኛውም ለሐኪሞቹም ቤት ተሠርቶ መድኃኒት ማድረግ ዠመሩ ።[1]

ባለፉት ምዕራፎች ፣ ከዓድዋ ጦርነት በፊት የፊታውራሪ ዳምጠው ከተማንና የጓደኞቻቸውን መስኮብ ደርሰው መመለሳቸውን ፣ እንደ ተመለሱም ፊታውራሪው ወደ ዓድዋ ዘምተው በውጊያው ላይ መሞታቸውን አንብበናል ። አሁንም በዚያው በተወጠነው የወዳጅነት ግንኙነት መሠረት በሊዎንቴቭ አሳሳቢነት የሁለቱን መንግሥት ወዳጅነት ለማጠንከር በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል ውጊያው እንደማይቀር በመገመት ፣ የመስኮብ መንግሥት በአማካሪነትም በሕክምናም ኢትዮጵያን የሚረዱ በርከት ያሉ ሐኪሞችና የጦር መኰንኖች ያሉበት የቀይ መስቀል ጓድ አቋቋመ ።

በቅድሚያ ኮንት ሊዎንቴቭ ከፒዮትርቡርግ እ.ኤ.አ የካቲት 1 ቀን 1896 ዓ.ም. ወደ ዙሪክ ከተማ (ሲዊስ) ደረሰ ። በዚያም ወዳጁና ያጼ ምኒልክ ዋናው አማካሪ እንጂነየር አልፍሬድ ኢልግ በለገሐር

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕ.64 ፣ ገጽ 271

ጠብቆ ተገናኘው ። በዙሪክ በኢልግ ቤት ሲጨዋወቱ ካደሩ በኋላ ስለቀይ መስቀሉ ማኅበር ጓድ ጉዞ ከአውሮፓ በምጥዋ በኩል አድርገው ወደ ዐፄ ምኒልክ ለመዝለቅ ታስቦ ነበር ። የጓዱ አቅዋም የሕክምና ሰብአዊ አገልግሎት ባሕርይ ያለው ስለሆነ ፣ እንደዚህ ያለውን ጉዞ የኢጣልያ መንግሥት አይቃወምም የሚሉ ተስፋ ነበር ። በዚህም ጊዜ የዓድዋው ጦርነት ገና አልተጀመረም ። በየካቲት 23 ቀን ለመፈጸም ጥቂት ጊዜ ነው የቀረው ። በእርግጥም የተፈጸመውም ሊዎንቴቭና ጓዶቹ ወደ ኢትዮጵያ ለመድረስ በጉዞ ላይ እንዳሉ ነው ።

ነገር ግን ከኢልግ ጋር ሲመካከሩ ፣ የኢጣልያንና የኢትዮጵያን ጦርነት መባባስ ከሊዎንቴቭ የበለጠ በቅርብ የተከታተለው ኢልግ የምጥዋውን መስመር እንደማይሆን ስለ አስገነዘበው ጉዞው በፈረንሳይ የወደብ ከተሞች በማርሴይና በጅቡቲ በኩል እንዲሆን ተወሰነ ። ይህንንም ከኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሲኞር ብላን መመሪያ በመቀበል ፓሪስ የሚቀመጠው ካርሎ አልቤርቶ ማፌይ፣ “ለምን በፈረንሳይ ወደቦች ያልፋሉ” በማለት ለፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ክርክር አቅርቦ ነበር ። እንደዚሁም ማርሴይ የሚቀመጠው ካርካኖ የሚባለው የኢጣልያ ቆንሲል ጓዱ በማርሴይ ሲያልፍ ፣ የሰዎቹን ቁጥርና የያዙትን መሣሪያ ለማየት ተጣጥሮ ነበር ። ነገር ግን በወሬ ካልሆነ በቀር በትክክል ለማወቅ አልቻለም ።

የሆነ ሆኖ ፣ ከማርሴይ በየካቲት 16 ቀን ያራ በሚባል በፈረንሳይ መርከብ ተሳፍረው እስክንድርያ በደህና ከደረሱ በኋላ ፣ ከዚያም ኑብያ በሚባል መርከብ ተጉዘው ጅቡቲ ገብተው ከጅቡቲ ወደ ሐረር ገቡ ። በዚህም ጉዞ ላይ እንዳሉ የዓድዋ ድል ተፈጽሞ ንጉሠ ነገሥቱ በዓድዋና በአካባቢው ስለ እርቅና ስለ ምርኮኞች ጉዳይ በማዦር ሳልሳ አማካይነት ከጄኔራል ባልዲሣራ ጋር በመጻጻፍ ያንድ ወር ጊዜ ካሳለፉ በኋላ ፣ ወደ ሸዋ ለመመለስ አሸንጌ ሐይቅ አጠገብ ፈረስ ማይ እንዳሉ ሊዎንቴቭ ከጅቡቲ በግሥጋሤ መጥቶ ተገናኛቸው ። እርሳቸውና መኳንንቶቻቸውም በፍቅርና በደስታ ተቀበሉት ። ምንም እንኳን ስለ ወዳጁ ስለ ፊታውራሪ ዳምጠው መሞት ቢያዝንም ፣ በተገኘው ድል እንደሚደሰት የታወቀ ነው ። ከዚህ በኋላ ሌዎንቴቭ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጣ ። ሐኪሞቹና የጦር መኰንኖቹ ግን በግንቦት ወር ሐረር ገብተው ግማሾቹ እዚያው ሐረር ቆይተው የቀሩት በሙሉ በሐምሌ ወር አዲስ አበባ ገብተው ንጉሠ ነገሥቱና መኳንንቱ የጋለ አቀባበል አደረጉላቸው ።

የመልእክቱ ጓድ የበላይ መሪ ማዦር ጄኔራል ስቪዶቭ ሲሆን ቁጥራቸው እስከ ሰላሳ አንድ ይደርሳል ። ከነዚሁ አምስት የኤታ



ማዦር መኰንኖች ፣ ሰባት ሐኪሞች ከስድስት ረዳቶቻቸው ጋር ሁለት ፋርማሲስቶች ፣ ከአራት ረዳቶች ፣ ዐሥራ ሁለት የሴት ፣ ሐያ አንድ የወንድ አስታማሚዎች ፣ ሁለት አስተርጓሚዎች ካንድ መነኩሴ ጋር ፣ እንደዚሁም ፕሮፌሰር ፖሎቶቭ የሚባል የኢትዮጵያን ቋንቋና ሥልጣኔ የተመራመረ ይገኙባቸዋል ። የዘመኑ ጸሐፊ በጄኔራል የሚመራው የመስኮብ ጓዶች ብዙ ሹማምንት ፣ ብዙ የጦር የሕክምና መሣሪያ ስለያዙ በምኒልክና በመኳንንቶቻቸው ዘንድ ትንሽ ሥጋትና ጥርጣሬ ጥሎ እንደ ነበረና በኋላም በወዳጃቸው በኮንት ሊዎንቴቭና አገላለጥ ማግባባት ሁኔታው ተስተካከለ ። ከቀይ መስቀሉ ጓድ ጋር የመጡት የጦር መኰንኖች የአመጣጣቸው ዓላማ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል የተዠመረው ጦርነት እየባሰ የሔደ እንደሆነ በኢትዮጵያ ጐን ተሰልፈው ኢጣልያን ለመውጋት ፣ ጦርነቱ አልቆ እንደሆነ ከሁለቱም ወገን የቆሰለውን እያከሙ ለማዳንና በዚያውም ለዘለቄታ የሚሆን በሐረርና በአዲስ አበባ ነዋሪ የሕክምና ሆስፒታል ለማቋቋም መሆኑንም ገለጠ ። እያደርም ሁኔታው እንዳመቸ የመስኮብ መንግሥት በኢትዮጵያ ተደግፎ አንድ የወደብ ከተማ አግኝቶ በንግድና በፖለቲካ መስክ ለመጠቀም መሆኑን አብራርቶአል ።

ከዚያም ለሐኪሞቹ ከሁለት ላይ ለሕክምና ተስማሚ በሆነ ቦታ ላይ ቤት ተሠርቶ ሐኪሞቹ ቀዳጆቹም ፣ የወንድና የሴት አስታማሚዎቹም ከነመሣሪያቸው እሁለት ቦታ ተመድበው የሕክምና ሥራቸውን በትጋት ዠመሩ ። አሁን የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ባለበት ሥፍራ ዋናው የሕክምና ቤት ተሠርቶ ፣ ሠላሳ የሚሆን አልጋ ተዘርግቶ በየቀኑ ሁለት መቶ ሃምሳ ቁስለኛ ሲታከም ፣ ሐረር የቀሩትም እስከ አንድ መቶ ሰው ያክሙ ዠመር ። በዚህም ጊዜ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመስማማት የኢጣልያንንም ቁስለኞች አብረው በማከም በኢጣልያኖቹ በኩል ተመስግነዋል ። በጠቅላላው ከኢትዮጵያ ወገን የታከሙት ቁጥራቸው ዐሥራ አንድ ሺ ስድስት መቶ ሲሆን ፣ ከነዚሁ ሰባት መቶ ሃምሳ ቀዶ ጥገና የተደረገላቸው መሆኑን መስኮቦቹ የተዉት ሰነድ ያመለክታል ።

ቀጥሎም የመስኮብ መንግሥት ሌጋሲዮን ከተከፈተ ወዲህ ፣ በሌጋሲዮኑ የሚሠሩት የኮር ዲፕሎማቲክ አባሎች ከነጸሐፊዎቻቸው ቁጥራቸው በርክቶ የመስኮብና የኢትዮጵያም ወዳጅነት እየተስፋፋ ሲሔድ የእንግሊዝና የኢጣልያን ፣ ቀጥሎም እስካሁን ለሁለቱም ወዳጅ የነበረውን የፈረንሳይን መንግሥት ጨምሮ በመጠኑ ከሥጋት ላይ ጥሎ ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ የመስኮብና የኢትዮጵያ ወዳጅነት ሥር እየሰደደ ከመሔድ አላቋረጠም ። ያፄ ምኒልክ ፣ የእቴጌ ጣይቱና የመኳንንቱ ሁሉ

ምስጋና ለመስኮብ መንግሥትና ሕዝብ አላቋረጠም ። ዘቅናትና በምቀኝነት የሆነ ያልሆነውን እያስወሩ ብዙ የአውሮፓ ተወላጆች ሊዎንቴቭንም ከምኒልክ ለማጣላትና ለማራቅ ሞክረው ነበር ። ይሁን እንጂ አልሆነላቸውም ። እንዲያውም በመጨረሻ ያለፈ አገልግሎቱን በመገምገም በ1890 ዓ.ም. በግንቦት ወር ዳግማዊ ምኒልክ የራስ ተስማ የነበረውን የገሙ ጐፋን አስተዳዳሪነት ጨምረው ከሙሉ ሽልማት ጋር የደጃዝማችነት ማዕርግ ሰጥተው አከበሩት ።

ይኸን ሹመት ተቀብሎ በ1891 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ሲሔድ ፣ ልክ እንደ አንድ የኢትዮጵያ ከፍተኛ መኰንን በሁለት ሺ የእግረኛና የፈረሰኛ ወታደር ታጅቦ ተጓዘ ። ከእርሱም ጋር ዓረቦችና ሴኔጋሎች የራሱ ወገኖች እነፊታውራሪ ባቢቸፍ ፣ እነ ሰቢሎን ፣ ሌሎችም ዶክተር ካን ማሪዮስቡሼ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የተመደቡት አብረውት ነበሩ ። እሱም ልክ እንደ ኢትዮጵያ መኳንንት ልማድ ለበታቾቹ የፊታውራሪነት ፣ የቀኛዝማችነት . . .ማዕረግ እየሰጠ ለሠራዊቱም ግብር እያገባ በግብነት ጭፍራውን ያስደስት ነበር ይባላል።[1]

እንዲዚህ እምሮበት ወደግዛቱ ከገባ በኋላ ፣ ደጃዝማች ሊዎንቴቭ እንደቀሩት የኢትዮጵያ ደጃዝማቶች እንደአገሩ ልማድ አቅሙን ዐውቆ ሥልጣኑን ገታ አድርጎ በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ሥር እየታዘዘ በቀጥታ የተሰጠውን አውራጃ በጸጥታና በሰላም ማስተዳደር አልቻለም ።

በዚህ ፈንታ በወርቅ ፣ በብረት ማዕድን ፣ በዝሆን ጥርስ ንግድ ለመክበር ተነሣ ። ከንጉሠ ነገሥቱም ያስፈቅድ ከፈረንሳይ ፣ ከእንግሊዝና ከቤልጅክ የንግድ ኩባንያዎች ጋር በቀጥታ እየተጻጻፈ ማኅበር ለማቋቋም በአክሲዮን ተካፋይ እንዲሁኑ ሌሎቹን የማኅበር አባሎች እየጋበዘ የወርቅና የብር ሌላም ማኅበር ለማቋቋም ይጣጣር ዠመር ። “በገሙጐፋ ፣ በእሞ ወንዝ ግራና ቀኝ ያለው አገር ለሕይወት ጤናማ ሲሆን ወርቅ ፣ ብረታ ብረት ፣ ብርና መዳብ ለማውጣት የሚያመች ፣ እህልና ቡና ሌላውንም ማናቸውንም አዝርእት የሚያበቅል ገነት የሆነ መልካም አገር ነው ” እያለ የውጭን አገር ኩባንያዎች በማኅኅት ማኅበሮቹ እንዲቋቋሙ አደረገ ። ዳግ ምኒልክ በቅድሚያ ሳያስታውቅ ይኸንንም ሁሉ የሚጻጻፈው በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ መሆኑን መግለጡ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሲሰማ ታላቅ ቅርታ በገዛ እጁ ፈጠረ ። እንደ ቀድሞው በመወደድና በመክበር ፈንታ ፣ “ለሥልጣንና ለሀብት የጓጓ አታላይና ደፋር ነው” የሚል ግምት በቤተ መንግሥቱም ፣ በውጭ አገር መልክተኞችም ዘንድ አሳደረ ።

1 I Russi in Etiopia . . .PP. 237 - 256, 270 - 302.



ስለዚህ ፣ ይኸን ሁሉ የሰሙት ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ ምኒልክ አዲስ አበባ ለሚገኙት ለውጭ አገር መልክተኞች ሚኒስትሮች ለእንግሊዙ ለሚስተር ሐሪንግተን ፣ ለፈረንሳዩ ለሙሴ ላጋርድ ፣ ለመስኮቡ ለሙሴ አርሎቭ ፣ ለኢጣልያው ለሲኞር ቺኮዲኮላ በጻፉት ደብዳቤ ፣

> ደጃዝማች ሌዎንቲፍ በእንግሊዝና በቤልጅክ አገር ከኔ ያስፈቀደ በማስመሰል ብዙ የወርቅ የማዕድን ማኅበር ማቋቋሙን ሰማሁ። . . .በኔ በኩል በኢትዮጵያ መሬት ላይ የወርቅ ማዕድን ለማውጣት በምንም ዓይነት የፈቀድሁለት ነገር የለም ። . . .እስካሁን ወሬውን ሰምቼ በቶሎ ያልጻፍሁላችሁ ነገሩ ወሬ ስለ መሰለኝ እርግጠኛውን ነገር እስከረዳው ድረስ ብዬ ነው ። እርሱም ከኔ ፈቃድ ወጥቶ በራሱ ፈቃድ እንደዚህ ያለውን ነገር ያደርገዋል ብዬ ስለ አልጠረጠርሁ ነበር . . . አሁንም ይኸን ነገር ሐሰት መሆኑን ላገራችሁ መንግሥትና ሕዝብ ወደ አገራችሁ ስትመለሱ አስታውቁ . . .[1]

በማለት አስታወቁ ። እርሱም ከግዛቱ ተሸሮ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ በመጥፎ ሁኔታ ወደ አውሮፓ ተመለሰ ። ፍጻሜውን ለጊዜው አናውቅም ።

1 I Russi in Etiopia, PP. 368 - 371.

# ምዕራፍ ሃምሳ ሰባት

## ስለ ምርኮኞች ነጻነት የሮማ ሊቀ ጳጳስ ልዮን 13ኛና ዳግማዊ ምኒልክ የተለዋወጡዋቸው ደብዳቤዎች

በኢጣልያ አገር ፣ ስለ ዓድዋ ድል ብድር መመለስና አለመመለስ የተደረገው ሁካታ እያደር ሲቀዘቅዝ ስለ ምርኮኞቹ ያለው ሥጋትና ክር ክር እየበዛ ሔደ ። በተለይ የዚህ ሥጋት ያደረባቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የምርኮኛ ቤተ ሰቦች ናቸው ። እነርሱም የሞተውን ፣ የቆሰለውንና የተማረከውን በትክክል ለይተው ባለማወቅ ይህ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው ፣ የተማረኩትም ነጻ የሚሆኑበትን መንገድ የመንግሥት መሪዎችን እየፈለጉ በአቤቱታ አሰለቹዋቸው ። እያንዳንዱ የዘመዱን ሁኔታ ባለማወቅ ቤተሰቦቹ ምንም እንኳ ተቻኋሪዎች ሆነው መንግሥቱን ቢያስቸግሩትም ፣ በጠቅላላው የኢጣልያ ሕዝብ በጉዳዩ ማሰቡ አልቀረም ። በፊተኛው ዘመን ሕዝቡም ፣ ቤተ ክህነቱም ፣ ከመቀሌውና ከዓድዋ ጦርነት በፊት ስለ ወረራውና ስለውጊያው ፈቃደኛ ሆነው ለመዝመት ወይም ዘማቾቹን በዘፈን በመሸኘት ይደሰቱ ነበር ። አሁን ግን ፣ በዓድዋ የተረጋገጠው የኢትዮጵያ ድል አድራጊነት የሁሉንም ቅስም ስለ ሰበረው የቀኝ ክፍሎች ፣ "የመበቀያ ጦር እንላክ" ያሉትንም መንግሥቱን የተረከበው የግራው ክፍል " እይሆንም ከሰላም በቀር የሚያዋጣን የለም " ብሎ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ ስለ ወሰነ ፣ ባሁኑ የሁለም እሳብ ያተኮረው ኢትዮጵያ ላሉት ምርኮኞች እርዳታ የሚላከበትን መንገድ መፈለግ ብቻ ሆነ ። ንጉሡ ኡምቤርቶ ግን በዚህ ጊዜ እንደቀኙ ቡድን በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ብስጭት እድሮበት እርሱም እንደ ማኩረፍ ብሎ ተቀምጧል ።

ስለዚህ ፣ ከሕዝብ ውስጥ በተለይ ባንዲት ቼዛሪኒ በምትባል የንጉሡ የኡምቤርቶ የቅርብ ወዳጅ በሆነች የሚመራ የሮማ እመቤቶች የእርዳታ ማኅበር ተቋቋመ ። ዓላማው ለሕዝብ ጥሪ አድርገው የእርዳታ ገንዘብና ልብስ እንዲሰበሰብና እርዳታው ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ለምርኮኞቹ እንዲደርሳቸው ለማድረግ ነበር ። ይኸንኑ የሚያከናውኑ ሰዎች ተመረጡ ። የእርዳታውም ገንዘብ ከተሰበሰበ በኋላ ኮንት ካርሎ ቢርስዊዝ

የሚባለው ዋና መሪ ሆኖ ኡንዲንና ዋትካሜልን በመጨመር የእርዳታውን ገንዘብ ይዘው ከኢጣልያ አገር ተነሥተው ግማሾቹ በዘይላ ፥ ግማሾቹ በጅቡቲ በኩል ሲጓዙ ፥ ከጅቡቲ ወደ ሐረር መንገድ የጀመረው መሪው ኮንት ቬርስዊዝ በመንገድ በፀሐይ በትርታሞ ሐረር ሲደርስ ሞተ ። ሌሎቹ እነኡንዲን በኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ ወደ አዲስ አበባ መጡ ። አዲስ አበባ በደረሱ ጊዜም በ150 ወታደር የታጀቡ ሹማምንት መጥተው በታላቅ ክብር ተቀበሏቸው ። እንጂኒዬር አልፍሬድ ኢልግ በንጉሠ ነገሥቱ ስም ቀርበው የንጉሠ ነገሥቱን ሰላምታ አቀረቡላቸው ። በማግሥቱ በብዙ ካህናት ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥቱ ሔደው በአምስት ሰዓት ላይ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው ንግግር አድርገው ፥ የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ደብዳቤ እንዳስረከቡ ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ በላኩት ራፖር ላይ ገልጸዋል ።

ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከልዮን 13ኛ ለዳግማዊ ምኒልክ የተጻፈው ደብዳቤ ከኢጣልያንኛ ወደ አማርኛ ሲተረጐም ቃሉ እንደዚህ የሚል ነው ።

> በጣም ኃያል ለሆኑት ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከልዮን 13ኛ ፓፓ በጣም ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት ሰላምና ኀናንነት ለርስዎ ይሁን ። የጵጵስናችን ዘመን በጀመረበት ጊዜ የሊቀ ካህንነታችን ኢዮቤልዩ በተከበረ በ10ኛው ዓመት ልባዊ በሆነ ተግባር ሰላም ይሉን ዘንድ ወደዱ* ይህም የደግነት ምስክር መሆኑ ነው ። በዚህም ደግነት ልባችንና ልብዎ ተገናኝቷል ። ዛሬ አንድ ንጉሣዊ ልግሥና እንዲያደርጉ የምክር ቃላችንን ክርስቲያናዊና ንጉሣዊ ለሆነው ልብዎ ለመላክ አሰብን ። ይህ ድል ብዙ ምርኮኞች በእጅዎ ጥሎልዎታል ። እነዚህ ምርኮኞች በወጣትነታቸውና በጎልማሳቸነታቸው ዘመን የኑሮአቸው ተስፋ ባበበበትና የብርሃኑ ጐህ በቀደደበት ሰዓት ከገራቸውና ከቤተሰባቸው ተነጥለው ይገኛሉ ።
>
> የነርሱ ምርኮ የግርማዊነትዎን ዝናና ገናናነት ምንም ሊያስፋፋው አይችልም ። ይልቅ የነርሱ የምርኮ ጊዜ በረዘመ መጠን በሺ የሚቆጠሩት የእናቶቻቸውና የንጹሐኑ ሚስቶቻቸው የመንፈስ ሐዘን እየበዛ ሔዷል ። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበልነው ለክርስቲያን አገሮች ሁሉ በሚስፋፋው የተቀደሰ መልእክት (ሐዋርያነት) እንደ ልጆቻችን ያህል እንወዳቸዋለን ። ስለዚህ ያንድ አባት ልብ በቅድስት ሥላሴና በተባረከችይቱ ድንግል ወይም ከዚህ ዓለም በአለው በሚወዱት ስም የሚያቀርብልዎትን ልመና ይቀበሉና ሳይዘገይ

* ንጉሠ ነገሥቱ ከዚህ በፊት ከዚያው ከትግሬ እንዳሉ የጻፉላቸውን ሲያወሱ ነው ።



> ነጻነታቸውን ይስጡዋቸው ። ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ይኸን የደግነት ሥራ ባለመሥራት እምቢታዎን ባለም ነገሥታት ዐይን ፊት አይግለጹ ። ይህችን ክብር ያላትን ገጽ (ደብዳቤ) በመንግሥትዎ ዜና መዋዕል ያስመዝግቧት ። በወንድማማችነትና በሰብአዊነት ተግባር እንጻር ያለው የጦር መብት ምንድነው የዚህን ብድር ርኅሩኅ አባት እግዚአብሔር በብዙ ይከስዎታል ። እንደዚሁም በሺ የሚቆጠሩ ድምጾች ከነዚያው የመጀመሪያይቱ የኛ የምትሆን ባንድነት ሊያመስግኑዎ ይነሣሉ ።
>
> እስከዚያም ለንጉሣዊው ቤተ ሰብ እግዚአብሔር በረከት እንዲያወርድ እንለምናለን ። ሮማ አቅዱስ ጴጥሮስ አጠገብ 11 ግንቦት 1896 ዓ. ም. በ19ነኛው ዘመነ ጵጵስና ተጻፈ ።

ይህ ደብዳቤ ፥ ሊቀ ጳጳሱ ለንጉሠ ነገሥቱ ለዳግማዊ ምኒልክ የጻፉት ነው ። አጻጻፋቸው አክብሮት ያለበት ሆኖ ዐፄ ምኒልክ ከዓድዋ ድል በኋላ በእጃቸው ለወደቁት ምርኮች ርኅራኄ አድርገው በቶሎ እንዲፈቱዋቸው በአባትነት የሚለምን ነው ። እንደ እውነቱ ቢሆን ፥ የሮማ ሊቀ ጳጳስ የክርስቲያኖች ሁሉ የበላይ አባትነት እንደሚሰማቸው ሁሉ አስቀድሞ ኢጣልያኖቹ ባሕር ተሻግረው ፥ “የሰው አገር ካልወረርን” ብለው ለጦርነት ሲዘጋጁ ፥ የአምባላጌና የመቀሌ እልቂት በተደረገበት ጊዜ ሁሉ ከሁለቱም ወገን ለሚፈሰው ደም በመራራት እቅርባቸው የሚገኙትን እንደ ልጆቻቸው የሚመለከቷቸውን ንጉሡን ኡምቤርቶንና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ክሪስፒን ፥ “የሰው አገር ለመውጋት ጦር አትላኩ የሰው አገር መፈለግ ይቅርባችሁ” ብለው አልመከሩዋቸውም ። ሶሺያሊስት የሆኑት ጣልያኖች የተቃወሙትን ያህል እንኳን ቀርቶ ከዚያም ያነሰ ለዚህ ለግፈኛ ወራሪነት ያባትነት ድምፃቸውን አሰሙ የሚል ጽሑፍ አልተገኘም ። ከዚህ በፊት እንዳል ነው የርሳቸው ምኞት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በጦርም ይሁን በፖለቲካ ይዛ በበላይ እንድታስተዳድር የመንግሥቱን ሥልጣን መከታ አድርገው የሮማ ቤተ ክርስቲያን ቢቻል መላውን ፥ ያለዚያም የተቻለውን ያህል የካቶሊካውያንን ቁጥር አበርክተው መንፈሳዊ ሥልጣናቸው በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ነው ። አሁንም ምኒልክ ከዚያው ከዓድዋ በመጋቢት ወር ላይ ለጻፉላቸው ሮሮ ፥ “እውነትዎን ነው ፥ የኢጣልያ ንጉሥና ጠቅላይ ሚኒስትር አገርዎን ለመውረር በመሞከራቸው አጥፍተዋል” አላሉም ።

ይሁን እንጂ ፥ ዐፄ ምኒልክ ምንም እንኳ የሊቀ ጳጳሱ ንግግርና የምርኮኞቹም ሁኔታ ቢያሳዝናቸው ፥ በእጃቸው የወደቁትን ምርኮኞች ፥ ስለ ወሰኑም ጉዳይና ስለ ግናቸውም አንድ ውል ከማድረጋቸው በፊት መልቀቅ ፥ ለመንግሥታቸውና ለሕዝባቸው እንደገና ሁከት መፍጠርን ስለሚያስከትልባቸው ፥ የዚህን የችግራቸውን ምክንያት የሚገልጽ ደብዳቤ አዘጋጅተው ሞንሲኞር መቃርዮስን መልሰው ላኩዋቸው ። የላኩት ደብዳቤ ትክክለኛ ግልባጩ የሚከተለው ነው ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአ
ብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ወደ ከበሩ ወደ ተቀደሱ የሮም ሊቀ ጳጳሳት ሊዮን 13ኛ
ሰላም ለርስዎ ይሁን ። የከበረው ያባትነትዎ ደብዳቤዎ ባቡነ መቃርዮስ
እጅ ደረሰልኝ ። በዚህም ደብዳቤዎ የቀድሞው መላላካችንን አሳምሮ
የሚያስታውስ ፣ እግዚአብሔር ከኔ እጅ የጣላቸውን ስለ ኢጣልያ ምርኮ
ኞች የሰብአዊነት ሥራ እንድሠራ የሚያመለክት መሆኑን በጣም አየሁ ።
ደግሞም የከበረ ቅድስናዎ ከአቡነ መቃርዮስ የበለጠ መልክተኛ ነገ
ሩን በጣም አስረድቶ አጣፍጦ ሐሳብዎን የሚናገር መላክ እንዳይቻ
ልዎ ዐወቅን ። የክርስቲያን ሁሉ አባት የላከው እጅግ የሚያስደንቅ
ደብዳቤዎን ባነበብሁ ጊዜ ልቤን መታው ። ዳግመኛም የከበረውን የመ
ልክተኛዎን የቃል ንግግር በሰማሁ ጊዜ ልቤ ቅድስናዎን በማክበር ስለ
መኑኝ ጉዳይ ለመፈጸም ጨክኖ ነበር ። እኔ ሳልፈልገው በዚህ በከፋ ጦር
ደማቸው ስፈሰሰው በክንቱ ላለቁት ወታደሮች እጅግ አለቀስሁ ። ነገር
ግን ፣ ቅድስናዎ የተመኙትን ለመፈጸም የኢጣልያ መንግሥት ያልታሰ
በው የዛሬ ሥራቸው የማያስፈጽመኝ ሆነ ። ይህንንም ማለቴ የእርቅ ፈቃ
ድና በደህና ስመላላክ መመኘታቸውን ካሳዩኝ በኋላ ፣ ሥራቸው በጦርነት
እንደ አለን አድርገው ይሔዱ ኸመር ። አሁንም የሚገባኝ ንጉሥነቴና
የሕዝብ አባትነቴ ይህን ዐውቆ በእጄ ያለውን የእርቅ መያዣ መል
ቀቅ የማይቻለኝ ሆነ ። ቅድስናዎ ያሰበውን ሐሳብ ደስ ለማሰኘት የኔም
መልካሙን ሐሳብ ለመፈጸም ከለከሰኝ ። በክርስቲያንነቴና በንጉሥነቴ
ልብ አውጥቼ አውርጄ ሳበቃ ፣ የፍቅሬን ምልክትና ብዙ ማክበሬን
በሌላ ቀን አደርገዋለሁ ማለት ስለ ሆነብኝ ዛሬ ሳይሆንልኝ በመቅ
ረቱ እጅግ ያሳዝነኛል ። እግዚአብሔር አደራ የሰጠኝ መንግሥቴን
የሕዝቤን ነጻነት የምፈልግ ስለሆንሁ ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ በማክበር
የሚሰማውን የቅድስናዎን ድምፅ ለኛ ብለው እንዲያሰሙልን ተስፋ
አለን ። ይህ የሆነ እንደሆነ ከዘመዶቻቸውም ስተለዩ ምርኮኞች በቅ
ርቡ ለመመለስ እንዲመቹን ማድረግም ነው ። ነገር ግን ይህ ነገር እስ
ኪጨረስ ድረስ ከኔ ዘንድ ያሉትን ምርኮኞች እንደ ክርስቲያን ሥራ
ከዚህ ቀደም ጠብቄ በመልካም አድርጌ እንዳኖርኋቸው ይልቁንም
ከእንግዲህ ወዲህ ስለእርስዎ ፍቅር በጣሙን ጠብቄ በደህና አሳምሬ
እንዳኖራቸው በዚህ አይጠርጥሩኝ ። መስከረም 12 ቀን በአዲስ አበባ
ከተማ ተጻፈ ። በ1889 ዓመተ ምሕረት ።1

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ
ልመና እስረኞቹን ለመልቀቅ አስበው ሳለ ፣ በመካከሉ የኢጣልያ መን
ግሥት ባንድ ወገን ፣ "ሰላምና መልካም ግንኙነት አደርጋለሁ" እያለ
በሌላ ወገን የበደል ሥራ መፈጸሙን ስለ ቀጠለ ፣ የምሕረት አሳባቸውን

1 Bibliothecae Apostolicae Vaticanae Codice Manu SCR1PT1 . . .
በቁጥር 88 የሚገኝ ። Adua- E. Bellavita PP. 447 - 449



እንደለወጡ ያስረዳል ። ይህ በደል የተባለው "ዶልዊክ" የሚባል የሆ
ላንድ መርከብ ወደጅቡቲ ለንግድ ሲመጣ "በውስጡ ለኢትዮጵያ መን
ግሥት የሚሆን የጦር መሣሪያ ጭኗል" ብለው በሆላንድ ያሉ የኢጣ
ልያ ዲፕሎማቶች ስለጠቆሙ ፣ መርከቡ የባብ ኤል መንደብን የባሕር
ሰርጥ አልፎ ጅቡቲ ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ፣ በኢጣልያ መንግሥት
ትእዛዝ ኢይና የሚባለው የኢጣልያ የጦር መርከብ በማሳደድና በመ
ማረክ ወደ ምጥዋ ሔዶ እንዲራገፍ አስገደደው ።

ሃይማኖታቸው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሆነው የቂሳርያ ኤጲስ
ቆጶስ ክቡር አባ መቃርዮስ የሊቀ ጳጳሱን ደብዳቤ ይዘው መጥተው
እስረኞቹን ለማስፈታት በቤተ መንግሥቱ እጠገብ ተቀምጠው ዐፄ
ምኒልክን ደጅ ይጠኑ ነበር ። በዚሁ ሰዓት ዐፄ ምኒልክም፣ "ሊቀ ጳጳሱንና
አባ መቃርዮስን ደስ ለማሰኘት ሙሉውን ምርኮኛ ያም ቢቀር በመስ
ኮብ ንጉሠ ነገሥት ልደት የለቀቁትን ያህል ሊለቁ ነው" እየተባለ
ይወራ ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱና አማካሪዎቻቸው ስለዚሁ ጉዳይ በሚመ
ካከሩበት ጊዜ በመካከሉ፣ "ለኢትዮጵያ መሣሪያ የያዘውን የሆላንድ
መርከብ ኢጣልያኖች ማረኩት" የሚለው ወሬ ሲደርስ ነገሩ ወዲያው
ደፈረሰ ። በዚህም ዓይነት የኢጣልያ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር የጀ
መረውን የጠብ መንገድ አልተወም ተብሎ ተገመተ ። መቃርዮስ ለር
ዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በጻፉት ራፖር ላይ ፣ "ንጉሠ ነገሥቱ ጄኔራሉንና
የጦር መኰንኖቹን አስቀርተው ፣ የቀረውን ምርኮኛ ወታደር በሙሉ
ለመልቀቅ ተስፋ ከሰጡኝ በኋላ በመካከሉ እንጅኒየር ኢልግ "በመር
ከቡ መያዝ ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ አሳባቸውን ለወጡ ብሎ እያ
ዘነ ነግሮኛል" ሲሉ ጠቅሰዋል ።

ይሁን እንጂ ፣ የምርኮኞቹን አለመለቀቅ የአሰናከለው የመርከቡ
መማረክ ብቻ አይመስልም ። ነገር ግን አጥቂና ወራሪ ሆኖ የመጣው
የኢጣልያ ጦር ምንም እንኳን በዓድዋ የተሸነፈ ቢሆን ፣ ጄኔ
ራል ባልዲሡራ ኤርትራ ከመጣ ወዲህ ያዲግራትን ምሽግ ለማ
ስለቀቅ ከነራስ ስብሐት ጋር ለጦርነት ተሰልፏል ። "እንደገና መረብ
ንም ተሻግሮ የዓድዋን ብድር ሊበቀል ከነራስ መንገሻ ጋር ውጊያ
ለመግጠም ያስባል" እየተባለ በሚወራበት ሰዓት ፣ የመርከቡ መማ
ረክ ስለ ተጨመረ ደንበኛ ውል ሳያደርጉ እነዚህን እንደ ዋስትና በእጃ
ቸው የወደቁላቸውን ምርኮኞች በሊቀ ጳጳሱ ልመና ፣ በአባ መቃርዮስ
ደጅ ጥናት ብቻ መልቀቅ እንደማይገባ ጉዳዩ በምክር ተጠንቶ ተወስ
ኗል ማለት ነው ። እርሳቸውም ራሳቸው ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በጻፉት
ደብዳቤ ውስጥ ፣ "ራሴንና ቅዱስነትዎን ደስ ለማሰኘት ስል የሰላም
መድን የሚሆኑትን ምርኮኞች በዚህ ዓይነት ሁኔታ እያለን ለመልቀቅ

በሕዝብ ላይ ያለኝ የአባትነትና የንጉሥነት ተግባር ይከለክለኛል ” ሲሉ የጨመሩት ቃል ነገሩን በትክክል አብራርቶት ይገኛል ።

ከዚህ ቀደም እንዳልነው ፣ የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን ጠረፍ ወርሮ እስከ አምባላጌ ሲደርስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በነገሩ ገብተው ለመገላገል እንኳ አልሞከሩም ። አሁንም በርሳቸው አማላጅነት ንጉሠ ነገሥቱ ምርኮኞቹን ከለቀቁ በኋላ ፣ ወዲያው ጄኔራል ባልዲሠራ በምኒልክ በኩል የተጠየቀውን ለማሟላት የሚችል መሆኑን ለመሞከር እንኳ ይሞክሩ ይሆናል ብንል የኢጣልያ መንግሥት እሺም እምቢም ለማለት ነጻነት ስለአለው ፣ ለዚህ ምንም ዋስትና የሌለው ነገር መሆኑ የታወቀ ነው ። የኢጣልያ መንግሥትም ከተመቸው ከእሺታ ይልቅ ወደ እምቢታው ማዘንበሉ ግልጽ ነው ። ደግሞ በዚህ ላይ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በአካል ኢጣልያዊ ከመሆናቸው በቀር የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖቷን የምታስፋፋውና የተከታይ ቁጥር የምታበዛው ከጥንት ጀምሮ የካቶሊክ ነገሥታት ከእስፓኝ ፣ ከፖርቱጋልና ከፈረንሣይ እየተነሡ በደቡብ አሜሪካና በአፍሪካ ሰፋፊ አገር እየወረሩ የቅኝ ግዛት ባስፋፉ መጠን መሆኑ በማንም ዘንድ ይታወቃል ። አሁንም የኢትዮጵያውያን አሸናፊነት ጉዳዩን አሰናከሉት እርሳቸውም የምርኮኛ ቤተሰብ ስለ አስቸገራቸው ነው እንጂ ፣ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ዓድዋ ላይ አሸንፋ መላዋን አገሪቱን ብትይዝ ደስታ እንደሚሰማቸው የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴውን ልኮ ደንበኛ የሰላም ውል አድርጎ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት እስኪያውቅ ድረስ እነዚህ ምርኮኞች እንዳሉ እንዲቆዩ ያደረጉበትን ምክንያት እንዲገነዘቡላቸው ከዚህ በላይ ያነበብነውን አስተዛዛኝና አጽናኝ ደብዳቤ በመጨመር ፣ በተለይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለእስረኞቹ ልዩ እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው አረጋግጠው አባ መቃርዮስን መልሰው ላኩ ።

የሮማ ርእሰ ሊቃ ጳጳሳት ልዮን 13ኛ ከሮማ አንድ ታላቅ የካርዲናልነት ማዕረግ ያለው በመላክ ፈንታ አባ መቃርዮስን አርቶዶክሳዊ የቂማርያ ኤጲስ ቆጶስ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ረዳት የሆኑትን የሊቀ ጳጳሱን ደብዳቤ ይዘው እንዲመጡ ያደረጉበት ምክንያት ለኢትዮጵያውያንና ለዐፄ ምኒልክ እንደ ሃይማኖት አባት ስለሚቆጠሩ ፣ በመንፈሳዊ አባትነት በማባበል ነገሩን አቃንተው ምርኮኞቹን ሊያስፈቱ ይችላሉ በሚል ተስፋ ነው ። አሁንም አባ መቃርዮስ በዚህ ዓይነት የመልሱን ደብዳቤ ይዘው ወደ ሮማ ሲመለሱ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱን ለማስደሰት ሲሉ ፣ ዐፄ ምኒልክ እስረኞቹን ለመልቀቅ የተቸገሩበት ምክንያት በሙሉ እንደ ተገለጸላቸውና እንደ ተረዱት ፣ አዲስ



አበባ በሰነበቱበት ጊዜ ሁሉ መልካም መስተንግዶ እንደ ተደረገላቸው ከንጉሠ ነገሥቱም ሲሰናበቱ ለመታሰቢያ ትልቅ መስቀል ተቀብለው በደስታ ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ እንደ ተመለሱና ከዳግማዊ ምኒልክ የተጻፈውን ደብዳቤ ለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እንዳስረከቡ እኚሁ አባ መቃርዮስ በኋላ በጻፉት ራፖር ላይ በሰፊው ገልጸውታል ።[1]

በዚህ አወዛጋቢ ጉዳይ መሐንዲስ አልፍሬድ ኢልግ እየገቡ በማማከር አባ መቃርዮስን እየመሩ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ በማቅረብና በማነጋገር ፣ ደብዳቤውንም በማዘጋጀት ይሠሩ እንደነበሩ በዚሁ ራፖር ላይ ተጠቅሷል ። ስለዚህ ይኸን የመሰለ ከፍ ያለ የፖለቲካ ጉዳይ ሲገጥም ከሌሎቹ ይበልጥ ከፈረንጆች ወገን እኚሁ የስዊስ ተወላጅ ሙሴ ኢልግ ፣ የፈረንሣዩ ተወላጅ ሙሴ ሞንዶን ፣ የመስኮብ ተወላጅ ኒኮላ ሊዮንቴቭና ከኢትዮጵያ ወገን ደግሞ ራስ መኰንን ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄ አስተርጓሚው ግራዝማች ዮሴፍና ሌሎችም የማናውቃቸው በምክር ፣ በተግባርም የንጉሠ ነገሥቱ የሥራ ተካፋይ መሆናቸው እርግጥ ነው ።

ስለዚህ ፣ የእስረኞቹ መለቀቅ ጉዳይ ከኢጣልያ መንግሥት ጠርነት ወይም ሰላም ፈላጊነት አቋም ጋር የተያያዘ መሆኑን የኢጣልያ መንግሥትም ፣ የሮማ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ተረድተውታል ። ስለሆነም የኢጣልያ ንጉሥ ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ኩርፊያው የማያዛልቅ መሆኑን በመረዳት ስለዚህ በመጨረሻ ባለሙሉ ሥልጣን ወኪሉን ወደ አዲስ አበባ ልኮ ደንበኛ ውል እንዲዋዋል ተገደደ ።

1 Storia Diplomatica C. Rossetti—PP.183—206

## ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት

### ማዦር ቼዛሬ ኔራሲኒ የመዋዋል ሥልጣን ተቀብሎ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣ

ዐፄ ምኒልክ ፥ ከእቴጌ ጣይቱና ከቅርብ ረዳቶቻቸው ጋር ከዓድዋ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው እንደገቡ የቀሩትም ታላላቅ መሳፍንትና መኳንንት ከታናናሽ ሹምምንትና ከተከታዮቻቸው ጋር ወደየአውራጃቸው ተመለሱ። ቤታቸውን ለረጅም ጊዜ ለቅቀው በዘመቻው ምክንያት ሲንከራተቱ የነበሩ ሁሉ ፥ ባሁኑ ጊዜ ይነስ ይብዛ የስምንት ወራት ጣመናቸውን በየቤታቸው በማቃለል ላይ ይገኛሉ ። ዘመዱና ወዳጁ የሞተበት ፥ የቆሰለበትና አካሉ የጐደለበት ወገን ሐዘንተኛ መሆኑ ባይቀርም ቁስለኛውም ፥ አካሉ የጐደለውም ሁሉም ባሁኑ ጊዜ በተገኘው ድል ይነስ ይብዛ መጽናናቱ የማይቀር ነው ።

በዚህ መካከል ፥ ባፄ ምኒልክና በቅርብ ረዳቶቻቸው መንፈስ የሚመላለሰው በምፅዋ በኩል አዲስ ጦር ይዞ የመጣው ዤኔራል ባልዲሡራ የልብ ልብ በቅቶት ያለፈውን የመሸነፍ በቀል ለመመለስ መረብን ተሻግሮ ራስ መንገሻ ዮሐንስን ማጥቃት ይዠምርና ወደ ጦርነቱ እንመለስ ይሆን ወይስ ፈረስ ማይ ሳሉ ፥ በማዦር ሳልሳ አማካይነት የተወጠነው የሰላም ድርድር ወደ ፍጻሜ ይደርስ ይሆን የሚል ነው ። ይኸም ማለት በጦር የተሸነፈው የኢጣልያ መንግሥት ፥ “ ከእንግዲህ ወዲህ የጦርነት ነገር በቃኝ ። የውጫሌን ውል ሠርዤ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነትና መንግሥት ዐውቃለሁ ” ብሎ ለመዋዋል እንደራሴ ይልክ ይሆን የሚለው አወላዋይ ሁኔታ ነው ። ምንም እንኳ ፓሪስ ባሉት በነአቶ ዘውገ (ነጋድራስ) ወይም በፈረንሳዮቹ በነሙሴ ሽፍነና አቦክ በሚገኙት በነሙሴ ላጋርድ አማካይነት ውሎ አድሮ የኢጣልያንን መንግሥት አቅዋም መስማታቸው ባይቀር በሮማ የሚደረገውን ግርግር በሶሻሊያሊስቶቹ ተጽእኖ ፥ በኢኮኖሚም ውድቀት በክሪስፒ እግር የተተካው ዲ ሩዲኒና አብዛኛው የካቢኔው የምክር ቤት አባሎች ከእንግዲህ ወዲያ ሰላም እንጂ ፥ ጦርነት አለመፈለጋቸውን የየዕለቱን የኢጣልያን መንግሥት አቅዋም ምኒልክና ረዳቶቻቸው በትክክል አያውቁትም ። መወላወሉንም የሚፈጥረው ይኸው ያለማወቅ ሁኔታ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፡ የኢጣልያ መንግሥት ወደ ሰላም ለመመለስ ከተገደደበት ከጦርነቱ አለመሳካት በቀር የእስረኞቹ በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ መቆየትና የየምርኮኛው የቤተሰብ አባል በየዕለቱ የሚያቀርበው አቤቱታና ውትወታ ነው ። የዚህ ሁሉ ተጽዕኖ አስገድዶ ባለፈው እንዳነበብነው ፡ በምክር ቤት የሰላሙ መንገድ በድምፅ ብልጫ ካለፈ በኋላ ወዳጄ ምኒልክ ተልኮ በውል እስረኞቹን ለማስፈታት የሚችለው ሰው ሲመረጥ ምርጫው ከማገር ቼዛሬ ኔራሲኒ ላይ ወደቀ ።

ማገር ኔራሲኒ እንደ እ.አ.ኤ. በ1849 ዓ.ም. በሞንቴች ላቺእኖ (ሲዬና ደቡብ ኢጣልያ) ተወልዶ ያደገ ነው ። ካደገ በኋላ ደንበኛ ሥራው ሕክምና ነበረ ። ከኢጣልያ ወደ ምሥራቅ በሚመላለሱ መርከቦች ላይ የሁለተኛ ደረጃ ሐኪም ሆኖ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ወደ ውጭ ጉዳይ ተዛውሮ በፖለቲካና በስለላ ሥራ ተሠማራ ። ከኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ በሚመላለስበት ጊዜ እ.ኤ.አ. በ1885 ዓ.ም. ዐፄ ዮሐንስ ዘንድ መጥቶ ተገናኝቷል ። ከዚያ ወዲህ ከኢጣልያ ወደ አሥመራ ምቀሌ ፡ ዓድዋ ፡ ሐረር ፡ ዘይላ ከዚያም ወደ ኢጣልያ በመሔድ ኢትዮጵያ ስለምትወረርበት መንገድ በመላላክ ብዙ ጊዜ ተመላልሷል።

የመልዕክቱ ዋና መሠረት ፡ በስሜን በኩል በትግሬ ራስ መንገሻን በምሥራቅ በኩል በሐረር ራስ መኰንንን የተለያየ የንጉሥነት ተስፋ በመንግሥቱ ስም እየሰጠ ካፄ ምኒልክ ሥልጣን ለይቶ ለማሸፈትና በግርግሩ መካከል የኢጣልያ ሥልጣን በኢትዮጵያ ላይ እንዲዘረጋ ለማድረግ ነበር ። በዚህ ምክንያት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከብላን መመሪያ እየተቀበለ ባደረገው ተንኮል ከጓደኛው ከደማርቲኖ ጃኮሞ ጋር ሆኖ በኋላ ባፄ ምኒልክ የፖለቲካ ዘዴ ሊፈርስ የቻለውን በምኒልክ ጀርባ በ1883 ዓ. ም. እ. ኤ. አ. በሐምሌ ወር ላይ በስሜን ኢትዮጵያ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት አስፋፊ የሆነውን ጄኔራል ጋንዶልፊንና ራስ መንገሻ ዮሐንስን መረብ ላይ ማዋዋሉ ይታወሳል ።

ይኸም አያያዝ ፡ በስሜን በኩል እነሊዎፖልዶ ትራቨርሲ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ከቀረ በኋላ ፡ በኢጣልያ መንግሥት ትዕዛዝ ከአሥመራ ወደ ሐረር ተዛውሮ የራስ መኰንንን አቅዋም ፡ የጦራቸውን ድርጅት በሚሰልልበት ወቅት ከመንግሥቱ በመታዘዝ በተቻለ መጠን ራስ መኰንንን ካፄ ምኒልክ ለማስከዳት በሐረር ብዙ ጊዜ ተቀምጦ ቢሞክርም ሳይሳካለት ቀርቶአል ። በስሜን በኩል ጦርነቱ የማይቀር መሆኑን ሲረዳው ከሐረር ወደኤደን ይልቁንም ወደ ዘይላ እየተመላለሰ ፡ ከባለሥልጣኖቹ እንግሊዞች ጋር በመመሳጠር በዘይላ አድርጎ ወደ ሐረር የሚደርስ የጦር ግንባር ለመክፈትና ወደስሜን የዘመተውን ጠቅላላ የኢትዮጵያ



ጦር በሁለት ወገን ጠምዶ ግራ ለማጋባት ሙከራ ማድረጉ ከዚህ በፊት ተመልክቷል ።

ቀጥሎ በሁሉም አንጻር ተስፋ የማይቆርጠው ቼዛሬ ኔራሲኒ ፡ በተለይ በኢጣልያ አገር ያሉት ባለሥልጣኖችና በሰሜን ኢትዮጵያ ያሉት ጄኔራሎች ፡ "የምኒልክ አቅም ሲገታን ከቶ አይችልምና ከምጥዋ እስከ እንጦጦ መውረር ነው" የሚለው ፕሮግራም እንዳስጐመጀው በመግለጽ እ.ኤ.አ. በ1895 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር ለወዳጁ ጽፎ እንደነበረው ሁሉ፥ አሁንም የዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ላይ የምኒልክን የጦር ድርጅት ለመከፋፈል ሲል ጉግሣ ዳርጌን ከአውሮፓ ወደ አሥመራ ያመጡት ጊዜ በጦርነቱ ሰዓት ከተማውን ለሚጠብቁት ላባትዬው ለራስ ዳርጌ የማግባቢያ ቃል ጽፎ ኖሮ ሐቀኛውና ታማኙ ሽማግሌ ራስ ዳርጌ ፡ "ኔራዚኒ የተባልከውን ናዚራ እባብ ያስመስልሃል" ብለው በማሾፍ የመለሱለትን እናስታውሳለን ።

በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ፡ በፖለቲካና በስለላ ሥራ እንጂ የውትድርና ሙያ ስለሌለው ውጊያውን አልተካፈለም ። በዚያን ሰዓት እሱ ከዘይላ ወደ ሐረር የሚላከውን የአዲሱን ጦር ግንባር ጉዳይ ለመምከር በኤደን ነበር ። በዚህ ወደብ ባንድ ሆቴል ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ፡ የኢጣልያን ጦር የመሸነፍ ወሬ ሬውተር የሚባለው የእንግሊዝ የወሬ ተላላኪ በቴሌግራም ወደ እንግሊዝ አገር ሲያስተላልፍ ሳያስበውና ሳይጠረጥር ስለሰማ ታላቅ ድንጋጤና ብርክ ወረደበት ። የሚያደርገውንም አጥቶ መንፈሱ በሐዘን ፡ ሰውነቱ በድንጋጤና በመሸበር ተበጠበጠ ። ስለዚህ በኢጣልያ አገር ላለው ትንሽ ትልቁን ለሚጽፍለት ባለሥልጣን ወዳጁ ለጄኔራል ሉቺኖ ዴል ቬርሜ ጦርነቱ በተደረገ በአምስተኛው ቀን እ.ኤ. አ. መጋቢት 5 ቀን 1896 ከኤደን በጻፈለት ደብዳቤ ውስጥ እንደዚህ የሚሉ ቃላት ሠፍረዋል ።

> የተወደዱ ጄኔራል የምታጽናና አንዲት ቃል እባክዎ ይጻፉልኝ ፡ እኔ ከሦስት ቀን ወዲህ (ወሬ ከሰማሁበት) ሕይወትም ደምም የለኝም ። እንዴት ያለ አደጋ ሆነ! አንዴት ያለ የሞራል በትር በላያችን ደረሰ! እኔ በድል አድራጊነታችን ተማምኜ ነበር . . . እዚህ አደን ሆቴል ፈረንሳዮች ስለሞሉ በላዬ ላይ ያለውን ጭንቀት ሊገምቱት ይችላሉ ፤ እንግዲህ የኢትዮጵያ ኩራትና ትምክህት የት ይሆን መድረሻው . . .[1]

እንግዲህ ይኸ ሰውዬ ነው አሁን ከኢጣልያ መንግሥት ሥልጣን ተቀብሎ ካፄ ምኒልክ ጋር ሊዋዋል ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው ። ቀደም ብሎ በሮማ በምርጫው ጊዜ ግማሾቹ ከፍ ያለ የጄኔራልነት

---

1 Precursori del' Impero Africano - R. Truffi PP. 101 103, 128 - 129, 146 - 148

ማዕረግ ያለው ቢላክ ይሻላል ሲሉ እርሱ ደግሞ ፡ ኤደን ላይ እንዳለ በወገኖቹ በመደገፍ ያገሩን ባህልና ቋንቋ እንደሚያውቅና የራስ መኰንን ወዳጅ በመሆኑ መልዕክቱን ለማከናወን እንደሚችል ስለአመለከተ ፣ የመልክተኝነቱ ሥልጣን በርሱ ላይ ስለተመደበ ወደ ሐረር ለራስ መኰንን ሥልጣን አግኝቼ መጥቻለሁና ንጉሠ ነገሥቱ እንዲቀበሉኝ እያለ ደጋግሞ በመጻፍ ይወተውት ዠመር ። ወዳጄ ምኒልክም ደብዳቤ እያደይዞ ልኮላቸው ነበር ። ዳሩ ግን ፣ የርሱን ተንኰልና መርዛማ ጠላትነት አሁንም በመንፈሱ ላይ የደረሰበትን ብስጭት የኛዎቹ አያውቁም ። በዚህ ምክንያት ለጻፈላቸው ደብዳቤ ራስ መኰንን ነሐሴ 7 ቀን 1888 እንደዚህ ሲሉ መለሱለት ።

የተላከ ከራስ መኰንን የሐረርና የአውራጃዋ ገዥ ይድረስ ከወዳጄ ከማዥር ናራሲኒ . . . በሰኔ በ27 ቀን ዓመተ ምሕረት 1896 እ.ኤ.አ. ዘኢላ ከተማ ወደ ጃንሆይ የላከውን ደብዳቤ ላከሁት ። ጃንሆይም የደብዳቤህን ቃል አይተው የዚህ ቀደሙን ወዳጅነታችንን የሚያስታውስ ቃል ነበርና ብዙ ደስ አሰኛቸው ። ወደ ጃንሆይም ለመውጣት ፈቅደውልሃል ። አሁንም መምጣትህ ከሆን ከዘኢላ ሳትነሣ እኔ ስለ ወዳጅነቴ የሚጠቅምህን አንድ አንድ ምክር ላመልክትህ ። ጃንሆይን ዳግማዊ ምኒልክ ከኢጣልያ ጋር የጠፋውን ፍቅር ለመመለስ አይጠሉም ፤ ይፈልጉታል እንጂ ። ስለዚህ መንግሥታችሁ ከኢትዮጵያ ጋራ እንደገና ፍቅርን ለመጀመር ከፈለገ የሚቀናውን የጃንሆይ አሳብ ላመልክትህ ። መጀመሪያ ነገር የውጫሌ ውል ፈጽሞ ካልጠፋ ኢትዮጵያም ፡ ራሷን የቻለች ለራሷም የምትበቃ ባለ ነጻ መንግሥት መሆኗን የኢጣልያ መንግሥት ካልተቀበለ ካላወቀ ፣ ይኸውም በጐረቤቶቻችን በሮጳ (አውሮፓ) ነገሥታት ምስክርነት ካልተጨረሰ ፣ የምትመጣበት ጉዳይ ይቃናልህ አይመስለኝም ። በከንቱ መንገድ አይምታህ ። ለምርኮኞችም የሚጠቅም ነገር ለማድረግ አይመችህም ።

ሁለተኛ ነገር ይኸን ሁሉ የተናገርነውን ነገር የሚፈጽም ሙሉ ሥልጣንህን የሚያስረዳን የታመነ ፣ የተደላደለ ከንጉሡ ከውጭ አገር ሚኒስቴር ከጦርነት ሚኒስቴር በመንግሥታችሁ ማኅተም የተረጋገጠ ደብዳቤ እንደሌለህ ጃንሆይ ጉዳይ ብለው አይቀበሉህም ፤ አስቀድመህ እወቀው ። ይኸንን ሁሉ ነገር በብዙ አድርጌ አሁን ሳንተ ስወዳጄ ማመልከቴ ሳትነሣ የጃንሆይን አሳብ እንድትረዳው ። አንተም በከንቱ መንገድ እንዳይመታህ ብዬ ነው ። እነዚህን ሁለት ትልልቅ ፍሬ ነገሮች በውል ለመፈጸም ከመጣህ የቀረው ነገር አያስቸግርም ። ጃንሆይ ከፍቅር ማደስ በቀር ሌላ አሳብ የለባቸውም (የላቸውም) ። ይልቅ አንተኑ የተላክህበት ነገር በቶሎ እንዲቀናህ ይረዱሀል እኔም እንደ ልማዴ በፍቅርና በማክበር አልረሳህም ። ከማዥር ሣልሳም ጃንሆይን ቆቦ ድረስ ሸኝቶ የተመለሰ ጊዜ የተነጋገርነው ቃል እንዲህ ነው ። ከኢጣልያ መንግሥት አንድ ትልቅ ሰው ባለ ሙሉ ሥልጣን የእርቅን ነገር ተነጋግሮ የሚፈጽም ሰው እስከመጣ (እስኪመጣ) ድረስ



ሠራዊታችሁ መረብን አይሻገር ፤ የኛም አይሻገርም ብለን ነገር እስኪፈጸም አቆይተነዋል ። ጤና ይስጥህ ። ተጻፈ ሐረር በነሐሴ 7 ቀን 1888 ዓ.ም.[1]

ይኸን ሁሉ የተሟላ ጥያቄ ላፄ ምኒልክ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ አስታውቆ ኖሮ ወዲያው ከንጉሠ ነገሥቱ "ይለፍ ፤ አትከልክለው" የሚል ለራስ መኰንን ደርሷቸዋል ። ለራሱም ጳጉሜ 2 ቀን 1888 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ምንም ችግር እንዳያገኘው እንዲያውም በማናቸውም ዕርዳታ እንዲያደርጉለት ማኅተማቸው ያለበትን የይለፍ ወረቀት ጽፈው ልከውለታል ። ስለዚህ በዘይላ በኩል አድርጎ ጊዜው የክረምት መውጫ ስለነበረ ከነጓዙ በችግር ሐረር ገባ ። ራስ መኰንንም በክብር ተቀብለው መልካም መስተንግዶ አደረጉለት ። ከዚያም ጓዙን የሚጭንበት አጋሰስና ለርሱ በመረሻት ያጌጠች ሠጋር በቅሎ ከሰጡት በኋላ ፣ ወደ አዲስ አበባ ተጉዞ በመስከረም ወር መጨረሻ ላይ 1889 ዓ.ም. (በአውሮፓ አቆጣጠር) ጥቅምት 6 ቀን 1896 ዓ.ም. አዲስ አበባ ደረሰ ።[2]

እንደ እውነቱ ይኸን የመሰለው ሰውዬ ፣ እንደዚህ ያለውን ከፍተኛ ሥልጣን ተቀብሎ ልምጣ ሲል የኢጣልያ መንግሥትም እሱን ሲወክል የኢትዮጵያ መንግሥት የሰውየውን ያለፈውን አድራጎትና የደረጃውንም ዝቅተኛነት ጠቅሶ ለመቃወምና ለዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ስለኢትዮጵያ የተሻለ ስሜት ያለውን ባለሥልጣን ለመጠቆም በቻለ ነበር ። የኢጣልያ መንግሥትም እምቢ ለማለት ባልደፈረ ነበር።

ነገር ግን ፣ በብዙ ያስተዳደር ጣጣ የተከበቡት ዐፄ ምኒልክ ከቅርብ ረዳቶቻቸው በመምከር ፣ "በኢጣልያ መንግሥት የግል ጉዳይ ገብተን እገሌ ይሁን እገሌ አይሁን ማለት አይገባንም ። የንጉሥ ማኅተም ያለበት ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ የመጣውን ማናቸውንም ሰው እንቀበላለን" የሚል ስሜት አድሮባቸው ይሆናል ።

1 Archivio storico Diplomatico. poz. 1. 1pos 1. 7 ROMA
2 Precursori del Impero Africano - R. Truffi PP.159 -163